አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ

(በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)

በ

ብርሃነሽ ሻንቆ

ሰኔ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ

(በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለ በተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ብርሃነሽ ሻንቆ

ሰኔ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ**

**(በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**
**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**
**የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር**

**ለ በተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት**

**በ**

**ብርሃነሽ ሻንቆ**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| ------------------------------------ | ----------------------- |
| **አማካሪ** | **ፊርማ** |
| ------------------------------------------ | ----------------------- |
| **ፈታኝ** | **ፊርማ** |
| ------------------------------------------ | ----------------------- |
| **ፈታኝ** | **ፊርማ** |

## ማረጋገጫ

የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ፣ በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማነኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም -----------------------------------------------------------------------

ፊርማ------------------------------

ቀን -------------------------------

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለልኡል እግዚአብሄር ምስጋና ይግባው እላለሁ። ከዚህ በመቀጠል ጥናቴን ከመነሻው እስከ መጨረሻ ድረስ በሚገባ እንዳከናውን ጊዜውንና እውቀቱን ሳካፈለኝ አማካሪዬ ታደሰ ሲባሞ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በሌላ በኩል ለጥናቴ መረጃ ሳይታክቱ ለሰጡኝ በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹረም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

በመጨረሻም ይህንን ፅሁፍ ከረቂቁ ጀምሮ አሁን እስከደረሰበት ድረስ ለፃፈችልኝ ለስራ ባልደረባዬ፣ ወይዘሮ ዘውዲቱ አባይ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

# አበርክቶ

ይህ ጥናት በዘላለማዊ ፍቅሩ እና በእውነተኛ የትዳር ጓደኝነት ተምሳሌቱ ከጎኔ በመሆን ለዚህ እንድበቃ ሁለንተናዊ ድጋፍ ሳይለየኝ ለረዳኝ እና ዛሬ ላይ በአካል ሳይሆን በመንፈስ ከጎኔ ላለው ለውድ ባለቤቴ ለመምህር ጌታሁን ደጀኔ መታሰቢያ ይሁንልኝ፡፡

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማ በሹርሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከተማሪዎቻቸው ጽሁፋዊ ስራ ጋር መመርመር ነው፡፡ በጥናቱም አይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ጽሁፋዊ ግብረመልሱን ፈትሿል፡፡ በትምህርት ቤቱ የሚገኙ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ የጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተመርጠዋል፡፡ ለጥናቱ እንደ ዋና መረጃነት ያገለገሉት በመምህራን ታርመው የተመለሱት የተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃዎች፣ የመምህራን ቃለ መጠይቅና የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቆች ናቸው፡፡ ታርመው የተመለሱ የጽሁፍ መልመጃዎች ከግብረመልስ አይነቶች፣ ከአሰጣጥ ስልት፣ ከትኩረት አቅጣጫና ከባህሪያት አንጻር ተተንትነዋል፡፡ በዚህም መሰረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአብዛኛው ገምጋሚ ግብረመልስን መጠቀማቸው፣ የግብረመልስ ስልቶችን በመጠኑም ቢሆን እያሰባጠሩ መጠቀማቸው፣ ቅርጽና ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ መስጠታቸው፣ የትምህርቱን ይዘት እና አላማ መሰረት አድርገው የተመጠነ አስተያየት መስጠታቸውና ግብረመልስ የሰጡባቸው ወረቀቶች በተወሰነ መልኩ በጊዜ አለመመለሳቸውንም ጥናቱ ያሳያል፡፡ በመጨረሻም መምህራን ሁሉንም የግብረመልስ አይነቶችን እንደ አስፈላጊነታቸው እያጣመሩ ቢሰጡና ግብረመልሱም ውጤታማ እንዲሆን በጊዜው ቢሰጥና ለተማሪዎች ማስተካከል ያለባቸውን ነገር ቢጠቆም ጥሩ ነው፡፡*

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና ........ ii
አጠቃሎ ........ iii
ማውጫ ........ v
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ vii
አህጽሮተ ቃላት ........ viii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ........ 5
1.4 የጥናቱ ዓላማ ........ 5
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 6
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 7
1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ አማራጮች ........ 7
ምዕራፍ ሁለት ........ 8
ክለሳ ድርሳናት ........ 8
2.1. የተዛማጅ ድርሳናት ቅኝት ........ 8
2.1.1. የግብረመልስ ምንነት ........ 8
2.1.2 የግብረመልስ አይነቶች ........ 9
2.1.3 የግብረመልስ ጠቃሜታዎች ........ 10
2.1.4 በግብረመልስ ላይ የመምህር የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 11
2.1.5 የግብረመልስ አቀራረብ ስልት (ዘዴ) ........ 11
2.1.6 ግብረመልስ የሚሰጥበት ጊዜ ........ 13
2.1.7 የጽሁፋዊ ግብረመልስ ባህሪያት ........ 14
2.2 የቀደምት ስራዎች ቅኝት ........ 14
ምዕራፍ ሶስት ........ 18
የጥናቱ ዘዴ ........ 18
3.1 የጥናቱ ስልት ........ 18
3.2 የናሙና አመራርጥ ........ 18

3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ............ 18
3.2.2 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ............ 19
3.2.3. የተማሪዎች እና የመማሪያ ክፍሎች ናሙና አመራረጥ ዘዴ ............ 19
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ............ 20
3.3.1 ሰነድ ፍተሻ ............ 20
3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ ............ 20
3.3.3 ቃለ መጠይቅ ............ 21
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ............ 21
ምዕራፍ አራት ............ 22
የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ ............ 22
4.1 ጠቅላላ መረጃ ............ 22
4.2 የመምህራን ግብረመልስ ከጽሁፋዊ ግብረመልስ አይነቶች፣ ስልቶች ባህሪያትና ከትኩረት አቅጣጫ የተሰጠ ትንታኔ ............ 25
4.2.1 ከጽሁፋዊ ግብረመልስ አይነቶች አንጻር የመምህራን ምላሽ ............ 25
4.2.2 የጽሁፋዊ ግብረመልስ ስልቶች ............ 33
4.2.3 ከግብረመልስ አሰጣጥ የትኩረት አቅጣጫ አንጻር ............ 42
4.2.4 ከግብረመልስ መገለጫ ባህርያት አንጻር ............ 46
4.2.5 በተማሪዎች የጽሑፍ ስራ ላይ ግብረመልሶችን በጊዜው ከመስጠት አንጻር ............ 52
4.3 ከመጠይቅ የተገኘ የተማሪዎች መልስ ............ 55
4.3.1 የመምህራን የግብረመልስ አይነት አተገባበር በተመለከተ ከተማሪዎች የተሰጠ ምላሽ ............ 55
4.3.2 የመምህራንን የግብረመልስ አይነት አተገባበር በተመለከተ ተማሪዎች ለጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት መረጃ ............ 57
4.3.3 ከጽሁፋዊ ግብረመልስ ስልቶች አንጻር ከተማሪዎች መጠይቅ የተወሰደ ምላሽ ............ 59
4.3.4 የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ባህሪያት በተማሪዎች እይታ ............ 62
4.3.5 ግብረመልስ ከጊዜ፣ከመጠንና ከግልጽነት አንጻር ............ 63
ምዕራፍ አምስት ............ 677
ማጠቃለያና አስተያየት ............ 67
5.1 ማጠቃለያ ............ 67
5.2 አስተያየት ............ 70
ዋቢ ጽሁፎች ............ 72
አባሪዎች ............ 75

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ አንድ፡- ለናሙና የተመረጡ መምህራን፣ ተማሪዎችና የመማሪያ  ክፍሎች ብዛት.....22

ሰንጠረዥ ሁለት፡- ግብረመልስ የተሰጠባቸው ሰነዶች ብዛት.....24

ሰንጠረዥ ሶስት፡- በተከታታይ ሶስት የተማሪ ወረቀቶች ላይ መምህራን የሰጧቸው የግብረመልስ አይነቶችና ድግግሞሽ.....26

ሰንጠረዥ አራት፡- በተከታታይ ሶስት የተማሪዎች ወረቀቶች ላይ መምህራን የተከተሏቸው የግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶች ብዛት.....36

ሰንጠረዥ አምስት፦የመምህራንን የግብረመልስ የትኩረት አቅጣጫ የሚያሳይ ሰንጠረዥ.....43

ሰንጠረዥ ስድስት፦ የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ባህሪያት ብዛት.....50

ሰንጠረዥ ሰባት፤-የመምህራን የግብረመልስ አይነት አተገባበር.....56

ሰንጠረዥ ስምንት፦የመምህራን የግብረመልስ አይነት አተገባበር በተመለከተ ተማሪዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት መረጃ.....57

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡-የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶችን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ.....59

ሰንጠረዥ አስር ፦የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ባህሪያት.....62

ሰንጠረዥ አስራ አንድ፡- አጠቃላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጣቸውን የሚያሳይ..64

# አህጽሮተ ቃላት

| | |
|---|---|
| መ.1 | መምህር አንድ |
| መ.2 | መምህር ሁለት |
| መ.3 | መምህር ሶስት |
| መ.4 | መምህር አራት |
| ጽ.1 | ጽሁፍ አንድ |
| ጽ.2 | ጽሁፍ ሁለት |
| ጽ.3 | ጽሁፍ ሶስት |
| ቁ. | ቁጥር |
| ተ.ቁ | ተራ ቁጥር |

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ዜጎችን ማስተማር የመንግስት ተቀዳሚ ተግባር መሆኑ የማይካድ ነገር ነው፡፡ በማንኛውም የትምህርት መስክ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን እውቀት፣ አስተሳሰብ እና ክህሎት በመምህራን እገዛ ከግብ መድረስ የትምህርት ፖሊሲው ዋና ዓላማ ነው፡፡ በተለይ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ሆነ በሁለተኛ ቋንቋቸው የሚሰጣቸውን የትምህርት አይነት በተገቢው መንገድ በመረዳት በትምህርታቸው ለውጥ ያመጣሉ ተብሎ ይታሰባል በማለት Brookhart (2008 : 1) ይገልጻሉ፡፡

የተለያዩ ምሁራን እንደሚያስረዱት በአፍ መፍቻ እና በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማር ተቀዳሚ አላማው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂላቸው በታቀደው እና በተጠበቀው መልኩ ከወትሮው የዳበረ ለውጥ እንዲያመጡ ነው፡፡ በተለይ በቋንቋ ትምህርት ላይ ተማሪዎች የሰዋስው እና የስነ ጽሁፍ እውቀት እንዲኖራቸው ማስቻል ተቀዳሚው ዓላማ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ እታለማሁ (2006:1) እንዲህ በማለት አስረድተዋል፡፡ ተማሪዎች የሚተላለፈውን መልዕክት አዳምጠው የመረዳት፣ የቀረበላቸውን ጽሁፍ የማንበብ፣ ሀሳባቸውን ያለፍርሃት የመግለጽ፣ በተጨማሪም ደረጃቸውን የሚመጥን የአጻጻፍ ስርዓት ተከትለው ሀሳባቸውን በጽሁፍ መወከል መቻል በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ሊዳብሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች ከንባብ ሊያዳብሩት የሚችሉትን ክህሎቶች ማለትም የፊደል አጣጣል እና ቅርጽ፣ የአረፍተ ነገሮችን መልዕክት እንዲሁም ጠቅላላ ጽንሰ ሃሳብ ካለመረዳት የተነሳ ሃሳባቸውን በጽሁፍ ወክለው በሚጽፉበት ወቅት የተለያዩ ስህተቶች ሲፈጽሙ ይስተዋላሉ::

ከመማር ማስተማር ሂደት መረዳት እንደሚቻለው እነዚህ ስህተቶች ቀጣይነት ላይ ባተኮረ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በተቻለ መጠን ሊቀረፉ ብሎም ጠቅላላ ሊወገዱ የሚችሉ ክስተቶች ናቸው፡፡ ስህተቱ ሊቀነስም ሆነ ሊቀረፍ የሚችለው በተማሪዎች የጽሁፍ ክህሎታቸው ላይ መምህራን ትኩረት ሰጥተው ተገቢውን የጽሁፍ እርማት ሲሰጡ ነው፡፡

በተለይ በአሁኑ ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን አስመልክቶ የተማሪዎችን ሆነ ሙያቸው አስገድዷቸው የሚጽፉ ጸሀፍት ጽሁፎች ደካማ እንደሆኑ ሌሎች ጥናቶችም አመልክተዋል፡፡ ከእነዚህም ጥናት መካከል (ጌታቸው 2001 እና ኢሳያስ 2002)ተጠቃሽ

ናቸው፡፡ አጥኚዎቹ በጥናታቸው እንዳስፈሩት በ1ኛ ደረጃም ሆነ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የጽሕፈት ክህሎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

ይሁን እንጂ ችግሩ ቋንቋው በትምህርትነት ቢቀርብም የክሂሉ አሰጣጥ የተዳከመና በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትኩረት የተነፈገው እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት በ2ኛ ደረጃ በ9ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በክሂሉ ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ከመምህራን ግብረመልስ ጋር በማገናዘብ ይመረምራል፡፡

በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ መምህራን እርማት የሚሰጡበት መንገድም ጽሁፋዊ ግብረመልስ የምንለው አይነት ነው፡፡ ጽሑፋዊ ግብረመልስ አጠቃላይ የጽህፈት ክሂል እንዲዳብርና ተማሪዎች ጥሩ ተግባቦትና የሀሳብ ፍሰት ያለው ጽሁፍ እንዲጽፉ ለማስቻል የሚሰጥ ነው፡፡ ስለዚህም ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከጽሁፍ ክሂል ተለይቶ የማይታይ የጽህፈት ክሂል እንዲጎለብት የሚያስችል፣ በተለያዩ የጽህፈት ተግባራት ወቅት ሊተገበር የሚችል፣ የጸሐፊውን ስህተት ለመቀነስ የሚያግዝ የማስተማሪያ ስነዘዴ ነው በማለትZamel (1985:117) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በጽሁፍ አማካኝነት የሚሰጣቸውን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችና ግቦች መምህራን ካነበቡ በኋላ በጽሑፍ የሰፈረው ሀሳብ በትክክል መጻፍ አለመጻፉን በመረጃ አስደግፈው የሚሰጡት ግብረመልስ እንደሆነም Brookhart (2008:1)ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ግብረመልስ ተማሪዎች በጻፏቸው ጽሁፎች ላይ ያሉ ስህተቶች እነዚህ ናቸው፤ በዚህ መልክ መስተካከል አለባቸው፤ ስህተቱ እንዲፈጠር የሆነው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በማለት እና ጥሩ ሙከራዎችን በማሳየት ለቀጣይ ጥሩ የጽሁፍ ስራ የሚጋብዝ አሰራር ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

እንግዲህ በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የመጻፍ  ክህሎታቸው በምን ያህል ደረጃ እየተሻሻለ መሆኑን በመከታተል እና ተገቢውን እይታ ከግብረ መልስ ጋር በማጣጣም ለውጥ እንዲያመጡ የመምህሩ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ሊኖረው እንደሚገባ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡ ጽሁፋዊ ግብረመልስን በተመለከተ የተለያዩ ጸኃፍት የተለያዩ አስተያየቶችን እና ትንታኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ ለምሳሌ Brookhart (2008: 1) ፣ Atkins, et al. (1996:11)፣ Byrne (1988:124)፣ Pincas (1982:116) እንደገለጹት ተማሪዎች ፊደላትን እንደ ቅርጻቸው እና አነባበባቸው ከንባብ ክህሎት በመረዳት የጽህፈት ችሎታን ለማሳደግ የሚያግዝ በክፍል ውስጥ ከሚሰጠው ትምህርት ጋር የሚተገበር የማስተማሪያ አካል ነው፡፡ ይህም ማለት የቋንቋ መምህሩ የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ሲያስተምር በተማሪዎች የልምምድ ስራዎች ወቅት አስተያየት ለመስጠትና ለመገምገም ብሎም የተጠበቀውን ለውጥ እንዲያመጡ የሚጠቀምበት ዘዴ ነው፡፡

ተማሪዎች በሚጽፏቸው ጽሁፎች ላይ ግብረመልስ የመስጠት ስራን መምህራን በሚያስተምሩት የቋንቋ መርሃ ግብር ላይ ሊተገብሩት ይገባቸዋል፡፡ ምክንያቱም በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የመልመጃ አዘገጃጀት ላይ መሰረት ያደርገ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ በክሂል ዓይነት ተከፋፍለው ስለሚቀርቡ መምህሩ ሁሉንም ክህሎቶች መተግበር ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ፡- Byrne (1988:124) እንደሚሉት “ግብረመልስ ውጤታማነቱ የጎላ እንዲሆን ተማሪዎች እየተማሩ ባሉበት ሂደት በተገቢው ቦታና ጊዜ ሊሰጥ መቻል እንዳለበት ያሳስባሉ፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የቋንቋ ትምህርትን ማስተማር እና መለማመጃዎች መስጠት ብቻ ሳይሆን ከትምህርቱ በኋላ የሚሰጧቸው ግብረመልሶች ላይ አስቀድሞ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ”ይህ ማለት ግብረመልስ ውጤታማ እንዲሆን መምህሩ ለሰጠው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ ሁልጊዜ እየተከታተለ በጊዜው ግብረመልስ መስጠት አለበት፡፡ ይህን መሰረት በማድርግ ተማሪዎች የሚፈለገውን የቋንቋ ክህሎት እና እውቀት ሊጨብጡ ይችላሉ፡፡ ይህም የሚሆነው መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ ትግበራዎች ላይ የሚታዩትን ጉድለቶች ወይንም ግድፈቶች ማወቅ ሲኖርባቸው ነው፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት እንዲያዳብሩ ተብሎ ከተደራጁ ከመሰረታዊ የቋንቋ ይዘቶች እና የክሂል ትምህርቶች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዳቸው ክሂሎች የየራሳቸው የሆነ መገለጫ አላቸው፡፡ በመምህሩ እና በተማሪው መካከል የመደማመጥ፣ የመስማማት እና በየግዜው በክፍል ውስጥ በቃል የሚተላለፉ መረጃዎችን በአግባቡ ወደ ተግባር የመቀየር ከቋንቋ ክህሎቶች ጥቅም ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በተጨማሪም የመጻፍ ክሂል ተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን በትክክል ከማዳመጥ በመቀጠል የተሰጣቸውን የጽህፈት መልመጃ በመስራት የመጻፍ ክሂላችውን ሚያዳብሩበት መንገድ ነው፡፡ በዋናኝነት የተማሪዎች የንባብ ክህሎት የተለያዩ የፊደል ቅርጾችን ከነፊደል አጣጣላችው እና የድምጽ አወጣጣቸው የሚያዳብርላቸው ከመሆን ባለፈ የመጻፍ ክሂላቸው የበለጠ እንዲሻሻል ይረዳቸዋል፡፡ ስለዚህ ከነኚህ ሃሳቦች በመነሳት የተማሪዎችን የጽህፈት ክህሎት ማነጽ ከሁሉም የቀደመ ተግባር እንደሆነ ለመረዳት አያስቸግርም፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የቋንቋ ትምህርት አላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበር ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ የጽህፈት ክሂል አንዱ ነው፡፡ የጽህፈት ክሂሉ ለመጀመሪያ ቋንቋም ሆነ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ አስቸጋሪ መሆኑን Kroll(1990) ገልጸዋል፡፡

ችግሮቹ የመጡትም ከስነልቦናዊ ችግሮች፣ ከአእምሮአዊ ችግሮች እና ከስነልሳናዊ ችግሮች መሆናቸውን Byme(1991) አብራርተዋል፡፡ ከላይ ምሁራኑ እንደገለጹት ክሂሉ ከባድና አስቸጋሪ በመሆኑ የተነሳ አጥኚዋ ጥናቱ የምሁራኑ ሃሳብ ትክክለኛና ጥናቱንም የሚደግፍ ሆኖ አግኝተዋለች፡፡

የጽህፈት ክሂል ትኩረት የሚሰጠው ከቋንቋ ክሂል ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ለጽህፈት ክሂል መዳበርም መሰረት የሚሆነው ከ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀጥሎ ማደግ እንዳለበት የሚጠበቅ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ የክፍል ደረጃ የጽህፈት ክሂል አለመዳበር ችግር እየሆነ መጥቷል፡፡ በ1ኛም ሆነ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ድርሰትን ሳንጽፍ ከትምህርት ቤት የምንወጣ ቁጥራችን ጥቂት አይደለም፡፡ በተለይ ከ10 እና ከ15 ዓመታት ወዲህ በተማሪዎች ቁጥር መብዛት ከትምህርት ክፍለጊዜ መብዛትና በመሳሰሉ ምክንያቶች እየተሳበበ የሚጻፈው ሳይታረም ይቀራል፡፡ የተጻፈው ካልታረመ ደግሞ ስህተት ወይም ትክክል መሆን አለመሆኑ ስለማይታወቅ ካለመጻፍ ብዙም አይለይም በማለት ተስፋዬ (1986:9) ይገልጻሉ፡፡

ይህ ማለት ተማሪዎች የጽህፈትን ክሂል የሚለማመዱት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በመቀጠል ከ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሂደት እያዳበሩት ይሄዳሉ፡፡ ተማሪዎች ባሉበት የክፍል ደረጃ ይደርሳሉ ተብሎ የሚጠበቅ የእውቀት ደረጃ አለ፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የጽህፈት ክሂል በተለያዩ ችግሮች ከዕለት ወደ ዕለት እየቀነሰ ይገኛል ማለት ነው፡፡

የጽህፈት ክሂል የሚፈለግበት ደረጃ ላይ አለመድረሱን ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ባየ(2009)ን መመልከት ይቻላል፡፡ ከ2ኛ ደረጃ የጨረሰ ተማሪ ዛሬ ጥሩ የሥራ ማመልከቻ ቀርቶ ጥሩ ደብዳቤ እንኳን በወጉ መጻፍ እየተሳነው መጥቷል፤ ከሁለት ያጣ ጎመን እንደሆነ ነው፡፡ ከስርዓቱም ሆነ ከክህሎቱ የለበትም፡፡ እንግዲህ ተማሪዎች በጽሁፍ ክሂል እና በሰዋሰውም በኩል በቂ ችሎታ እንደሌላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተማሪዎች በየትኛውም ደረጃ ድርሰትን መጻፍ ባይችሉ ወይም ሀሳብን በሥርዓት በጽሁፍ ማስፈር ቢሳናቸው የሚደንቅ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ከፍ ብለው ከጠቀሱት ከተለያዩ ችግሮች አኳያ ድርሰትን ማስተማር እና ማለማመድ የተተወ ሆኗል፤ ከዚህም የተነሳ የተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ክሂል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ተማሪዎች የጽሁፍ ስራ በተለይ ድርሰትን ማለማመድ እየቀነሰ መምጣቱን ነው፡፡ የተማሪዎች የጽህፈት ክሂል መጎልበት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ነገርግን በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ችግሮች እየተስተዋሉ ይገኛሉ፡፡

በመጀመሪያ አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለማድረግ ያነሳሳት ነገር በተለያዩ የተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃዎች ላይ የጽህፈት ችግሮች በተማሪዎች ሲፈጸም ስላጋጠማት ነው። ለምሳሌ፡- ተማሪዎች በሚሰጣቸው ዓረፍተ ነገር የመስራት፣ አሳጥሮ የመጻፍ፣ አስፋቶ የመጻፍ፣ የሕይወት ታሪካቸውን የመጻፍ እና ወዘተ. ጊዜ የሚጽፉት ጽሁፎች የሥርዓተ ነጥብ ጉድለት፣ የሃሳብ መዘበራረቅ፣ የሰዋሰው ስህተቶች፣ መስመር ያለመጠበቅ እና የመሳሰሉት ችግሮን ተማሪዎች ሲፈጽሙ አስተውላለች። በመቀጠል አጥኚዋ ከላይ የተዘረዘሩት የጽህፈት ችግሮች ተማሪዎች እንዳይሰሩ እና ለወደፊቱ በጽህፈት ስራቸው ላይ የሃሳብ መቆራረጥ፣ የስርአተ ነጥብ ጉድለትና ወዘተ. እንዳይኖር ከማሰብ የተነሳ መምህራን ግብረመልስ ቢሰጡ ችግሮቹ ይቀረፋሉ ብላ በማሰቧ ነው። በመሆኑም ከእነዚህ ችግሮች በመነሳት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ ግብረመልስ አተገባበራቸውን ለመፈተሽ ተነሳስታለች።

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን መሪ ጥያቄዎች ይመልሳል ።

1. በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ ስራ ላይ የጽሁፋዊ ግብረመልስ አይነቶችን አመጣጥነው ይሰጣሉ ወይ?
2. .የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ ላይ ትኩረቶች ምን ምን ናቸው?
3. የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ ከመዋቅር አንጻር ምን ይመስላል?
4. የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ ከይዘት አንጻር ምን ይመስላል?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማው በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስን ከተማሪዎች ጽሁፋዊ ስራ ጋር መመርመር ነው።

ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል።

1. መምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ በሚሰጡበት ወቅት የግብረመልስ አይነቶችን አመጣጥነው መስጠት አለመስጠታቸውን ከተማሪዎቹ ቅበላ ጋር በማመሳከር መመርመር፡፡

2. የመምህራንን የፅሑፋዊ ግብረመልስ አስተያየት አሰጣጥ ትኩረታቸው ምን ምን እንደሆኑ መፈተሸ ፡፡

3. የመምህራን የግብረመልስ አሰጣጣቸው ከመዋቅር አንጻር ምን እንደሚመስል መመርመር፡፡

4. የመምህራን የግብረመልስ አሰጣጥ ከይዘት አንጻር ምን እንደሚመስል መመርመር፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ተገቢ የሆነ የመምህራን ግብረመልስ በተማሪዎች የጽህፈት ክህሎት ላይ በመስጠት ረገድ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ከማዳበር አንጻር ብዙ ጠቀሜታዎች ይኖረዋል ብላ አጥኚዋ ታምናለች፡፡

- በመጀመሪያ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የግብረመልስ አሰጣጥ ዘዴያቸውን ካለው ነባራዊ የመማር ማስተማር ሂደት ጋር በማጣጣም እንዲያስኬዱ የሚያስችላቸውን ደረጃ እንዲተገብሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

- በተመሳሳይ የመምህራን የግብረመልስ አሰጣጥ ላይ ትኩረት ማድረግ ያለባቸውን ነገሮች እንዲያውቁ፣ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን ከወትሮው በመገንዘብ እንዲያዳብሩ መረጃ ይሰጣል፡፡

- ለመምህራን ከመዋቅር አንጻር የጽህፈት ግብረመልስ እንደሚሰጥ በመፈተሽ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡

- ለመምህራን ከይዘት አንጻር የጽህፈት ግብረመልስ አስጣጣችውን በመፈተሽ ለመምህራን ግንዛቤ ይሰጣል፡፡

- በዚህ ጥናት ርዕስ ዙሪያ ተመሳሳይ እና ሰፋ ያለ ጥናት ለሚያካሂዱ ባለሙያዎች የጥናት መነሻ በመሆን ሊያገለግል እንደሚችል ይገመታል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚከናወነው በሌሞ ወረዳ በሚገኘው በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ባሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች እና በተጠቀሰው ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በ2015 ዓ.ም ከጥር ወር እስከ ግንቦት ወር ማለትም የ4 ወራት መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ ስራ ላይ ግብረመልስ ሰጥተው የተመለሱትን የጽሁፍ ይዘቶች፣ አንቀጾች፣ አሳጥሮ መጻፍ ወይም አስፋፍቶ መጻፍ፣ ደብዳቤዎች፣ የሕይወት ታሪኮች እና አጫጭር ድርሰቶች ናቸው፡፡ ጥናቱ ትኩረት የሚያደረገው መምህራን ግብረመልስ በሚሰጡባቸው በመጻፍ ክህሎት ላይ ብቻ ተወስኖ ሌሎች ክሂሎችን አይጨምርም፡፡ ከመምህራን በሚወሰድ ቃለ መጠይቅ እና ከተማሪዎች በሚወሰድ የጽሁፍ መጠይቅ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ነገር ግን ለጥናቱ ከዚህ በበለጠ ጊዜ ቢጨመር ከተለያዩ ክፍሎች ጋር አጣምሮ ቢጠና ከዚህ በተሻለ አስፍቶ መስራት ይቻል ነበር፡፡

## 1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ አማራጮች

በማንኛውም ጥናታዊ ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአፈጻጸም ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ የታወቀ ነው፡፡ ይህን ጥናት ከግብ ከማድረስ አኳያ ያጋጠሙ ችገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም ችግሮች መካከል አንዱ በጥናቱ ሂደት መረጃ አቀባይ የሆኑ ተማሪዎች ትክክለኛውን ምላሽ ከመስጠት ወይም እውነተኛ ባህሪያቸውንና መረጃውን ከማሳየትና ከመግለጽ ይቆጠቡ ይሆናል የሚል ስጋት አለ፡፡ የመረጃ አቀባይ ተማሪዎች ችግርን ለማቃለል የተለያዩ መረጃ መቀበያ ስልቶች ላይ በመመርኮዝ የመረጃዎችን ትክክለኛነት መስቀለኛ በሆነ መንገድ የማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የተዛማጅ ድርሳናት ቅኝት

### 2.1.1. የግብረመልስ ምንነት

ግብረመልስ ማለት የተማሪዎችን የጽሁፈት ክሂል ለማዳበር የሚጠቅም አስተያየት ወይንም ምክር የያዘ በመምህራን የሚሰጥ ግብአት ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በሚጽፉት የተለያየ የጽሁፍ ስራ ላይ መምህራን ተማሪው ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚሰጡት እርማት ነው፡፡ የተማሪዎች የጽህፈት ስራ ትክክል መሆኑን በመምህራን ስለሚረጋገጥ  መምህራን ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ስለ ግብረመልስ ምንነት የተለያዩ ምሁራን ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡ እንደ Wajnery (1992:49) አገላለጽ ግብረመልስ ተማሪዎች ለሰሩት ማንኛውም ክንውን የተማሪዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ መምህሩ የሚሰጠው አጸፋዊ ምላሽ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ስለ ግብረመልስ ምንነት ብዙ ተመራማሪዎች አንድ በሚያደርጋቸው ሃሳብ ሲገልጹት ግብረመልስ በተማሪዎች በኩል በጽሁፍ የተቀናጁ መልሶችን የቋንቋ መምህራን ካነበቡ በኂላ ለተማሪዎች መልሳቸው ትክክል ወይም ግድፈት አለበት  በማለት የሚሰጡት እርማት  ነው ይላሉ፡፡

Cole እና Lorena (1994) በበኩላቸው ሰለግብረመልስን ምንነት  እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ተማሪውና መምህሩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሀሳባቸውን በንግግር ከሚስማሙበት በተጨማሪ በጽሁፍም ሀሳባቸውን ይለዋወጣሉ፡፡ ይኸውም መምህሩም ሆነ መማሪያ መጽሐፍ በሚያዘው መልመጃ አማካኝነት ተማሪው ጽህፈት እንዲለማመድ ይደረጋል፡፡ ተማሪው በጽሑፍ የሰራውን ስራ መምህሩ አስተያየት ይሰጥበታል፡፡ ይህ አይነት አስተያየት የሚሰጥበት ክንውንም ጽሁፋዊ ግብረመልስ ይባላል፡፡ ይህንን የሃሳብ ልውውጥ Hyland (1990:230) በበኩላቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በሚገልጹበት ጊዜ ያላቸውን ችሎታ አስመልክቶ መረጃ ለመስጠትና የሚታይባቸውን ስህተት ለመቀነስ የሚያግዝ የትምህርት ክንዋኔ አጋዥ መሳሪያ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ በሚገልጹበት ጊዜ የጽሕፈት ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለመለየትና ሀሳባቸውን በጽሁፍ ለማስተላለፍ ሲሉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመቀነስ የሚያስችል ከማስተማሪያ ስነ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ግብረመልስ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማከናወን የሚያመችና እንደ አንድ ማስተማሪያ ዘዴ የሚያገለግል መሳሪያ ነው ለማለት ያስችላል ፡፡

### 2.1.2 የግብረመልስ አይነቶች

የግብረመልስ አይነቶችን በተመለከተ ምሁራን በተለያዩ ክፍሎች በመመደብ ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡ ለምሳሌ፡- አመቻች ግብረመልስ አንዱ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ Moxely (1989) ሲያብራሩ ይህ የግብረመልስ አይነት በተማሪዎች የጽሁፍ ስህተት ላይ በአብዛኛው በጥያቄና በአስተያየት መልክ የሚቀርብ (የሚሰጥ) ግብረመልስ ሲሆን ጥያቄዎቹ በተወሰነ ጉዳይ ላይ በማተኮር ጠቅለል ባለ ሁኔታ በማቅረብ የሚከናወን እርማት ነው፡፡ ይህም ሲባል ግብረመልሱ የሚያተኩረው ከቋንቋው ቅርጽ ይልቅ በቋንቋው ይዘት ላይ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ሌላው ትዕዛዛዊ ግብረመልስ የሚባል ሲሆን ተማሪዎች የራሳቸውን ስህተት ራሳቸው እንዲያስተካክሉ በትእዛዝ መልክ መምህሩ ግብረመልስ የሚሰጥበት አካሄድ እንደሆነ (Anker 2000 እና Duker 1989) ይገልጻሉ፡፡ ይህ የግብረመልስ አይነት ተማሪዎች ምን አይነት ስህተት እንደሰሩ እና እንዴት መታረም እንዳለበት የሚረዱበት አይነት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹ የጻፉትን ጽሁፍ ይዘት ስለሚያውቁት ቶሎ እርማቱን ለመስጠት አይቸገሩም፡፡ ነገር ግን የተማሪዎችን የጽህፈት ችግር ለመቅረፍ ያለው ጠቀሜታ ያነሰ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ የራሳቸውን እርማት ስለሚፈልጉ ምን ያህል በታማኝነት አስተካክለው ይወስዱታል የሚለው ነገር አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የግብረመልስ ዘዴ ብዙም ተቀባይነት የለውም በማለት Moxely (1989) አብራርተውታል፡፡

አስተካካይ ግብረመልስን በተመለከተ (Anglo and Cross 1993) እንደሚሉት ይህ ግብረመልስ ተማሪዎች የፈጸሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች በመጠቆምና ስህተቶችን አስተካክሎ ቀጥተኛ ምላሽ በመስጠት የሚተገበር ነው፡፡

የግብረመልስ አሰጣጡም በተለያየ ዘዴ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በማጥፋት፣ በመጨመር፣ ቅደም ተከተልን በማስተካከልና የሳቱትን በማስተካከል እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ በተጨማሪም የሥርዓተ ነጥብ ስህተቶችን፣ የተሳሳቱ ቃላትንና ሀረጋትን፣ በስህተት የገቡ አያያዦችን፣ የዓረፍተ ነገር ድግግሞሽን፣ ሳይጻፉ የተዘለሉ ቃላትና ሀረጋትን በመሙላት ማስተካከል ናቸው፡፡

የመጨረሻ የግብረመልስ አይነት ገምጋሚ ግብረመልስ ይባላል፡፡ እንደ Daiker (1989) አተናተን ይህ ግብረመልስ ተማሪዎች በጽሁፋቸው ላይ በመምህራን የሚሰጣቸውን ውጤት በማየት የጻፉት ጽሁፍ ምን ያህል ጥሩ ጽሁፍ እንደሆነ በቀጣይ ድርሰታቸው ቀሪውን ነጥብ ለመሙላት ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ የምላሽ አይነት ነው፡፡

ይህ የግብረመልስ አይነት ከተማሪዎች ጥሩ ውጤት ማምጣትና አለማምጣት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ጥሩ ስራ የሰሩትን ስለሚያበረታታ ጥሩ ያልሰሩትን ግን የመስራት ፍላጎታቸውን ይቀንሳል፡፡ ስለዚህ የዚህ ግብረመልስ አይነቱ በተማሪዎች የጽሁፍ ይዘት ላይ በማተኮሩ ያለው አስተዋጽኦ አነስተኛ መሆኑንም አያይዘው አብራርተዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት የትኞቹ የግብረመልስ አይነት በመምህራን እንደሚተገበር ለመመርመር ያለመ ነው፡፡

### 2.1.3 የግብረመልስ ጠቃሜታዎች

ግብረመልስ በቋንቋ ማስተማር ውስጥ የላቀ ጠቀሜታ አለው፡፡ የግብረመልስ ጠቃሜታዎችን በተመለከተ ብዙ ምሁራን እንደሚሉት ግብረመልስ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከሚከናወኑ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በተጨማሪም ግብረመልስ አንድን የትምህርት ይዘት ለማስተማር ይቻል ዘንድ እንደ አንድ የማስተማሪያ ዘዴ የሚያገለግል አስተግባሪ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እነJacobs (1981) ግብረመልስ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ነው ማለት  በግብረመልስ ስህተትን እንደ አንድ መረጃ ግብአት በመጠቀም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ግብረመልስ መምህራን የሚያስተምሩትን የትምህርት ይዘት ተማሪዎች ምን ያህል እንደተረዱት እንዲሁም ይዘውት የተነሱት አላማና ግብ ምን ያህል እንደተሳካላቸው ለመገምገም ያስችላቸው ዘንድ የሚጠቀሙበት መሳሪያቸው ነው፡፡ ከዚህም አንጻር ግብረመልስ ለመምህር ትልቅ ፋይዳ አንዳለው እና የተማሪዎች ጽሑፍ ስህተቶችን በግልጽ ለማሳየት ማስቻሉ ለመምህሩ ትልቅ እገዛ እንደሚፈጥርለት Kroll (1990)፣ Lee (1997) እና Leki (1990) ይገልጻሉ፡ ፡ ነገር ግን በግብረመልስ አሰጣጥ ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ጉዳዮች ብዙ እንደሆኑ ሒሩት (1997) የተባሉ ተመራማሪ ሲገልጹ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ የመምህራን የማስተማር ልምድና እድሜ፣ የመምህራን አመለካከትና ባህሪ ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ምሁራን የግብረመልስን ጠቀሜታ በመግለጽ መምህሩ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማተኮር አለበት በማለት ገልጸዋል፡፡

- የግብረመልስን አላማ ማወቅ አለበት፡፡
- የተማሪዎችን ደረጃ ማወቅ እና በደረጃቸው ግብረመልሶችን መስጠት፡፡
- የተማሪዎችን ጽህፈት የምናርምበትን መስፈርት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡
- የተማሪዎችን ጠንካራ እና ደካማ ጎን መለየት የሚሉት ናቸው፡፡

### 2.1.4 በግብረመልስ ላይ የመምህር የትኩረት አቅጣጫዎች

በመማር ማስተማር ሂደት ጽሑፋዊ ግብረመልስ ሲከወን በዋናነት ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች በቁጥር ብዙ ቢሆኑም ለዚህ ጥናት ይጠቅማሉ ተብለው የታሰቡትን በትንሹ ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ ስለሆነም ግብረመልስ ለመስጠት በመጀመሪያ መምህሩ የሚያስተምረውን የቋንቋ ትምህርት በሚገባ ሊያውቀው ይገባል፡፡ ለምሳሌ ይህን ሃሳብ Brookhart (2008:32) ሲያስረዱ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ለመስጠት መጀመሪያ ቋንቋውን በደንብ ልናውቀው (ልንረዳው) መቻል እንዳለብንእንዲሁምአንድ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ሲሰጥ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ጉዳዮች ግልጽነት እና ለዛነት የተሞላበት ምላሽ እንዲሆን ያሳስባሉ፡፡

በብዙ የዘርፉ ተመራማሪዎች እንደተገለጸው በተማሪዎች የጽህፈት መልመጃ ስራ ላይ ከመምህራን የሚቀርብ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ትኩረት ወቅት የፊደላትን አጻጻፍ (አጣጣል) እንዲሁም በጽሁፋዊ ስራው መዋቅር ወይም ቅርጽ እና በጽሁፉ ትርጉም ወይም ይዘት ላይ ሊሆን እንደሚችል Richards (1996) አስረድተዋል:: ከዚህ አኳያ መዋቅር ተኮር ግብረመልስ ትኩረቱ፡- በሆሄያት፣ በቃላት፣ በአረፍተነገሮች፣ በሰዋስዋዊ ስህተቶች፣ በስርዓተ ነጥቦች፣ ወዘተ. ላይ ሲሆን አብዛኞቹ መምህራን ምቅድሚያ የሚሰጡት ለመዋቅር (ቅርጽ) መሆኑን Zamel (1985) ያስረዳሉ:: ይሁን እንጂ እንደ ምሁሩ ገለጻ መምህራን በቅርጽ ላይ ማተኮር ያለባቸው በተማሪዎቹ የመጀመሪያ ረቂቆች ላይ ሳይሆን በመጨረሻዎቹ ጽሁፋዊ ስራዎች ላይ ቢሆን ተመራጭነት እንዳለው ጠቁመዋል:: አክለውም ግብረመልስ የሚሰጥበት ዓላማ ታውቆ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም ይገልጻሉ፡፡ ይዘት ተኮር ግብረመልስ ትኩረቱ ጸሀፊው ማስተላለፍ የፈለገውን ነጥብ ትክክለኛ መሆኑንና አለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡ ስለዚህ ይዘት ተኮር ግብረመልስ ሊቀርብ የሚችለው፡- ሂሳዊ አስተያየት በመስጠት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ማጠቃለያ በማቅረብ፣ ስህተት የሆነውን አቃንተን በማሳየት፣ በማድነቅ፣ ስህተቱን በማሳየት፣ በትክክል ለሰሩት በማበረታታት ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህን ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት የታቀደው ጥናት የመምህር ግብረመልስ የትኩረት አቅጣጫዎች ምን እንደሚመስል ይመርምራል፡፡

### 2.1.5 የግብረመልስ አቀራረብ ስልት (ዘዴ)

መምህራን የተማሪዎች የቋንቋና የጽሁፍ ክሂላቸው እንዲዳብር ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡ የሚሰጠውም ግብረመልስ የተለያዩ መሆን አለባቸው፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎችን ችሎታ ለመመዘን የተለያዩ የእርማት ስልቶች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ የመጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ስልቱ እንደ መምህራን ቢለያይም ዋናው አላማውም  የተማሪውን የጽሁፍ ክሂል

ማዳበር ነው በማለት Laland (1982) እና (Ur 1996) የጽሁፋዊ መጋቤ ምላሽ ስልቶችን እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡

- ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት፡- የዚህ አስተራረም ስልት ስህተትን ለቅሞ ማሳየት ነው፡፡ ለተማሪው ስህተቱን እንዲያርም የሚረዳው መሆኑን Laland (1982) ይገልጻሉ፡፡
- ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት፡- የዚህ የአስተራረም ስልት ለጽሁፍ ስራው እንቅፋት የሚሆኑትን ዋና ዋና ስህተቶች እና በአብዛኛው የሚፈጽሙትን ስህተቶች መርጦ የማረም ስልት ነው በማለት Laland (1982) ይገልጻሉ፡፡
- ጠቋሚ የአስተራረም ስልት፡- በተማሪው የጽሁፍ ስራ ላይ ስህተትን ጠቋሚ የሆኑ የተለያዩ ምልክቶችን በመጻፍ መጠቆም ነው፡፡ በተማሪዎች የድርሰት ላይ ምክቶችን በመጠቆም ስህተቶችን ለማመልከት እና ለማረም ስህተት የሆነው ላይ ጥያቄ በመጠየቅ፣ በማስመር፣ ስህተቱ ምን እንደሆነ የጽሁፍ ማብራሪያ በመስጠት፣ በማክበብ እና በመሳሰሉት ምልክቶች ለተማሪዎች ስህተታቸውን በማሳየት እንዲያርሙት ማድረግ ማለት ነው፡፡ በዚህም የአስተራረም ስልት ተማሪዎች ከስህተታቸው በመረዳት አስተካክለው እንዲጽፉ ይረዳቸዋል በማለት Byrne (1988) ይገልጻሉ፡፡ በመጨረሻም የአጻጻፍ ስልት ግብረመልስ ትኩረቱ የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም፣ በጽሁፍ ስራቸው ብቃት፣ የጽሁፍ ወጥነትና አዲስነት ናቸው፡፡ በተጨማሪም የግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶች በተማሪዎች እንዲዳብር የተፈለገው ክህሎትና እንዲገነዘቡት የተፈለገው እውቀት ፍሬያማ መሆን አለመሆን መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው ለማሳወቅ በአገልግሎት ላይ የሚያውሏቸውን የእርማት መስጫ ስልቶችን የሚያካትት መሆኑን ፋንታዬ (1988:8) ይገልጻሉ፡፡

መምህራን ተማሪዎቻቸው በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ የቋንቋ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ የማለማመዱና ለልምምዱም ተገቢ የሆነ ግብረመልስ የመስጠት ሙያዊ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ቢሆንም ግብረመልስ የሚሰጡባቸው ስልቶች ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ የልዩነታቸው ዋና መንስኤም መምህራን የተማሪውን ችሎታ ለመገመት ያስችላል የሚሉትን የእርማት ስልት በተመቻቸው መንገድ ስለሚጠቀሙ ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳል፡፡ እንደ (Byrne 1988, Laland 1982 እና Ur 1996) አስተያየት ይህ የሃሳብ ትኩረት መምህራን ይሆናል የሚሉት የእርማት አሰጣጥ ስልት በተግባር ላይ ማዋል እንደሚችሉ መብት እንዳላቸውም ያሳያል፡፡ ሆኖም የግብረመልስ አሰጣጥ ስልት እንደ የምሁራኑ አገላለጽና አተያይ ይለያይ እንጂ መምህራን ግብረመልስን

የሚጠቀሙት ዋና አላማቸው የተማሪዎችን የጽሁፍ ክሂል ለማዳበር መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡

በመምህራን ለተማሪዎች የሚቀርቡት ግብረመልሶች በየትኛው ዘዴ ላይ መሆን እንዳለባቸው የተለያዩ አጥኚዎች ገልጸዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ Asri (1996) እና Raimes (1983) እንዳሉት ቀጥተኛ እርማት፣ ኢቀጥተኛ እርማት፣ አዎንታዊና አሉታዊ ግብረመልስ፣ ጥያቄና አስተያየቶች ናቸው፡፡

ቀጥተኛ እርማት፡- የተማሪዎችን ድክመቶች በመጠቆም ትክክለኛውን የቋንቋ አጠቃቀም ወይም ስርአት የማቅረቢያ መንገድ ነው፡፡

ኢቀጥተኛ እርማት፡- ወኪል በሆኑ ምልክቶችና መለያዎች ስህተትን ማመልከቻ ዘዴ ነው፡፡

አዎንታዊና አሉታዊ ግብረመልሶች፡- አዎንታዊ ግብረመልስ ስህተትን በቀጥታ የማይገልጽ ሲሆን አሉታዊ ግብረመልስ የተማሪውን የመጻፍ ተነሳሽነት የሚቀንስና ስነልቦናውን የሚጎዳ ነው፡፡

ጥያቄዎችና አስተያየቶች፡- መምህራን የተማሪዎችን ስህተቶች በመጠቆምና ጥያቄያዊ አስተያየቶችን በማቅረብ ተማሪዎቹ ለጥያቄዎቹ መልስ በመስጠት ሂደት በራሳቸው ድክመቶች የሚያስተካክሉትን መንገድ እንዲቀይሱ የሚረዳ ዘዴ ነው በማለት አብራርተውታል፡፡ ስለዚህ መምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልሳቸውን ሲሰጡ ተማሪን ሊረዳ በሚችል መልኩ መስጠት ይገባቸዋል፡፡

### 2.1.6 ግብረመልስ የሚሰጥበት ጊዜ

መምህራን ለተማሪዎች ግብረመልስ ሲሰጡ በጊዜው መስጠት እንዳለባቸው Brookhart (2008) ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ከዚህ እንደሚከተለው አብራርተውታል፡፡ ለተማሪዎች ግብረመልስ መስጠት የሰሩትን ስህተት እንዲያርሙ ይረዳቸዋል፡፡ ስለዚህ የሚሰጣቸው ግብረመልስ ሳይቆይ ወይም የሚማሩት ምዕራፍ ሳይጠናቀቅ ቢሰጥ ትምህርቱን ሳይረሱት የሰሩትን ስህተት ወዲያው ሊያርሙት ይችላሉ በማለት ያብራራሉ፡፡ የሚማሩትን የምዕራፉን ዋና ዓላማ ለማሳካትም ሆነ ራሳቸውን ለመመዘን በጊዜው ግብረመልስ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል፡፡ ጥሩ ግብረመልስ የሚባለው ተማሪዎች የተሰጣቸውን የጽሁፈት ስራ ሰርተው ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ውጤታቸውን ቢያዩት ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ከአንድ እና ከሁለት ሳምንታት በኋላ እንዲሁም ምዕራፉ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚሰጥ ግብረመልስ ጥሩ ግብረመልስ ስለማይባልና ተማሪዎች የሰሩትን ስህተት ሳያርሙ ወደ ሌላ ስራ

ስለሚገቡ ሌላ ስህተት እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡ በአጠቃላይ ከጊዜ አንጻር ግብረመልስ ሲሰጥ ተማሪዎች በጻፉት ጽህፈት ላይ ወዲያውኑ ወይም የትምህርቱ ምዕራፍ ከማለቁ በፊት መሰጠት አለበት፡፡

## 2.1.7 የጽሁፋዊ ግብረመልስ ባህሪያት

መምህራን በተማሪዎች የጽሁፍ ሥራ ላይ የሚሰጡት እርማት የተለያየ ነው፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች ጥሩ ጽሁፍ ከጻፉ ጥሩ ምላሽ ሲሰጣቸው ነገር ግን የጽሁፍ ስራቸው ጥሩ ካልሆነ የሚሰጣቸው እርማት ጥሩ ምላሽ አይሆንም፡፡ ስለዚህ ግብረመልሱ የሁለት ነገሮችን ባህሪ የያዘ ነው፡፡ እነርሱም አዎንታዊ ምላሽ እና አሉታዊ ምላሽ ናቸው፡፡ እነዚህን የግብረመልስ አይነቶች አዎንታዊ እና አሉታዊ የግብረመልስ ባህሪያት ብለን በሁለት እንከፍላቸዋለን በማለት Leki (1990) ይገልጻሉ፡፡ አዎንታዊ ባህሪያት የተማሪዎች ስራ ጥሩ ስለመሆኑ የሚጠቆምበት በመሆኑ የተማሪዎችን ስራ ስለሚያበረታታ መምህራን መጠቀም አለባቸው፡፡ ነገር ግን ለተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ለማዳበር ስህተታቸውንም የሚጠቁም ግብረመልስ መስጠት እንደሚገባ Byrne (1988) ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ጥሩ ስራ ያልሰሩ ተማሪዎችን በአሉታዊ እርማት ስራቸውን ስለሚጠቁም ተማሪዎች ሳይፈሩ እና ሳይሸማቀቁ የተሳሳተውን የጽሁፍ ስራ ለማስተካከል ይረዳቸዋል ብለዋል፡፡

## 2.2 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

ጽሁፋዊ ግብረመልስ ላይ ያተኮሩ በርካታ የጥናት ስራዎች ቢኖሩም ስራዎቻቸው የሚያተኩሩት በተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃ ላይ ማለትም በተማሪዎች የቀረበው ጽሁፍ ጥሩ የማግባባት ብቃት እንዲኖረው፤ የሀሳብ ፍሰቱ በጥሩ ሁኔታ እንዲደራጅ፤ የሰዋሰው ቅንብሩ እንዲስተካከል፤ የሆሄያት አጣጣል እና ሥርዓተ ነጥቦች በተገቢው ቦታቸው እንዲሰፍሩ በማስቻል ላይ ያተኮሩ ናቸው፤ ነገር ግን የመምህሩ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከተማሪዎች ከጽሁፍ ክህሎት ጋር ተመጋጋቢ እንደሆነ እና ሊያመጣ የሚችለውን ትልቅ የቋንቋ ክህሎት መዳበር እና መስተካከል ሚና አላጠቃለሉም፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ካላቸው ውስጥ የመጀመሪያው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ እታለማሁ (2006) የጥናቱ ርዕስ "የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ፍተሻ በየካቲት 23 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት" ነው፡፡ የጥናቱም ዓላማ በየካቲት 23 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡትን ጽሁፋዊ ግብረመልስ መፈተሽ የሚል ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያው ሰነድ ፍተሻ ፣ የጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ የጥናቱም ትኩረት መምህራን በተማሪዎቻቸው ጽሁፍ

ውስጥ የሚታዩትን ስህተቶች በምን ላይ እንደሚያተኩሩ፣ ምን አይነት የግብረመልስ ስልት እንደሚጠቀሙ፣ቦታ፣ባህሪ እና አቀራረብ ምን እንደሚመስል ነው፡፡ የጥናቱም ማጠቃለያ መምህራን ገምጋሚ ግብረመልስ በከፍተኛ መጠን እንደሚያዘወትሩ ለተማሪዎቻቸውም የጽሁፍ መልመጃዎች ላይ ማርክ ሰጥተው እንደሚመልሱላቸው አረጋግጠዋል፡፡

የዚህ ጥናት ከቀደመው ጥናት ጋር ያለው ዝምድና መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት መምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ አተገባበርን ከተማሪው የጽሁፍ ስራ ጋር እየመረመረ ያለውን ሂደት፣ ክፍተት እና መሻሻል ከትምህርት አሰጣጥ እና የተማሪዎችን ምላሽ መሰረት በማድረግ ሲያተኩር ያለፈው ጥናት ግን የመምህራንን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አይነቶችን፣ ከሚሰጥበት ቦታ፣ ወቅት፣ ትኩረት፣ አቅጣጫ እና ባህሪ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥናት ከሚካሄድበት አካባቢ እና ከትምህርት ቤት አንጻርም ይለያል፡፡

እንዳለ (1992) "በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ሚና" በሚል ርዕስ የተሰራ ጥናት ነው ፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በተማሪዎች የድርሰት ስራ ላይ መምህራን የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ የሚያመጣውን ለውጥ መመርመር ነው፡፡ ጥናቱን ያካሄዱት በአዲስ አበባ ከሚገኙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎችን ከአንዱ ትምህርት ቤት መርጠው ነው፡፡ ጥናቱን የሰሩት በአይነታዊ የጥናት ዘዴ ሆኖ መረጃ መሰብሰቢያው የድርሰት ፈተና፣ ምልከታና መጠይቆች ናቸው፡፡ የጥናቱ መደምደሚያ በድርሰት ትምህርት ውስጥ በቡድንና በግል ከሚከናወኑ ምላሾች ይልቅ በመምህራን የሚሰጥ ግብረመልስ የተሻለ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ በመጨረሻም ጽሁፋዊ ግብረመልስ በየጊዜው በድርሰት መስክ በሚካሄዱ ምርምሮች መታነጽ አለበት በማለት አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

የአሁኑ ጥናት ከቀደመው ጥናት ጋር ያለው ተዛምዶ መምህራን በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ውስጥ የሚሰጡትን ግብረመልስ ፍተሻ ላይ ማተኮራቸው ነው፡፡ ነገር ግን የአሁኑ ጥናት ከቀደመው ጥናት ጋር ያለውን ልዩነት ስንመለከት የአሁኑ ጥናት የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ ያለውን ጠቀሜታ ከሰነድ ፍተሻና ከመጠይቆች ጋር መረጃ በመሰብሰብ የሚጠና ሲሆን የቀደመው ጥናት ግን የተማሪዎች ጽሁፋዊ ክሂል መሻሻሉን በሙከራ በመፈተሽ ምልከታንና መጠይቆችን እንደ መረጃ መሰብሰቢያ ተጠቅሞ ጽሁፋቸው የአተገባበርመሻሻሉን ይመረምራል፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥናት ከቀደመው ጥናት ጋር በቦታና በክፍል ደረጃ ልዩነት አለው፡፡

ዳዊት (2008) "የመምህር-ተማሪ ምክክርና የመምህር ጽሁፋዊ ግብረመልስ በተማሪዎች ጽሁፋዊ ክሂል ላይ ያላቸው ተጽእኖ" በሚል ርዕስ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከመምህር-ተማሪ ምክክር ጋር ያለውን ተጽዕኖ መመርመር በሚል ዓላማ በሙከራ ላይ ተመስርቶ የተሰራ ጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ከመሰረታዊ የቋንቋ ክሂል ትምህርቶች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) መካከል በመጻፍ ክሂል ትምህርት ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ቅድመ እና ድህረ-ሙከራ ፈተናዎች፣ የጽህፈት መልመጃዎች እና ቃለ-መጠይቆች ናቸው፡፡ በጥናቱም የመምህር-ተማሪ ምክክራዊ ግብረመልስም ሆነ የመምህር ጽሁፋዊ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጽሀፍ ክሂል እድገት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳላቸው አጥኚው ደምድሟል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተዛምዶ ሁለቱም መምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ በሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ላይ ስለሚያተኩሩ ነው፡፡ የዳዊት ጥናት በሙከራ ፈተና ፣ በጽህፈት መልመጃዎችና ቃለ መጠይቆች ላይ ያተኮረ ሙከራዊ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ሙከራዊ ጥናት ሳይሆን በሰነድ ፍተሻ ላይ ትኩረቱን አድርጎ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ እና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ መረጃ በመሰብሰብ የሚሰራ ጥናት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የመጻፍ ክሂል ሲታሰብ ሊነሱ የሚችሉ በርካታ ዝርዝር የትኩረት አቅጣጫዎች መኖራቸው ጥናቱ የተወሰኑ ገደቦች እንዲኖሩት አድርጎታል፡፡ ከእነዚህም መካከል ለምሳሌ የተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ለውጥ ማሳየቱን ወይም አለማሳየቱን የሚመለከተው ከተማሪዎቹ ጽሁፋዊ ስራዎች ይዘት፣ የሐሳብ አደረጃጀት፣ ቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የቋንቋ አጠቃቀም እንዲሁም ስርአተ ጽህፈት አንጻር መሆኑ ነው፡፡ የቀደሙት ጥናቶ የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች የሚኖራቸውን ተጽዕኖ በንጽጽር ትኩረት ሰጥቶ አልተመለከቱትም፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ጽህፈትን ከመረዳት አልፎ በምን ያህል ለውጥ የሐሳብ አደረጃጀት፣ ቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ ስርአተ ጽህፈት ማዳበራቸውን፣ ጥናቱ ከሚከናወንበት አካባቢ፣ ከትምህርት ቤትና ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አኳያ ልዩነት ይታይበታል::

እርግጥ ነው ከላይ የተጠቀሱት አጥኚዎች ጥናታቸውን እንዲያጠኑ ያነሳሳቸው ምክንያቶች ማለትም ተማሪዎች አንቀጽ፣ ደብዳቤ፣ አስተዋጽኦ፣ ድርሰት፣ አሳጥሮ እንዲጽፉ ወዘተ. በሚጠየቁበት ጊዜ የሚጽፉት ጽሁፍ የሃሳብ ተያያዥነት ጉድለት፣ የሰዋስው ስህተት፣ መደበኛ ቋንቋ ያለመጠቀም፣ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ ያለመጠቀም እና የመሳሰሉት ስህተቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህ የክሂል ክፍተቶች እንዲቀረፉ የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ ምን እንደሚመስልና የአተገባበሩ ሁኔታ ከተማሪዎች ድህረ ጽሁፋዊ

ግብረመልስ ወይንም እስተያየት በመስጠት ማስተካከል ለተማሪዎች ጽሁፍ ክሂል መዳበር አስተዋጽኦ በመኖሩ ለማጥናት የታቀደ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ የአተገባበሩ ያለውን ጠቀሜታ ይፈትሻል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ስልት

ይህ ጥናት አይነታዊና መጠናዊ የአጠናን ዘዴን በመጠቀም ለናሙና ከተመረጡት የጥናቱ ተሳታፊዎች በዓላማው መሰረት የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውሰጥ በስፋት የሰነድ ፍተሻ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ከመምህራን ጋር የሚካሄድ ቃለ መጠይቅና ከተማሪዎች የሚወሰድ የጽሁፍ መጠይቅ በመጠቀም መረጃ በመስብሰብ የተገኙትን መረጃዎች በመተንተንና በመተርጎም የጥናቱን ውጤት በማሳየት የማጠቃለያና መፍትሄ ሀሳብ ተጠቁሟል፡፡ ይህም ሲባል ቅይጣዊ የጥናት ስልት ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ምክንቱም ከሰነዶች የተወሰዱት መረጃዎችና ቃለ መጠይቆች በአይነታዊ የመተንተኛ ስልት በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቆች ተሰብስበውና ተደራጅተው በመቶኛ በማስቀመጥ በመጠናዊ መተንተኛ ስልት ተተንትነዋል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራርጥ

ይህ ጥናት የተሰራው በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራንና የአማርኛ ቋንቋ ላይ ብቻ አተኩሯል፡፡ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡትም ዓመቱን ሙሉ በትምህርት ቤት ስለሚቆዩ በቂ መረጃ አገኝበታለሁ ብላ አጥኚዋ በማመኗ ነው፡፡

### 3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በሌሞ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ 7 የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና አመራጭ ዘዴ ተመርጧል፡፡ በትምህርት ቤቱ ያሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ ተጠኚዎች ናችው፡፡ ትምህርት ቤቱ የተመረጠውም በአጥኚዋ አቅራቢያ ስለሚገኝና መረጃ ለመሰብሰብ ቅርብ ስለሆነ ለጥናቱ መሳካት ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በአጠቃላይ አጥኚዋ ችግሩን በቅርበት በየዕለቱ እየተመለከተች ስለሆነና ትምህርት ቤቱን በአመቺ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በመምረጥ ጥናት ባደርግበት ያለውን ችግር እቀርፋለሁ ብላ በመነሳቷ ጥናቱን ለማካሄድም ሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ያለውን አመቺነት በመረዳት በታቀደው መሰረት እንዲሳካና ቀልጣፋ ያደርግልኛል ብላ በማሰቧ ጥናቱ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተካሂዷል፡፡

### 3.2.2 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

የመምህራን ናሙና አመራረጥን በተመለከተ ከላይ እንደተጠቀሰው በጥናቱ ተተኳሪ በሆነው ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሁሉም ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸውና ለብዙ ጊዜ በማስተማር ስራ ላይ የቆዩ መምህራን ናቸው፡፡ በትምህርት ቤቱ ውስጥ አራት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይገኛሉ፡፡ ወንድ 2 እና ሴት 2 በድምሩ 4 መምህራን ናቸው፡፡ ሁሉም በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ለጥናቱ አካላይ እንዲሆኑና መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም በትምህርት ቤቱ ውስጥ የአማርኛን ቋንቋ የሚያስተምሩት የ9ኛ ክፍል መምህራን በቁጥር ጥቂት ስለሆኑና በናሙናነት በተመረጡት ክፍሎች ውስጥ ስለሚገኙ ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡ እያንዳንዳቸውም ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ምድቦችን ያስተምራሉ፡፡

### 3.2.3. የተማሪዎች እና የመማሪያ ክፍሎች ናሙና አመራረጥ ዘዴ

ለጥናት ተተኳሪ በሆነው ትምህርት ቤት በደረጃቸው የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ አጥኚዋ ችግሩን በቅርበት ስለምትመለከትና በዚህ ችግር ላይ ጥናት ብሰራበት ችግሩን እቀርፋለሁ ብላ በማሰቧ ነው፡፡ በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የትምህርት ዓመቱ እስከሚገባደድ በትምህርት ቤቱ ስለሚገኙ የሚፈለገውን በቂ መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል የሚል እሳቤ ስላለ ነው፡፡ በ2015 ዓ.ም በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 705 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውሰጥ ወንድ 339 ሴት 366 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ ከነዚህ ተማሪዎች ሁሉ መረጃ መቀበል አዳጋች ነው፡፡ ካሉት ከአራቱ መምህራን ውስጥ ሁለቱ መምህራን ሁለት ሁለት ክፍሎች ውስጥ ሲገቡ የቀሩት ሁለቱ መምህራን ሶስት ሶስት የ9ኛ ክፍሎችን ያስተምራሉ፡፡ ሶስት ሶስት ክፍል ለሚገቡት ለሁለቱ መምህራን ላሉት ሶስት ሶስት ክፍሎች እጣ በማውጣት ሁለት ሁለት ክፍሎች የጥናቱ ተሳታፊ ተደርገዋል፥ ስለዚህ ከእያንዳንዱ መምህር ሁለት ሁለት ክፍሎችን በመውሰድ በአጠቃላይ ከ294 ተማሪዎች ማለትም ከወንድ 141 ከሴት 153 መረጃዎችን ለመውሰድ ቢታቀድም 77 ወንድ ተማሪዎችና 73 ሴት ተማሪዎች በአጠቃላይ 150 ተማሪዎች በጊዜው ባለመገኘትና የጽሁፍ መጠይቁን በአግባቡ ባለመሙላታቸው ከ64 ወንዶችና ከ80 ሴት ተማሪዎች በድምሩ ከ144 ተማሪዎች መረጃው ተወስዷል፡፡ ይህም ማለት ከእያንዳንዱ ክፍል ከወንድ 8 እና ከሴት ተማሪዎች 10 በአጠቃላይ ከስምንት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በተራ ዕጣ ንሞና ዘዴ ከተመረጡት መካከል መረጃ አቀባይ ተደርገዋል፡፡ ይህም ተግባራዊ የሚደረገው 144 የወንድ ተማሪዎች ብዛትን ላሉት ለ8

ክፍሎች ሲካፈል 18 ወንድ ተማሪዎች በየክፍሉ ስለሚደርስ በእያንዳንዱ ክፍል ካሉት ወንዶች ውስጥ ቁጥሩ 18 እስከሚደርስ ድረስ በተራ ዕጣ ናሙና በመለየት ወንዶች ተሳታፊ ተደረገዋል፡፡ የሴት ተማሪዎችን ብዛት ማለትም 80ን ለ8 ክፍሎች ሲካፈል 10 ሴት ተማሪዎች በየክፍሉ ስለሚደርስ በእያንዳንዱ ክፍል ካሉት ሴቶች ውስጥ ቁጥሩ 10 እስከሚደርስ ድረስ በተራ ዕጣ ናሙና በማውጣትና በመለየት የሴቶች ተሳታፊ ተመርጠዋል፡፡

### 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

የጥናቱ ዋና አላማ ከግብ እንዲደርስ የሚሰበሰቡት መረጃዎች ግብረመልስ ተሰጥቶባቸው ለተማሪዎች የተመለሱ የተለያዩ ጽሁፎች ማለትም የተለያዩ የታሪክ ይዘት ያላቸው ጽሁፎች ፣ አጫጭር ድርሰቶችና ዓረፍተ ነገሮች ሲሆኑ በተጨማሪም በመምህራን የተመለሱ ቃለ መጠይቆችና በተማሪዎች የተሞሉ የጽሁፍ መጠይቆች ናቸው፡፡

#### 3.3.1 ሰነድ ፍተሻ

ለዚህ ጥናት በዋናነት ያገለግላል ተብሎ አሁን የተሰራበት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ ተሰጥቶባቸው ለተማሪዎች የተመለሱ የተማሪ ጽሁፎች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ጽሁፎቹ የተሰበሰቡት ለሰነዶች ባለቤት ከሆኑት ተማሪዎችና በናሙናነት ከተመረጡት መምህራን ፍቃደኝነታቸውን በመጠየቅ ነው፡፡ ሰነዶቹም የተማሪዎችን ፍቃደኝነት በመጠየቅ ኮፒ ተደርጎ ተመልሶላቸዋል፡፡ ከላይ በናሙናነት የተመረጡትን ወንድ 64 ተማሪዎችና ሴት 80 ተማሪዎች በድምሩ 144 ተማሪዎች ተረትና ምሳሌዎች፣ አጫጭር ድረሰቶችና የተጻፉ ዓረፍተ ነገሮች ላይ በተጻፉ መምህራን የሰጧቸውን ግብረመልሶች በጥናቱ ተፈትሸዋል፡፡ በመምህራን ግብረመልስ የተሰጠበትን ከላይ የተዘረዘሩትን ከእያንዳንዱ መምህር ክፍል ሶስት ሶስት መረጃዎችን በመውሰድ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

#### 3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቅ እንደ መረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠው በዋና መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሳይሆን የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጣቸው ስኬታማ መርህን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥና በምላሹ የተማሪዎች እይታ ምን እንደሚመስል የተሻለ መረጃ ይሰጣል በሚል እሳቤ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ ለናሙናነት በተመረጡት በወንድ 64 ተማሪዎችና በሴት 80 ተማሪዎች በድምሩ 144 ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቁ ተሞልቷል፡፡

### 3.3.3 ቃለ መጠይቅ

ሌላው መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል የተባለው ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ቃለ መጠይቁ ለመምህራን ከመቅረቡ በፊት በደንብ ለመገምገም ተገቢው ጥረት ተደርጓል፡፡ ግብረመልስ ተሰጥቶባቸው የተመለሱ ተማሪዎች የጽሁፍ ወረቀቶች ምን እንደሚመስሉ ከተፈተሸ በኋላ የተገኘው ውጤት በይበልጥ ለማጠናከር በተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅና በመምህራን የቃለመጠይቅ ሰፊ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ቃለ መጠይቆቹ የተዘጋጁት በናሙናነት ለተመረጡት ወንድ 2 እና ሴት 2 በድምሩ 4 መምህራን ነው፡፡ የመረጃ አሰባሰቡንም ሂደት የተሻለ ለማድረግ መረጃዎቹ እንዳይባክኑ ይረዳ ዘንድ ከመምህራን ጋር የተደረገው ቃለ ምልልስም በመቅረጸ ድምጽ ከመቀዳቱም ሌላ ቃለ ምልልሱም ወደ ጽሁፍ ተቀይሮ በአባሪነት ተያይዟል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ጥናት ከመምህራን ጋር የተደረገው ቃለ ምልልስ ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ ተግባራዊ በማድረግ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ ብዙ መረጃዎችን ለማግኘት ረድቷል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ ለመተንተን እያንዳንዳቸው መምህራን በእያንዳንዱ የተማሪ ጽሁፍ ላይ የሰጡትን የግብረመልስ አይነቶች፣ የግብረመልሱ የትኩረት አቅጣጫ፣ ስልት እና ስህተትን ከመጠቆም አንጻር የተሰጠውን የግብረመልስ በቁጥር ተመዝግቦ ከግብረመልስ አንጻር፣ ከግብረመልስ የትኩረት አቅጣጫ አንጻር፣ ስህተትን ከመጠቆም አንጻርና ስልት በአይነታዊ የመረጃ ትንተና ስልት ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡

በመቀጠል ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በመሰብሰብና በመቶኛ በማስቀመጥ ተዛማጅነት ካላቸው ጥያቄዎችና ከስነድ ፍተሻ ከተገኘው መረጃ ጋር በማቀናጀት ተተንትኗል፡፡ በመጨረሻም ከመምህራን ጋር የተደረገውም ቃለ ምልልስ የሰጡት መልስ ተመዝግቦ ማብራሪያና ትንተና ተሰጥቶበታል፡፡ ከክፍት ጥያቄና ከቃለ መጠይቁ የተገኙ መረጃዎች አይነታዊ የአተናተን ዘዴን በመከተል ተተንትነዋል፡፡ ከሰነድ ፍተሻውና ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኙት መረጃዎች በመጠናዊ የአተናተን ስልት ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ

በምዕራፍ አንድ ስር እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ተማሪዎች በጻፏቸው ጽሁፎች ላይ መምህራን የሰጧቸውን ግብረመልሶችን መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ግብረመልስ የተሰጠባቸው የተማሪ ጽሑፎች ፣ ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅና ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሆነው አገልግለዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ ከላይ ጽሁፋቸው ለተሰበሰበው ተማሪዎች በመበተን መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በዚህ መሰረት የተገኘው መረጃም እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## 4.1 ጠቅላላ መረጃ

በዚህ ጥናት ውስጥ እንደዋና መረጃ ሆነው ያገለገሉት መምህራን በተማሪዎች ጽሁፎች ላይ ለተከታታይ 4 ወራት የሰጧቸው ግብረመልሶች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ለጥናቱ ናሙናነት የተመረጡ አራቱ መምህራን ተከታታይ በሆኑ ሶስት የጽሁፍ ይዘት ባላቸው የተማሪ ጽሁፎች ላይ ግብረመልስ የሰጡባቸው ወረቀቶች ለትንተና ቀርበዋል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ግብረመልስ የተሰጠባቸው የተማሪዎች የጽሁፎች(ሰነዶች)፣ የመማሪያ ክፍሎች ብዛት፣ የመምህራን ብዛትና የትምህርት ደረጃ ተጠቃለው በሚቀጥሉት ሰንጠረዦች ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ አንድ፡- ለናሙና የተመረጡ መምህራን፣ ተማሪዎችና የመማሪያ ክፍሎች ብዛት**

### 1.1 የመምህራን ብዛት

| | ወንድ | ሴት | ድምር | የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| | መ.1 | | 1 | ዲግሪ |
| | መ.2 | | 1 | ዲግሪ |
| | | መ.3 | 1 | ዲግሪ |
| | | መ.4 | 1 | ዲግሪ |
| ድምር | 2 | 2 | 4 | |

### 1.2 ጠቅላላ የተማሪዎች ብዛት

| የተማሪዎች ብዛት | | | ለናሙና የተወሰዱ የተማሪዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 339 | 366 | 705 | 64 | 80 | 144 |

### 1.3 የመማሪያ ክፍሎች ብዛት

| የ9ኛ መማሪያ ክፍል ጠቅላላ ብዛት | ለጥናት ናሙና የተወሰደ የክፍል ብዛት | ከእያንዳንዱ ክፍል የተወሰደ የተማሪዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 10 | 8 | 8 | 10 | 18 |

ሰንጠረዥ አንድ የሚያሳየው ለጥናቱ መረጃ የሰጡ መምህራን፣ ተማሪዎች እና የመማሪያ ክፍሎች ብዛትን ነው፡፡ በ1.1 ላይ በሴሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጠቅላላ የ9ኛ ክፍል የመምህራንን ስብጥር ስንመለከት፣ 2 ሴት እና 2 ወንድ መምህራን ተመርጠዋል፡፡ የትምህርት ደረጃቸውም ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ ባለቤት ናቸው፡፡ በ1.2 ላይ ተማሪዎች ብዛት 705 ሲሆን፣ 339 ወንድና 366ቱ ሴቶች ናቸው፡፡ ለጥናቱ እንደ መረጃ ሰጪነት የሚወሰዱት የጥናቱ አካላይ ተማሪዎች ብዙ ስለሆኑ ሁሉንም በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ አይቻልም፣ ከጥናቱ አካላይ ውስጥ እንደ ናሙና የተወሰኑ አባላትን መውሰድ ይቻላል በማለት ያለው (2017) ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ የጥናቱ አካላይ ከሆኑት ውስጥ በቂ መረጃ ይሰጣሉ የተባሉት ተመርጠዋል፡፡ በ3.2.3 ላይ እንደተጠቀሰው በአጠቃላይ ከ294 ተማሪዎች ማለትም ከወንድ 141 ከሴት 153 መረጃዎችን ለመውሰድ ቢታቀድም 77 ወንድ ተማሪዎችና 73 ሴት ተማሪዎች በአጠቃላይ 150 ተማሪዎች በጊዜው ባለመገኘትና በአግባቡ ባለመሙላታቸው ከ64 ወንዶችና ከ80 ሴት ተማሪዎች በድምሩ ከ144 ተማሪዎች መረጃው ተወስዷል፡፡ በ1.3 ላይ የመማሪያ ክፍላቸው ብዛት 10 ሲሆን፣ ለናሙና 8 ክፍሎች ሁሉንም መምህራን ለማካለል በጠቅላይ የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ለናሙና ከተመረጡት 8 ክፍሎች ከእያንዳንዳቸው 18 ተማሪዎች ሲመረጡ ፣ በጾታ ደረጃ

ከእያንዳንዳቸው የመማሪያ ክፍሎች 8 ወንድ እና 10 ሴት ተማሪዎች በእድል ሰጭ ናሙና ተመርጠዋል፡፡

**ሰንጠረዥ ሁለት፡- ግብረመልስ የተሰጠባቸው ሰነዶች ብዛት**

ከታች ያለው ሰንጠረዥ ሁለት የሚያሳየው ለጥናቱ መረጃነት የተሰበሰቡትን ግብረመልስ ተሰጥቶባቸው ለተማሪዎች የተመለሱላቸውን የወረቀት (በደብተር መልክ የተወሰደ ሰነድ) ብዛትን ነው፡፡ የጽሁፍ ወረቀቶች መጠን በትምህርት ገበታቸው ላይ የነበሩ ተማሪዎችን ያጠቃለለ ነው፡፡

| **መምህር** | **የወረቀት (የሰነድብዛት)** | | | **ጠቅላላ የሰነድ ብዛት** |
|---|---|---|---|---|
| | ጽሁፍ 1 | ጽሁፍ 2 | ጽሁፍ 3 | |
| መ.1 | 36 | 36 | 36 | 108 |
| መ.2 | 36 | 36 | 36 | 108 |
| መ.3 | 36 | 36 | 36 | 108 |
| መ.4 | 36 | 36 | 36 | 108 |
| **ድምር** | **144** | **144** | **144** | **432** |

ተማሪዎች የጽሁፍ ልምምድ ያደረጉባቸው ወረቀቶች (የደብተር ላይ የጽሁፍ መልመጃ) ብዛት 432 ናቸው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎቹ የጽሁፍ ልምምድ ያደረጉባቸውን ጽሁፎች መሰረት አድርገው መምህራን የሰጧቸውን ግብረመልሶች በሚከተለው ክፍል በትንተና መልክ ቀርበዋል፡፡

የመምህራን እና የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ በተመለከተ ከአራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቃለ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰበ መረጃ እና በቁጥር 144 በሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃ በትንተናው ቀርበዋል፡፡ በአጠቃላይ የመምህራን ግብረመልስ ከጽሁፋዊ ግብረመልስ አይነቶች ፣ስልቶች ባህሪያት፣ የትኩረት አቅጣጫ እና ከሰነዶች የተገኘውን መረጃ በዋናነት መሰረት በማድረግ በደጋፊነት

ከገባው ከጽሁፍ መጠይቆች እና ከቃለ መጠይቆች የተገኘውን መረጃ በማያያዝ ትንታኔው በተቀናጀ መልክ ቀርቧል፡፡ ለጥናቱ ከተመረጡት ተማሪዎች ደብተር ላይ መምህራን ግብረመልስ የሰጡበትን መረጃ በማገላበጥ ከእያንዳንዱ ተማሪ ላይ ሶስት ሶስት ጽሑፍ በመውሰድ የተገኘ ቁጥር ነው፡፡ የተለያየ ብዛት ያለው መረጃ ቢወሰድ የጥናቱ ውጤት የተለያየ ሊሆን ስለሚችል ተመሳሳይ ብዛት ያለው ጽሑፍ ይወሰዳል በማለት (ያለው 2017) ይገልጻሉ፡፡ ከሁሉም መምህራን እኩል የጽሑፍ ይዘት ቢወሰድ የመልሱን አስተማማኝነት ከፍ እንዲል ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ለዚህ ጥናት በዚሁ መሰረት መረጃው ተወስዷል፡፡

## 4.2 የመምህራን ግብረመልስ ከጽሁፋዊ ግብረመልስ አይነቶች፣ ስልቶች ባህሪያትና ከትኩረት አቅጣጫ የተሰጠ ትንታኔ

### 4.2.1 ከጽሁፋዊ ግብረመልስ አይነቶች አንጻር የመምህራን ምላሽ

በቀደመው በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ላይ በዝርዝር እንደተጠቀሰው ግብረመልስ በቋንቋ ማስተማር ውስጥ የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው እና የግብረመልስ አይነቶችን በተመለከተ Moxely (1989) በአራት ክፍሎች በመመደብ ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡ ከታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን በተለያየ አይነት የግብረመልስ የሰጡትን እርማት ከተማሪዎች ወረቀቶች ላይ ተመዝግቦ ለምን ያህል ጊዜ ደጋግመው እንደተጠቀሙ በቁጥርና በመቶኛ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም የመምህራን የግብረመልስ አይነቶች አተገባበር ምን እንደሚመስል ለማወቅ በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ አማካኝነት መረጃዎች ተሰብስበው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ ለምሳሌ ከታች ሰንጠረዥ ሶስት እንደሚያሳየው ለናሙና ከተወሰዱ ሶስት ጽሁፎች ላይ መ.1 በጽ.1 ላይ እና በጽ.3 የሰጧቸው የግብረመልስ አይነቶችከአስተካካይ ግብረመልስ አይነት በስተቀር ማለትም አመቻች፣ ትዕዛዛዊ እና ገምጋሚ የግብረመልስ አይነቶችን እያሰባጠሩ እርማት እንደሰጡ ቢታይም በእያንዳነዱ መምህር አተገባበር ላይ ግን ልዩነት እንዳለ ታይቷል፡፡

### ሰንጠረዥ ሶስት፡- በተከታታይ ሶስት የተማሪ ወረቀቶች ላይ መምህራን የሰጧቸው የግብረመልስ አይነቶችና ድግግሞሽ

| መምህር | የግብረመልስ አይነቶች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አመቻች | | | | | | አስተካካይ | | | | | | ትዕዛዛዊ | | | | | | ገምጋሚ | | | | | |
| | ጽ1 | | ጽ2 | | ጽ3 | | ጽ1 | | ጽ2 | | ጽ3 | | ጽ1 | | ጽ2 | | ጽ3 | | ጽ1 | | ጽ2 | | ጽ3 | |
| | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % |
| መ1 | 6 | 54.5 | 5 | 45.5 | | | | | | | | | 4 | 26.7 | 5 | 33.3 | 6 | 40 | 5 | 41.7 | 7 | 58.3 | | |
| መ2 | | | 6 | 54.5 | 5 | 45.5 | 5 | 31.3 | 7 | 43.8 | 4 | 25 | | | | | | | 7 | 46.7 | 4 | 26.7 | 4 | 26.7 |
| መ3 | | | 7 | 53.8 | 6 | 46.2 | 5 | 31.3 | 8 | 50 | 3 | 18.8 | | | | | | | 6 | 46.2 | 4 | 30.8 | 3 | 23.07 |
| መ4 | 6 | 42.9 | 8 | 57.1 | | | | | | | | | 5 | 31.3 | 6 | 37.5 | 5 | 31.3 | 5 | 41.7 | 7 | 58.3 | | |

ከላይ ሰንጠረዥ ሶስት እንደሚያሳየው ለትንታኔ ያመች ዘንድ መምህራን በተመረጡት የግብረመልስ አይነቶች ላይ የሰጡትን ምላሽ እንመለከታለን፡፡ በዚህ መሰረት የመ.1 መልስ ስንመለከት ጠቅላላ ከሰጡት 11 አመቻች ግብረመልስ ውስጥ በጽ.1 ላይ 54.5% ፣በጽ.2 45.5%ያህል ተጠቅመዋል፡፡ እንዲሁም ጠቅላላ ከሰጡት 15 ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ውስጥበጽ.1 26.7% ፣ በጽ.2 33.3% እና በጽ.3 ላይ 40% ተጠቅመዋል፡፡ በተጨማሪም መ.1 ጠቅላላ ከሰጡት 12 ገምጋሚ ግብረመልስ ውስጥ 41% በጽ.1 58.3% በጽ.2ላይተጠቅመዋል፡፡ ነገር ግን መ.1 በጽ.2 ላይ የተሻለ ተግባራዊ ያደረጉት የግብረመልስ አይነት ገምጋሚ የግብረመልስ አይነትን ነው፡፡ በአጠቃላይ መ.1 የግብረመልስ አይነቶችን ተጠቅመው ከጠቅላላ ከሰጡትግብረመልስ ውስጥ አመቻች ግብረመልስን፣ ትዕዛዛዊ ግብረመልስን እና ገምጋሚ ግብረመልስን በስብጥር እርማት ሰጥተዋል፡፡

ከመ.2 ለናሙናየተወሰዱ ጽሁፎች ላይ አመቻች ግብረመልስ በጽ.2 54.5 % እና በጽ.3 ላይ 45.5% ሰጥተዋል፡፡ከሰጧቸው በአመቻች የግብረመልስ በጽ.2 ላይ የበለጠ ሰጥተዋል፡፡ መ.2 ጠቅላላ ከሰጡት 16 አስተካካይ ግብረመልስ ውስጥ 31.3% በጽ.1 ላይ ሲጠቀሙ 43.8 % በጽ.2 ላይ እናበጽ.3 ላይ 25% ተጠቅመዋል፡፡ በተጨማሪም መ.2 ጠቅላላ ከሰጡት 16 አስተካካይ ግብረመልስ ውስጥ 43.8 % በጽ.2 ላይ ተጠቅመዋል፡፡ መ.2 ከሰጡት የገምጋሚ የግብረመልስ ውስጥ በጽ.1 46.7% በጽ.2 26.7% ያህል እናበጽ.3 ላይ 26.7 % ሰጥተዋል ፡፡ ከዚህም ውስጥ በጽ.1ላይ 46.7% በማምጣትበላቀ ሁኔታቢሰጡም ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር መ.2 ትዕዛዛዊ ግብረመልስ እንዳላዘወተሩ መረጃው ያሳያል፡፡

መ.3 ጠቅላላ ከሰጡት 13 አመቻች ግብረመልስ ውስጥ በጽ.2 53.8%በጽ3 46.2 % ያህልሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ጠቅላላ ከሰጡት 16 አስተካካይ ግብረመልስውስጥ በጽ.1 31.3% ፣ በጽ.2 50%እናበጽ.3 ላይ 18.8%ያህልሰጥተዋል:: በተጨማሪም መ.3 ጠቅላላ ከሰጡት 13 ገምጋሚ የግብረመልስ ውስጥ በጽ.1ላይ 46.2% ፣ በጽ.2 30.8% እናበጽ.3 ላይ 23.07% ያህል እርማት ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ መ.3 ከሌሎች በላቀ ሁኔታ ገምጋሚ ግብረመልስን እንዳዘወተሩ መረጃው ያሳያል፡፡

መ.4 ጠቅላላ ከሰጡት 14 አመቻች ግብረመልስ ውስጥ በጽ.1 42.9% እና በጽ.2 57.1% ያህል ሲሆን ጠቅላላ ከሰጡት 16 ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ውስጥበጽ.1 31.3 % በጽ.2 37.5% እና በጽ.3 ላይ 31.3% ያህል ተጠቅመዋል፡፡ ነገር ግን በጽ.3 ላይ ትዕዛዛዊ ግብረመልስን በመጠቀም ውጤት ብቻ አስፍረዋል፡፡ በአጠቃላይ መ.4 የግብረመልስ አይነቶችን ተጠቅመው ጠቅላላ ከሰጡትግብረመልስ ውስጥ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ገምጋሚ ግብረመልስን እንዳዘወተሩ መረጃው ያሳያል፡፡ ነገር ግን መ.4 የግብረመልስ አይነቶችን

ተጠቅመው ጠቅላላ ከሰጡትግብረመልስ ውስጥ አመቻች ግብረመልስን ፣ ትዕዛዛዊ ግብረመልስን እና ገምጋሚ ግብረመልስን በስብጥር እንዳዘወተሩ መረጃው ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተገለጹት መምህራን በእያንዳንዱ የተማሪዎች ጽሁፍ ላይ አራቱን የግብረመልስ አይነቶችን በተገለጸው መጠን ደጋግመው ግብረመልስ መስጠታቸው ያመለክታል፡፡

ከሰነድ ግምገማ የተገኘውን ውጤት የመምህራን ቃለ መጠይቅ ጋር ስናነጻጽረው በጥያቄ ቁ1 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ በተማሪዎች ጽሁፋዊ መልመጃዎች ላይ ግብረመልስ ይሰጣሉ? ለሚለው መጠይቅ ሁሉም መምህራን አዎ እሰጣለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ለጥያቄ ቁ2:- ማለትም የተለያዩ የግብረመልስ አይነቶችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ :- አመቻች ግብረመልስ ፣ ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ፣ አስተካካይ ግብረመልስና ገምጋሚ ግብረመልስ፡፡ አልጠቀምም ካሉ ለምን? ለሚለው የሚከተለውን ምላሽ አቅርበዋል፡፡ መ.1 ሲመልሱ ያው ሁሉንም እጠቀማለሁ፡፡ግን ሁሌም ባይሆን አልፎ አልፎ ሁሉንም ማወቅ ስላለባቸው ለመጠቀም እሞክራለሁ፡፡ ነገር ግን በእኔ ትኩረት የማደርገው በገምጋሚ ግብረመልስ ነው፡፡ በሌላ መልኩ መ.2 ከነዚህ ከተዘረዘሩት ውስጥ የተጠቀሙት አስተካካይ ወይም ስህተትን መጠቆምና ገምጋሚ ግብረመልሶች ናቸው፡፡ ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ብዙ ግዜ አልጠቀምም ምክንያቱም ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን ከ5ኛ ክፍል ስለሚጀምሩ እራሳቸው ካለረመዳት ሊያርሙ ስለማይችሉ ነው ብለዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እንደ መ.2፤ መ.3 የሚከተለውን አስቀምጠዋል:- ከእነዚህ ውሰጥ አመቻች ግብረመልስ እጠቀማለሁ፡፡ አስተካካይ ግብረመልስና ገምጋሚ ግብረመልስ እጠቀማለሁ፤ ነገር ግን ትዕዛዛዊ ግብረመልስን ብዙ ግዜ አልሰጥም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የእራሳቸውን ሰህተት እንዲያስተካክሉ የሚል ስለሆነ ተማሪዎቹ ራሳቸው ማስተካከል ከበድ ስለሚላቸው እሱን አልጠቀመም፡፡ በመጨረሻ መ.4 የተለያዩ የግብረመልስ አይነቶችን እጠቀማለሁ፡፡ ትእዛዛዊን እና አመቻችን በአብዛኛው የማዘወትረው ይሆናል ብለዋል፡፡

መምህራን በዚህ መለኪያ መሰረት ገምጋሚ ግብረመልስ በአብላጫነት እንደተጠቀሙ ሲያሳይ በአጠቃላይ ገምጋሚ ግብረመልስን ስለተጠቀሙ ተዘውታሪው ግብረመልስ ገምጋሚ ግብረመልስ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአመቻች ግብረመልስ ፣ በትዕዛዛዊ ግብረመልስና በአስተካካይ ግብረመልስ መካከል የተወሰነ የውጤት ቀረቤታ ቢኖረም ከገምጋሚ ግብረመልስ አንጻር ሲታይ ግን የተመጣጠነ አይደለም፡፡ ምላሹ በግብረመልስ አይነት የተመጣጠነ አለመሆኑ ደግሞ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል ረገድ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ ምንም እንኳን መምህራን ግብረመልስ ቢሰጡም የተለያየ የአሰጣጥ ልዩነት ይታባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- መ.1 ቅርጽንም ሆነ ይዘትን ትኩረት ያደረገ የግብረመልስ ቢሰጡም ከማክበብና ሰርዝ ከማድረግ በስተቀር ችግሩ ምን እንደሆነ ወይም ምን ማስተካከል እንዳለበት አልገለጹም፡፡ መ.2 ምንም እንኳን ቅርጽንም ሆነ ይዘትንም ትኩረት ያደረገ ግብረመልስ ቢሰጡም ቅርጽን በተመለከተ በማክበብ፣ በማስመርና የጥያቄ ምልክት በማድረግ ይዘትን ባተኮረ ግብረመልስ ላይ ሁሉንም ስህተት ለማረም ችግር አለበት፡፡ መ.3 ከሌሎቹ መምህራን በተለየ ሁኔታ ለቅርጻዊ ግብረመልስ ችግሩን ቢጠቁሙም በተሟላ ሁኔታ አልተሰጠም፤ ነገር ግን ለይዘታዊ ግብረመልስ ጥሩ እርማት ሰጥተዋል፡፡ መ.4 ለቅርጻዊ ግብረመልስ የሰዋሰው ችግር እንዳለበት ቢገልጹም የቱጋር እንደሆነ አልተጠቆመም፡፡ ነገር ግን ለይዘታዊ ግብረመልስ በማክበብና በማስመር ስህተቱን ቢያሳዩም ችግሩ ምን እንደሆነ አልተጠቆመም፡፡

ከላይ ለቀረበው ትንታኔ እንደማሳያ የሚሆኑ የተለያየ ይዘት ያላቸው በተማሪዎች የተጻፉና በመምህራን ግብረመልስ የተሰጠባቸው ጽሁፎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ ሰነዶቹም የተማሪዎችን ፍቃደኝነት በመጠየቅ ኮፒ ተደርጎ ተመልሶላቸዋል፡፡

ነገድ ካሳ

ፋኖቹና ገርጥቆው ::

እንደ፡ የፋኖቿ መበርታ፡ በማበር፡ የኮሌ፡
እንዷሹ ሰብ፡ ተጠላ፡ ከገርጥቆው፡ ጋሬ ::
እኔ፡ ኗኝ መበርቱ፡ በርኳን፡ ያገርሰጠ
መምጣለምን ከጂፋቼ የምገለልፕ
እንዘ፡ ዓን፡ እሳቱ እንዷሪሁ ተደንቆሁ፡
ዘርዓያን፡ ከበኸኝ እንዷሪው፡ ተማኝሁ ::
እለማበቸው ከቶ፡ የምንኘውረው፡ ለሀኬ፡
በርካኬ ሌቃ፡ ደረስ ደግሞዋ፡ እንዷሬጎበኪ፡
ተሰሊሟቶ፡ በመጠ እንዷደዘሊገ
እንዷቱን ፋመጠሪቧቹ መንገደ፡ የምንዝገ ::
ዐንክፋት፡ እያሆንህ ሠኪዮን፡ እንቶሏሌ
ገለለ፡ በለ ከፋት በርካኬ፡ ደከፋል ::

እንገልግለው ፋጠ፡ ከሆኑበኝ፡ ጢፋት
እወፍናጠን፡ ለኔተ፡ ከሆንክሁ፡ ዐንቋቁፋት
ለኒደለሁ፡ በርቃ፡ ለለቀለት፡ በቻ
ከጎን፡ የኳሰ የኳለሰ ጽዋን
መጠና መበርቱን፡ እጠፋው፡ በንድ እፋን
እጮር፡ ~~ዋቶ~~ እያሆኝ ተጠለከቶኛቶ
መለያና፡ እንቅፋት፡ ጸቀመን፡ ከገባኝ ::
እወቀኝ፡ እወቅኝ እንዷለ፡ በኳሠ
ሰጠማው፡ እንደዘሁ፡ ያመጠላ እጫበሰ ::


6/10

እንተዋቂ፡ የኪዳኔ ጸሀፊዎች ሽፋሮል
መምህር ሽንዘለለ
የቶለቶ ዓገረፍኝ ሽፋሮል

በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳን እነደተብራራው አመቻች ግብረመልስ በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ በጥያቄና አስተያየት መልክ የሚሰጥ የግብረመልስ አይነት ነው፡፡ ግብረመልሱ በተወሰነ ጉዳይ ላይ በማተኮር ጠቅለል ባለ ሁኔታ በማቅረብ የሚከናወን እርማት ነው በማለት Moxely (1989)ያብራራሉ፡፡ ከላይ በቀረበው የተማሪ ጽሁፍ ላይ ተማሪው ስርአተ ነጥብ ባለመጠቀሙ ለምን ስርአተ ነጥብ እንዳልተጠቀመ ተጠይቆ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ደግሞ የእጅ ጽሁፉን እንዲያሻሽል፣ መስመር እንዳይዘልና የቃላት ግድፈቶችን እንዲያሻሽል አስተያየት ተሰጥቶታል፡፡

በክለሳ ድርሳኑ እንደተገለጸው አስተካካይ ግብረመልስ ተማሪዎች የፈጸሟቸውን ሰዋሰዋዊ ስህተቶች በመጠቆምና ስተቶችን አስተካክሎ ቀጥተኛ ግብረመልስ የሚሰጠበት ተግባር ነው፡፡ ግብረመልስ አሰጠጡም በማጥፋት፣ በመጨመር፣ ቅደምተከተልን በማስተካከል፣ የተሳሳቱትን ቃላትና ሀረጋት፣ በስህተት የገቡ አያያዦችን፣ የአረፍተ ነገር ድግግሞሽን፣ የተዘለሉ ቃላትንና ሀረጋትን በመሙላት ማስተካከል ናቸው በማለት Anglo and Cross (1993) ይገልጻሉ፡፡ ከላይ ያለው ግብረመልስ በዚሁ አይነት መንገድ የተሰጠ ነው፡፡ ለምሳሌ ተማሪው ሲጽፍ የፈጠራቸውን የቃላት ግድፈቶች መምህሩ አስተካክሎ በመጻፍ ስህተቱን ጠቁሟል፡፡ በተደጋጋሚ የገባውን አረፍተ ነገር በመሰረዝ ቀጥተኛ ግብረመልስ ሰቷል፡፡

ከዚህ በታች እንደማሳያ የቀረበው የገመጋሚ የግብረመልስ አይነት ነው፡፡



ይህ የግብረመልስ አይነት በምዕራፍ ሁለት ስር እንደተብራራው ከተማሪዎች ጥሩ ውጤት ማምጣት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ጥሩ ጽሁፍ የጻፉትን ተማሪዎች የሚያበረታታ ጥሩ

ያልሰሩትን ግን የመስራት ፍላጎታቸውን የሚቀንስ፣ በቀጣይ የድርሰት ጽሁፋቸው ቀሪውን ነጥብ ለሞሙላት ትነሳሽነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ የግብረመልስ አይነት ነው በማለት Daiker (1989)ያብራራሉ፡፡ በመሆኑም ከላይ የቀረበው በመምህር ግብረመልስ የተሰጠበት ጽሁፍ በዚሁ መንገድ የተሰጠ በመሆኑ ጥሩ ጽሁፍ የጻፉትን ተማሪዎች የሚያበረታታ ነው፡፡

### 4.2.2 የጽሁፋዊ ግብረመልስ ስልቶች

በዚህ አርዕስት ስር በተከታታይ ሶስት የተማሪዎች ወረቀቶች ላይ መምህራን የተከተሏቸው የግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶች ብዛት ይተነተናል፡፡ ስለሆነም መምህራን የተጠቀሙትን የጽሁፋዊ ግብረመልስ ስልቶች ማለትም ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት፤ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት እና ጠቋሚ የአስተራረም ስልት እንዴት እንደሆነ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ሰንጠረዥ አራት፡- በተከታታይ ሶስት የተማሪዎች ወረቀቶች ላይ መምህራን የተከተሏቸው የግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶች ብዛት

| መምህር | የጽሁፋዊ ግብረመልስ ስልቶች | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት | | | | | | ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት | | | | | | ጠቋሚ የአስተራረም ስልት | | | | | |
| | ጽ 1 | | ጽ2 | | ጽ3 | | ጽ1 | | ጽ2 | | ጽ3 | | ጽ1 | | ጽ2 | | ጽ3 | |
| | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % |
| መ.1 | 28 | 26 | 44 | 41 | 36 | 33 | 28 | 26 | 32 | 30 | 48 | 44 | 36 | 33 | 36 | 33 | 36 | 33 |
| መ.2 | 45 | 42 | 38 | 35 | 25 | 23 | 32 | 30 | 26 | 24 | 50 | 46 | 35 | 32 | 30 | 28 | 43 | 40 |
| መ.3 | 37 | 34 | 36 | 33 | 35 | 32 | 30 | 28 | 33 | 31 | 45 | 42 | 36 | 33 | 36 | 33 | 36 | 33 |
| መ.4 | 31 | 29 | 40 | 37 | 37 | 34 | 34 | 31 | 32 | 30 | 42 | 39 | 32 | 30 | 38 | 35 | 38 | 35 |

ከላይ ከሰንጠረዥ አራት መረዳት እንደሚቻለው ለናሙና ከተወሰዱ ሶስት የተማሪ ጽሁፎች ውስጥ መ.1 ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልትን ተጠቅመው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.2 ላይ 41 % ፣ መ.2 በጽ.1 ላይ 42% ፣ መ.3 በጽ.2 33% እና መ.4 በጽ.2 ላይ 37% ያህል ሁሉንም ስህተቶችን አርመዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው መ.1 ፣ መ.3 እና መ.4 ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት በ ጽ.2 ላይ ይበልጡን ተጠቅመዋል፡፡ እንዲሁም ጠቅላላ ከሰጡት ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት ውስጥ ሁሉም መምህራን ለጽ.3 የበለጠ ትኩረት በመስጠት ማለትም መ.1 ለ ጽ.3 33% ፣ መ.2 ለጽ.3 23% ፣ መ.3 ለ ጽ.3 32% እና መ4 ለ ጽ.3 34 % ከ ጽ.1 እና ጽ.2 የበለጠ ትኩረት በመስጠት ስህተቶችን መርጠው አርመዋል፡፡ በተጨማሪም መ.4 በ ጽ.3 ላይ የበለጠ ትኩረት እንደሰጡ ያሳያል፡፡

ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት የሁሉም መምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ተመሳሳይ (ተቀራራቢ) ነው፡፡ መ.1 በጽ.3 44% ፣ መ.2 ለጽ.3 በ 46% ፣ መ.3 በጽ.42%እና መ.4በጽ.3 ላይ 45% ከሌሎች ጽሁፎች በላቀ ሁኔታ ግብረመልስን እንዳዘወተሩ መረጃው ያሳያል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልትን ከሌሎች በላቀ ሁኔታ መምህራን እንዳዘወተሩት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም የሚያመለክተው መምህራን በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ ጠቃሚ ስህተቶችን መርጦ በማረም ስልት አብዘኛውን ጊዜ አዘውትረው እርማት የሚሰጡ መሆኑ ነው፡፡

ጠቃሚ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት የሚካሄደው በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ የሚታዩ ስህተቶችን በሙሉ ሳይሆን በተመረጡና በዋና ዋና ስህተቶች ላይ በማተኮር የሚከናወን ነው፡፡ ጠቃሚ የአስተራረም ስልትን በመጠቀም ጠቅላላ ለእያንዳንዱ ከተሰጡት 108 ግብረመልስ ውስጥ መ.1 እና መ.3 በ በጽ.1፣ ጽ.2 እና በጽ.3 ላይ በእኩል መጠን ማለትም 33 % ጠቃሚ የአሰተራረም ስልትን ተጠቅመው እርማት ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ ይህ የሚያሳየው ሁሉንም ስልቶችን እየቀላቀሉ ግብረመልስ ለመስጠት መ.1 እና መ.3 ሞክረዋል ማለት ነው ፡፡ ነገር ግን በአጠቃላይ መ.2 ለጽ.3 በ 40%፣ መ.4 ለ ጽ.2 እና 3 በ እኩል የ35% የድርሻ ደረጃ የበለጠ ጠቃሚ የግብረመልስ ስልቶችን ተጠቅመዋል፡፡ ስለዚህ መ.1፣ መ.2፣ መ.3 እና መ.4 ተቀራራቢ በሆነ መልኩ ከሌሎች የአስተራርም ስለቶች ለጠቃሚ የአስተራረም ስልትን እንዳዘወተሩ መረጃው ያሳያል፡፡ ስለሆነም አጠቃላይ የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ መምህራን በሁሉም የተማሪ ወረቀቶች ላይ የተጠቀሟቸው የግብረመልስ ስልቶች ብዛት 432 ናቸው፡፡ ስለዚህ መምህራን የግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶች መሰረት አድርገው

ጠቅላላ ከሰጡት 432 ግብረመልስ ውስጥ የበለጠ ጠቋሚ የአስተራረም ስልት ግብረመልስ መስጠታቸውን ያሳያል፡፡

የመምህራን ቃለ መጠይቅ ማለትም ለጥያቄ ቁጥር 3 ፡- የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልሶች ምን ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው? መ.1 ሲመልሱ ፡- በግምጋሚ ግብረመልስ በመስጠት ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት ነው የምጠቀመው ሲሉ፤ መ.2 በተመሳሳይ መልኩ ስህተትን በመጠቆም ተማሪዎች የሚሰጡትን ስህተት የመጠቆም አዝማሚያ አዘወትራለሁ ብለዋል፡፡ መ.3 እና መ.2 እንደተጠቆመው ሁሉንም ስህተቶች የማረምስልት ላይ ያዘወትራሉ፡፡ መ.4 ጠቋሚ የአስተራረም ስልትን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም ጠቋሚ ስህተቶችን መርጦ በማረም የመምህራን አጠቃቀም ስልት በጣም ተቀራራቢ ነው፡፡ ሌላው ጉዳይ መምህራን በሁለቱ ማለትም ስህተቶችን መርጦ በማረም ስልት እና ጠቋሚ የአስተራርም ስልት ከሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት የግብረመልስ አሰጣጣቸው ሁኔታ ክፍተቱ በጣም የሰፋ ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን ስልቶችን አመጣጥነው የመጠቀም አካሄድ በተለይ በሁለቱ ስልቶች ላይ ልዩነት አይታይባቸውም፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪዎች የጽሁፍ ክሂል ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

ከላይ ለቀረበው ትንታኔ እንደማሳያ የሚሆኑ በተማሪዎች የተጻፉና በመምህራን ግብረመልስ የተሰጠባቸው ጽሁፎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

# ጅብና አንበሳ

ተሰጠው አበጋዝ

አንዴ አንበሳና ዘመዱ ጅብ ሆነው ወደ አደን ሄዱ ???
ቅጠሉ ሰይጹሩ ሆዱ ሆዱ ፍራጹ አለጁ. ነበር ፈነ ፍጆርም ቢሞሉጹ
እየጁርጣጠው መካሰስ እንቃፉምና እሱን? ሁሉ ተገባኩ በዚያን ጊዜ የዘመዱ
አንድ ሰፈር ገቡ መፍጨም ሁሉ እንፀደቅምና ጠጠዘመዱ ሁሉም ከአፉ አንበሳአለም
ከዘመዶቹን ሁሉ ገቡ ተናገረ የየጁርጣጠውን ተናገሮ መሰረታቸው ሄዱ:: ደዩ ግን መደመን
የቆላ መጠየቅ እንቃፉምና ከበተዋን የቆላ የኩሌሉ እንታቸው የቆኩሱቹን ምንንዴፉ
ለመጋቃተው እየመጡ አንበሳና ዘመዱ ጅቦቹ ሆኑን መደ አደን ሄደን ቆል:: ከእንሰሁቹና
ሰላሜ አግኝተን ሁሉን እንደምንገባን ከዘመዶቹን እንደ ሁሉም ተገናኙ መምጣጣቸውንና
አየቱ:: እንዴት ደክ ነገር ጅዩ ለማጣለው የክም ከአንበሳ አንበሳ ዘመዱ ከዘመዱ
ጅቦች አንደ እንዴት ደክ መግባት ነው:: ከምንቱን ሰፈርና አንዱ ሰገነ ዘመዱ
እሰመሩጣከው እንዲከ መደ አንበሰው በቶ እየፈነሊ ደሊልና ቋየአንበሳን ወቶ
ለመስከተው እንደገለሰ እንደታቸውን ተቀበሎ ዘመዱን ያመራቸን ነገሩዩ ፈሩ እንደደቱ
ስከጥ ደሕንፉበቱ ከበለ በሆዴ መስጠ ፀፀቱ እደሮቡ ፍዩ እንቶ ከበስ እከተ
ጉልበ ቆየዉና ለሰ የመጠጡሁበቶችን አሳይ ተናገር በእሰው ሞ ጉዳዩ ደቱን የዘመዱ
ደርስ ገሀን የተሰጡጠውን ፈሪ አሰሩ አደርጋው እንደቀረበን ከልጅ ለምም ውን
እክምምነቱከው ሁሉ ወቦርስ አስረከበው:: እዩ እንበሳም በመሰሩ ቆረሰ ከምሁን
ወፈረስ የምምሩ ሰራን ነውና እመሰገና ለሰቁና ለመሆፍ ሰናው ግብሰ

ሃጥታሪክና ምሳሌ


ገብረ መንግሥቱ

5/10

የተመሰገነበት ሀሳብ
ጽሑፍ ቢስተካከል አሪፍ ነዉ ::

ሁሉንም ስህተቶች በማረም ስልት ለተማሪው ሁሉንም ስህተቱን ለቅሞ ማሳየት ነው፡፡ በዚህ አስተራረም ተማሪው ስህተቱን ተረድቶ እንዲያስተካክል ይረዳዋል በማለት Laland (1982) ይገልጻሉ፡፡ መምህራን የተማሪዎችን ችሎታ ለመመዘን የተለያዩ የግብረመልስ ስልቶችን መጠቀም አለባቸው፡፡ ምንም እንኳን የመምህራን የግብረመልስ አሰጣጥ ቢለያዩም ዋናው አላማው የተማሪውን የጽህፈት ክሂል ማዳበር ነው፡፡ በዚህ ማሳያም ተማሪው ሳይጽፍ የዘለለውን ቦታ የጥያቄ ምልክት በማድረግ፣ የቃላትና የሀረጋትን ግድፈቶች ለቅሞ ከስራቸው በማስመር መምህሩ ጠቁሟል፡፡

ከዚህ በታች የቀረበው ጽሁፍ በጠቋሚ የአስተራረም ስልት ግብረመልስ የተሰጠበት ነው፡፡


Memo No.
Date.

በምዕራፍ ሁለት ስር እንደተብራራው በጽሁፍ ስራ ላይ ስህተትን ጠቋሚ የሆኑ የተለያዩ ምልክቶችን በመጻፍ መጠቆም ነው፡፡ በተማሪዎች ድርሰት ላይ ስህተት የሆነውን ጥያቄ ምልክት በማድረግ፣ በማስመር፣ በጽሁፍ በማብራራት፣ በማክበብና በመሳሰሉት ምልክቶች ስህተታቸውን በማሳየት እንዲያርሙት ማድረግ ነው በማለት Byrne (1988) ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ማሳያ መምህሩ የራሳቸውን ዘዴ ተጠቅመው ተማሪው ስህተቱ ምን እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ለምሳሌ የቃላት ግድፈቶች ላይ የጥያቄ ምልክት በማድረግ፣ በስህተት የገባውን ሆሄ በማክበብና ትክክለኛውን በመጻፍ፤ በስህተት የገቡ አረፍተ ነገሮችን በማክበብ ስህተቶችን ጠቁመዋል፡፡

### 4.2.3 ከግብረመልስ አሰጣጥ የትኩረት አቅጣጫ አንጻር

መምህራን የተማሪዎችን ጽሁፍ በሚያርሙበት ወቅት በቋንቋው ቅርጽ ላይ እና በጽሁፉ ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ እንደሚሰጡ በምዕራፍ ሁለት የጥናቱ ክፍል ተገልጿል፡፡ በዚህ መሰረት እያንዳንዱ መምህር በተከታታይ ሶስት የተማሪ ጽሁፎች ላይ ትኩረት ያደረጉበትን ግብረመልስ ለመጠቆም እና እነዚህን የትኩረት ነጥቦች ለምን ያህል ጊዜ ደጋግመው እንደተጠቀሙ በቁጥርና በመቶኛ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ተገልጿል፡፡

ሰንጠረዥ አምስት፦የመምህራንን የግብረመልስ የትኩረት አቅጣጫ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| መምህር | የመምህራን የጽሁፍ ግብረመልስ የትኩረት አቅጣጫ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቅርጽን ትኩረት ያደረገ | | | | | | ጠቅላላድምር | | ይዘትን ትኩረት ያደረገ | | | | | | ጠቅላላ ድምር | |
| | ጽ | | ጽ2 | | ጽ3 | | | | ጽ1 | | ጽ2 | | ጽ3 | | | |
| | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % |
| **መ.1** | 39 | 36 | 40 | 37 | 29 | 27 | 108 | 100 | 27 | 25 | 40 | 37 | 41 | 38 | 108 | 100 |
| **መ.2** | 31 | 29 | 48 | 44 | 29 | 27 | 108 | 100 | 40 | 37 | 32 | 30 | 36 | 33 | 108 | 100 |
| **መ.3** | 37 | 34 | 43 | 40 | 28 | 26 | 108 | 100 | 34 | 31 | 41 | 38 | 33 | 31 | 108 | 100 |
| **መ.4** | 47 | 44 | 44 | 41 | 17 | 16 | 108 | 100 | 32 | 30 | 47 | 44 | 29 | 27 | 108 | 100 |

ከላይ ከሰንጠረዥ አምስት መረዳት እንደሚቻለው ለናሙና ከተወሰዱ ሶስት የተማሪ ጽሁፎች ውስጥ መ.1 ቅርጽን ትኩረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 36 %፣ በጽ.2 ላይ 37% እና በጽ.3 ላይ 27% ግብረመልስ ሰጥተዋል። እንዲሁም ይዘትን ትኩረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ግብረመልስ ውስጥ 25% በጽ.1 ላይ፣ 37% በጽ.2 ላይ እና 38% በጽ.3 ላይ ይዘትን ትኩረት ያደረገ ግብረመልስ ሰጥተዋል፡ ፡ በአጠቃላይ መ.1 ቅርጽንም ይዘትንም መሰረት አድርገው ግብረመልስ ቢሰጡም ይዘትን ትኩረት ያደርገ ለጽሁፍ 2 እና 3 ተቀራራቢ በሆነ መልኩ ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ ሰጥተዋል። ስለዚህ መ.1 በይበልጥ ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ እንደሰጡ መረጃው ያሳያል።

በሌላ መልኩ መ.2 ቅርጽን ትኩረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 29 %፣ በጽ.2 ላይ 44% እና በጽ.3 ላይ 27% ግብረመልስ ሰጥተዋል። እንዲሁም ይዘትን ትኩረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ግብረመልስ ውስጥ 37% በጽ.1 ላይ፣ 30% በጽ.2 ላይ እና 33% በጽ.3 ላይ ይዘትን ትኩረት ያደረገ ግብረመልስ ሰጥተዋል፡ ፡ በአጠቃላይ መ.2 ቅርጽንም ይዘትንም መሰረት አድርገው ጠቅላላ የቅርጽ እና ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስሰ ጥተዋል። ስለዚህ መ.2 በሁለቱም መካከል ያለው ልዩነት ያን ያህል የሰፋ ስላልሆነ ቅርጽም ይዘትም ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ ይሰጣሉ ወደሚል ድምዳሜ መድረስ ይቻላል።

በተመሳሳይ መልኩ የመምህራንን የግብረመልስ የትኩረት አቅጣጫ ከመ.3 አቅጣጫ ስንመለከት ቅርጽን ትኩረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 34 %፣ በጽ.2 ላይ 40% እና በጽ.3 ላይ 26% ግብረመልስ ሰጥተዋል። እንዲሁም ይዘትን ትኩረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ግብረመልስ ውስጥ 31% በጽ.1 ላይ፣ 38% በጽ.2 ላይ እና 31% በጽ.3 ላይ ይዘትን ትኩረት ያደረገ ግብረመልስ ሰጥተዋል። በአጠቃላይ መ.3 ቅርጽንም ይዘትንም መሰረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ያህል ግብረመልስ ውስጥ ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ ሰጥተዋል። ስለዚህ መ.3 በይበልጥ ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ ሰጥተዋል ማለት ነው።

የመ.4 መልስ ስንመለከት ቅርጽን ትኩረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 44 %፣ በጽ.2 ላይ 41% እና በጽ.3 ላይ 16% ግብረመልስ ሰጥተዋል።

እንዲሁም ይዘትን ትኩረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት108 ግብረመልስ ውስጥ 30% በጽ.1 ላይ፣ 44% በጽ.2 ላይእና 27% በጽ.3 ላይ ይዘትን ትኩረትን ያደረገ ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ መ.4 ቅርጽን ምይዘትንም መሰረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ያህል ግብረመልስ ውስጥ ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ መ.4 በይበልጥ ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ ሰጥተዋል የሚል ድመዳሜ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡

የመምህራን ቃለ መጠየቅ ማለትም ለ5ኛ ጥያቄ፡- የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከመዋቅር አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ ፡- በሆሄያት፣ በቃላት፣ በአርፍተ ነገሮች፣ በሰዋሰዋዊ ስህተቶች፣ በሥርዓተ ነጥብ ስህተቶችና ወዘተ... ለሚለው መ.1 ሲመልሱ ፡- ሁሉንም ያካትታል ግን ቢሆንም በአርፍተ ነገር ላይ አተኩራለሁ፡፡ አርፍተ ነገር በሚሰሩበት ጊዜ ሁሉንም ቃላትና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀምንና ሌሎችንም አካቶ በውስጡ ስለሚይዝ ነው፡፡ በተመረጡ ስህተቶች ላይ ትኩረት ቢኖርም ሁለንም መነካካቴ አይቀርም ብለዋል፡፡ መ.2 በፊናቸው ሲያብራሩ፡- እንግዲህ እነኚህ ተማሪዎች ይህንን ስህተቶቻችውን ካልተማሩ የትምህርቱን ይዘት ሙሉ በሙሉ አወቁ ወይንም ተማሩ ስለማይባል በቃላት፣ በስርዓተ ነጥብና በሰዋሰው እንዲሁም ሌሎችን ስህተቶችን የግድ ግብረመልስ ተማሪው እንዲያውቅ መስጠት አለብኝ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከሌሎቹ በተለየ መልኩ መ.3 ሁሉንም ማስተካከያ እሰጣለሁ በማለት ምክንያታቸውን ሲያብራሩ፡- ምክንያቱም ትምህርቱ ጽሁፍ ላይ ያለው ስርዓተ ነጥብንም፣ የሆሄያትን ግድፈትንም፣ የቃላት ግድፈትንና የሰዋሰው መዋቅርን የሚመለከት ስለሆነ ሁሉንም በተቻለ መጠን ለማስያዝ እና ለማስጨበጥ ወይም ስህተታቸውን እንዲያርሙ ለማድረግ እሞክራለሁ ብለዋል፡፡ መ.4 በአዎንታዊ መልኩ መክንያታቸውን ሲያብራሩ፡- ...... የጽሁፍ ስራ ላይ የምሰጠው የግብረመልስ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነው፡፡ በአብዛኛው የሚጽፉት በአማርኛ ስለሆነ የ1ኛ ቋንቋ በ2ኛ ቋንቋ ንግግራቸውና ጽሁፋቸው ላይ ተጽዕኖ እንዳያመጣ በማሰብ በፊደል ላይ ትኩረት አላደርግም፡ ፡ ነገር ግን ሥርዓተ ነጥቦችንና ሰዋሰዎችን በልዩ ትኩረት እርማት እሰጣለሁ ብለዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለ6ኛ ጥያቄ፡- የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከይዘት አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ፡- የመልዕክቱ ትክክለኛነት ላይ ሂሳዊ አስተያየት በመስጠት፣ በመጠየቅና በማስተካከል፡፡ መ1 ይዘት አንዱ የትምህርቱ አካል ነው፤ ይዘት ግድ ነው፡፡ እንደ ርዕሱ ማጠርና መርዘም ምላሽ እሰጣለሁ በማለት ያላቸውን አስተያየት አቅርበዋል፡፡ በተመሳሳይም መ2 ሲያብራሩ፡- በጥያቄናመልስ መንገድ ገለጻ አደርጋለሁ፡፡ የመልክቱም ትክክለኛነት እከታተላለሁ ሲሉ፤ መ3 በተለየ መልኩ ሁሉንም እጠቀማለሁ፡፡ ጽሁፉ የሚያተኩረው ስህተቶችን ለማረም ስለሆነ እዚያ ላይ ትኩረት ሰጥቼ እከታተላለሁ ፤

እንዲያስተካክሉ አደርጋለሁ የሚል መልስ መልሰዋል፡፡ በመጨረሻ መ4 ለተማሪዎች የምሰጠው ግብረመልስ በተለይ በይዘቱ ትክክለኛነት ላይ ግብረመልስ በትኩረት እሰጣለሁ በማለት የትምህርቱን ሂደት አብራርተዋል፡፡ ስለሆነም መምህራን የተማሪዎችን የጽሁፍ ስራ ለማረም በሁለት ነገሮች ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ ተገልጿል፡፡ ስለሆነም ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ መምህራን ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ጠቅላላ የሰጡት ግብረመልስ ላይ ትኩረት አድርገዋል ማለት ይህም የሚያሳየው መምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ ሲሰጡ ይዘትና ቅርጽ ላይ የሚሰጡት ትኩረት ሙሉ በሙሉ ተቀራራቢ አለመሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም በሁለቱ መካከል የተገኘው ውጤት የጎላ ልዩነት ስላላሳየ ነው፡፡

ይዘት ተኮር ግብረመልስ ትኩረቱ ጸሐፊው ማስተላለፍ የፈለገውን መለዕክት ትክክለኛ መሆኑን መመርመር ነው፡፡ ስለዚህ ይዘት ተኮር ግብረመልስ ሊቀርብ የሚችለው ሂሳዊ አስተያየት በመስጠት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ማጠቃለያ በማቅረብ፣ ስህተት የሆነውን አቃንተን በማሳየት፣ በማድነቅ፣ ስህተቱን በማሳየት፣ በትክክል ለሰሩት በማበረታታት ናቸው፡፡ መምህራን በተማሪዎች የመጨረሻ ጽሁፍ ላይ ትኩረት ቢያደርጉ ይመረጣል በማለትZamel (1985) ያብራራሉ፡፡ ከላይ ያለው ሰነድ ተማሪዋ ማስተላለፍ የፈለገችው መልዕክት ትክክለኛ መሆኑንና አለመሆኑን ለመግለጽ የተሰጠ ግብረመልስ ነው፡፡ ተማሪዋ በጻፈችው ድርሰት ውስጥ የቃላት ግድፈትና ስርዝ ድልዝ መሆኑን መምህሩ ቢጠቁመምም በዋነኛነት በአንድ ቁጥር ላይ የተገለጸው የተማሪዋ የሕይወት ታሪክ የተሟላ አለመሆኑንና ቀሪ ታሪኮችን ጨምራ አስፋፍታ እንድትጽፍ የተሰጣት የግብረመልስ አይነት ነው፡፡

### 4.2.4 ከግብረመልስ መገለጫ ባህርያት አንጻር

መምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ ሲሰጡ ግብረመልስን የሚገልጹበት ባህሪ አዎንታዊ ባህሪያት እና አሉታዊ ባህሪያት ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ በዚህ ጥናት በቀደመው በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ላይ በዝርዝር ሀሳብ ተቀምጧል፡፡ ስለሆነም በሶስት ተከታታይ የተማሪ ጽሁፎች ላይ እያንዳንዱ መምህር የትኛውን የግብረመልስ መገለጫ ባህሪይ ተከትለው እርማት እንዳካሄዱ ለመጠቀም ከሰነድ የተገኘውን መረጃ በሚከተለው ሰንጠረዥ ለማሳየት ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ ስድስት፦ የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ባህሪያት ብዛት

| መምህር | የመምህራን የጽሁፋዊ ግብረመልስ መግለጫ ባህርያት | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አዎንታዊ ባህሪያት | | | | | | ጠቅላላ ድምር | | አሉታዊ ባህሪያት | | | | | | ጠቅላላ ድምር | |
| | ጽ 1 | | ጽ2 | | ጽ3 | | | | ጽ1 | | ጽ2 | | ጽ3 | | | |
| | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % |
| መ1 | 46 | 43 | 31 | 29 | 31 | 29 | 108 | 100 | 45 | 42 | 43 | 40 | 20 | 19 | 108 | 100 |
| መ2 | 47 | 44 | 42 | 39 | 19 | 18 | 108 | 100 | 30 | 28 | 41 | 38 | 37 | 34 | 108 | 100 |
| መ3 | 38 | 35 | 32 | 30 | 38 | 35 | 108 | 100 | 34 | 31 | 46 | 43 | 28 | 26 | 108 | 100 |
| መ4 | 39 | 36 | 41 | 38 | 28 | 26 | 108 | 100 | 37 | 34 | 40 | 37 | 31 | 29 | 108 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ ስድስት መረዳት እንደሚቻለው ለናሙና ከተወሰዱ ሶስት የተማሪ ጽሁፎች ውስጥ መ.1 ጠቅላላ ከሰጡት አዎንታዊ ባህሪን ከያዘ 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 43 % ፣በጽ.2 እና ጽ.3 ላይ በተመሳሳይ መልኩ 29% ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ጠቅላላ ከሰጡት አሉታዊ ባህሪን ከያዘ 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 42%፣ በጽ.2 ላይ 40% እና በጽ.3 ላይ 19% ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ መ.1 የግብረመልስ መግለጫ ባህሪያትን ተጠቅመው ለአሉታዊ ግብረመልስ የበለጠ ትኩረት ሰጥተዋል፡፡ ሆኖም ግን በሁለቱም መካከል ያለው የግብረመልስ ልዩነት ብዙ ስላልሆነ አዎንታዊና አሉታዊ ግብረመልስን እያጣመሩ ይሰጣሉ ወደሚል ድምዳሜ ለመድረስ ያስችላል፡፡

የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ባህሪያትን ስንመለከት፤ መ.2 ጠቅላላ ከሰጡት አዎንታዊ ባህሪን ከያዘ 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 44%፣ በጽ.2 ላይ 39% እና በጽ.3 ላይ 18% ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ጠቅላላ ከሰጡት አሉታዊ ባህሪን ከያዘ 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 28%፣በጽ.2 ላይ 38 % እና በጽ.3 ላይ 34% ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ መ.2 የግብረመልስ መግለጫ ባህሪያትን ተጠቅመው ጠቅላላ ከሰጡት ግብረመልስ ውስጥ አዎንታዊ ግብረመልስን በበለጠ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ መ.2 ከአሉታዊ ይልቅ አዎንታዊ ግብረመልስ እንደሚያዘወትሩ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመቀጠል መ.3 ጠቅላላ ከሰጡት አዎንታዊ ባህሪን ከያዘ 108 ግብረመልሶች ውስጥ በ ጽ.1 ላይ 35%፣ በጽ.2 ላይ 30% እና በጽ.3 ላይ 35% ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ጠቅላላ ከሰጡት አሉታዊ ባህሪን ከያዘ 108 ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 31%፣ በጽ.2 ላይ 43% እና በጽ.3 ላይ 26% ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ መ.3 የግብረመልስ መግለጫ ባህሪያትን ተጠቅመው ተጠቅላላ ከሰጡት 216 ግብረመልስ ውስጥ አዎንታዊ ግብረመልስን በተመጣጣኝ መልኩ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ መ.3 ከአሉታዊ ይልቅ አዎንታዊ ግብረመልስ እንደሚያዘወትሩ ለማረጋገጥተ ችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መ.4 ጠቅላላ ከሰጡት አዎንታዊ ባህሪን ከያዘ 108 ግብረመልሶች ውስጥ በ ጽ.1 ላይ 36%፣ በጽ.2 ላይ 38% እና በጽ.3 ላይ 26% ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ጠቅላላ ከሰጡት አሉታዊ ባህሪን ከያዘ 108 ያህል ግብረመልሶች ውስጥ በጽ.1 ላይ 34%፣ በጽ.2 ላይ 37% እና በጽ.3 ላይ 29% ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ መ.4 የግብረመልስ መግለጫ ባህሪያትን ተጠቅመው ጠቅላላ ከሰጡት 108 ግብረመልስ ውስጥ በተመጣጣኝ መልኩ አሉታዊ ግብረመልስ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ መ.4 ከአዎንታዊ ይልቅ አሉታዊ ግብረመልስ እንደሚያዘወትሩ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የመምህራን ቃለ መጠይቅ ማለትም ለ8ኛ ጥያቄ፡- የግብረመልስ አሰጣጥ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ፡- ቀጥተኛ እርማት፣ ኢቀጥተኛ እርማት፣ አዎንታዊ እና አሉታዊ ግብረመልስ ፣ ጥያቄ እና አስተያየቶችን ይጠቀማሉ፡፡ ካልተጠቀሙ ለምን? ለሚለው መ.1 በብዛት የምጠቀመው ቀጥተኛ እርማት ነው፡፡ ምክንያቱም ከተማሪዎች አቅም አንጻር ስለማወዳድረው ነው፡፡ በቀጥታ እኔ ልጽፍላቸው እችላለሁ፤ ቋንቋውን በማስፋት ደረጃ እንዲታይልኝ ለማለት ነው፡፡ ለተማሪው በተለያዩ ቃላቶች መጠቀም በቀላሉ ሊገባው ስለ ሚችል በብዛት የምጠቀመው ቀጥተኛ እርማት ነው፡፡ አልፎ አልፎ ተማሪው በተለያየ መንገድ እንዲገባው ሲባል ኢቀጥተኛም እርማት ሊኖር ይችላል ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መ2 ሲመልሱ፡- እንግዲህ እኔ በቀጥተኛ እርማት ድክመታቸውን መጠቆም አዘወትራለሁ፡፡ በቀጥተኛ እርማት ምልክቶችን በመጠቀም እጠቁማቸዋለሁ፡፡ ኢአዎንታዊ ግብረመልስ በቀጥታ የማያገለግል ስለሆነ ይህንን ከተማሪዎቹ የቋንቋ ችግር አንጻር አልጠቀመውም፡፡ በተጨማሪ አሉታዊ ግብረመልስ የተባለውን ብዙ አላዘወትርም ምክንያቱም የተማሪውን ሞራል ስለሚነካ፤ ለመጠቀም ያክል ሌሎችም መምህራን ይህንን ባይጠቀሙ እሞክራለሁ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ እንደ መ.1፣ መ.2፣ መ.3 እና መ.4 አሉታዊ ግብረመልስን እንደማይጠቀሙ በማብራራት ምክንያታቸውን ሲገልጹ፡- ምክንያቱም የተማሪዎችን የጽሁፍ ተነሳሽነት ስለሚቀንሰው ነው በማለት መልስ አስቀምጠዋል፡፡ በመጨረሻም መ.4 እንደጠቀሱት፡- … ለተማሪዎች ግብረመልስ ከአሉታዊ በስተቀር ሌሎችን የግብረመልስ ዓይነቶች እና ዘዴዎች እሰጣለሁ በማለት ጠቅለል አድርገው ምላሻቸውን ዘርዝርዋል፡፡

ጠቅላላ መምህራን አርመው በመለሷቸው የተማሪ ጽሁፎች ላይ ግብረመልሱን የገለጹበት ባህሪ ምን እንደሚመስል አጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በአጠቃላይ በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ መምህራን በተማሪ ወረቀቶች ላይ አዎንታዊ እና አሉታዊ ግብረመልስ ምላሾች ሰጥተዋል፡፡ ሁሉም መምህራን ባህሪያትን መሰረት አድርገው ጠቅላላ ከሰጡት ግብረመልስ ውስጥ አዎንታዊ ግብረመልስን ያተኮረ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው መምህራን በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ ጽሁፏዊ ግብረመልስ ሲሰጡ አሉታዊ ከሆነ ግብረመልስ ይልቅ አዎንታዊ ግብረመልስ እንደሚያዘወትሩ ከፍተሻ ሰነዱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.2.5 በተማሪዎች የጽሑፍ ስራ ላይ ግብረመልሶችን በጊዜው ከመስጠት አንጻር

የመምህራን ቃለ መጠይቅ ማለትም ለ4ኛ ጥያቄ፡- በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ ግብረመልሶችን በጊዜው ይሰጣለሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን? ለሚለው መ.1 ሲመልሱ፡-

ይህንን ለማድርግ የራሱ የሆነ እቅድ ስላለው ከጊዜው ጋር ለማጣጣም በማሳጠር ምላሽ ለመስጠት እሞክራለሁ ሲሉ መ.2 ግብረመልስ በጊዜው እንደሚሰጡ በመስማማት አስፈላጊነቱን እንዲህ በማለት አቅርበዋል፦ ምክንያቱም ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ ወዲያው ካልተጠቆሙ ስህተት ውስጥ ስለሚገቡ ይህን በግልጽ ከማድርግ በተጨማሪም እንደሚሰጡም ተናግርዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መ.3 ከግዜ አንጻር ሲያብራሩ፦ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ መልሱን በጽሁፋቸው ላይ ትኩረት አድርጌ እሰጣለሁ በማለት ዘርዝርዋል፡፡ በመጨረሻም መ.4 የድርሻቸውን ሲመልሱ፦ …….ለተማሪዎች የጽሁፍ ሥራ ላይ የምሰጠው ግብረመልስ ከጊዜ ጋር በተጣጣመ መልኩ እንደሚሰጡ አበክረው አብራርተዋል፡፡

የመምህራንን የግብረመልስ አሰጣጥ ከግብረመልሶቹ አንጻር ምን ያህል ከክፍል ደረጃው ጋር የተገናዘቡ ናቸው? ተብሎ ለተነሳው መጠይቅ፤ መ.1፦ ……… መጽሐፉን በምናይበት ጊዜ የተለያዩ ችግሮች አይጠፉም፡፡ ነገር ግን  የተለያዩ ዋቢ ምንጮችን (ሪፈረንሶችን) በመጠቀምና በማሳጠር እንዲሁም በማስተካከል ምላሽ እሰጣለሁ፡፡ በተጨማሪም መጽሐፉ የራሱ የኦርደር ችግር አለበት፡፡ ስለሆነም መምህር እንደ መሆኔ መጠን በራሴ ስልት በመጠቀም ተገቢውን ምላሽ ለተማሪዎቹ በአግባቡ እሰጣለሁ በማለት ምላሻቸውን ዘርዝርዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለተማሪዎች የሚሰጠው ምላሽ በክፍል ደረጃቸው መሰረት እንደሆነ በማብራራት አንዳንድ ችግሮችን በመጥቀስ እንዲህ በማለት አብራርተዋል፦ ………… ተገቢውን ምላሽ እሰጣቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ስላልሆነ በተወሰነ መልኩ ምላሽ መስጠት ያስቸግረኛል፡፡ ቢሆንም ያንን አጣጥሜ በመስራት ምላሽ ለመስጠት እሞክራለሁ ሲሉ አብራርተዋል፡፡ ከሌሎቹ መምህራን ምላሽ በተለየ መልኩ ከግብረመልሶቹ አንጻር ምን ያህል ከክፍል ደረጃው ጋር ማገናዘብ ብዙም የማይከብድና የማይቀል መሆኑን በማስታወቅ ፤ መካከለኛ አድርጌ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ምላሽ እሰጣቸዋለሁ በማለት መ3 አብራርተዋል፡፡ ከሌሎቹ መምህራን ባልተለየ መልኩ መ4 ሲያብራሩ፦ ……ግብረመልሶቹ ተማሪዎቹ ካሉበት የክፍል ደረጃ ያነሰና በታች እንዳይሆን ከፍተኛ ጥረት በማድረግና በመተግበር ተማሪዎቹ ባላቸው የትምህርት ደረጃ ልክ እንዲጽፉ እና እንደስራቸው ግብረመልስ ይሰጣቸዋል፡፡ ከተቻለ ግን ከዛ በላይ እንጂ በታች እንዳይሆን ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ በማለት ጥረታቸውን ገልጸዋል፡፡

የሚሰጡት ግብረመልሶች ከሳምንታዊ ክፍለ ጊዜው እና ከተማሪዎች ብዛት ጋር ምን ያህል እያጣጣሙ ይሰጣሉ? ለሚለው መጠይቅ መ1 የሚከተለውን አብራርተዋል፦…. እስኬጁልም ስላለ ማጣጣም ግድ ነው፡፡ ርዕሱም እንዲገፋልኝ መጽሀፉም ብዙ ስለሆነ በማሳጠርም በተለያየ ሲስተም በመጠቀም በማጣጣም በሚለው ብዙ ጊዜ እጠቀማለሁ፡፡ ዋናውን ፍሬ

ነገር በማስጨበጥ እና በመስጠት ላይ ያተኮረ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የሣምንቱን ትምህርት ለሚቀጥለው ማግኘት የለባቸውም፤ ተመራጭ የሚሆነው ሌላ አዲስ ርዕስ ማወቅ ስለሚጠቅባቸው ነው በማለት ዘርዝርዋል፡፡ በተጨማሪም በተመረጠው ትምህርት ቤት ያለውን የተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ ብዛት ጋር ያልተጣጣመ መሆኑን እና በአንድ ክፍል እጅግ በርካታ ተማሪዎች መኖራቸውን አብራርተው፤ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በሣምንት አናሳ መሆኑንም በመግለጽ፤ ይህንን ችግር እያጣጣሙ ግብረመልስ እንደሚሰጡ መ.2፣ መ3 እና መ4 በተመሳሳይ መልኩ ተናግረዋል፡፡ በዚህ መሰረት ግብረመልሱን ከተማሪዎች ቁጥርና ካለው ክፍለ ጊዜ ጥበት አንጻር አስቸጋሪ ቢሆንም ተማሪዎች የሚጽፉትን ጽሁፎች ሰብስቦ ወደ ቤት እና ወደ እስታፍ በመውሰድ ለተማሪዎች ግብረመልስ ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት አደሚያደርጉ ለናሙና የተመረጡት መምህራን አብራርተዋል፡፡ በመጨረሻም በተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃ ላይ ስለሚሰጠው ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ መምህራን እና ተማሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው መምህራን የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡ በዚህ መሰረት ፤ መ.1 ሲያብራሩ፡- መጀመሪያ መምህሩ የተማዎቹን አቅም ማወቅ አለበት፡፡ ምን ያህል ይችላሉ ፤ ወይንም ደግሞ ምን ያህል በቅተዋል በሚል እሳቤ በማለት ነው፡፡ ማለትም ተማሪዎች በራሳቸው ጽፈው ይመጣሉ ፤ ወይስ ጽፈው ሲመጡ ምን ያህል ይለማመዳሉ፣ ያውቃሉ የሚል ግንዛቤ መኖር አለበት፡፡ ምክንያቱም ጽፈው ሲመጡ ሲያዛቸው ይጽፋሉ፤ ሲያዛቸው ይጠይቃሉ፡፡ ስለዚህ የጽፈት አድማሳቸውን ለማስፋፋት መምህሩ ማዘዝ አለበት፡፡ ከርዕሱ ጋርም ይሁን ከመጽሀፉ ውጭ አቅማቸውን በሚመጥን መልኩ ልምምዶችን መርጦ መስጠት የተማሪዎችን የጽህፈት አድማስ ለማስፋት ይረዳቸዋል በማለት አብራርተዋል፡፡ በተያያዘ መልኩ ይህንኑ ሃሳብ መ.2 ሲያብራሩት፡- በየጊዜው የተማሪዎችን የእጅ ጽሑፍ መከታተል የመምህራን የዘወትር ተግባር መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በርትተው ሰርተው ማሳየት አለባቸው የሚል ሃሳብ ሰንዝርዋል፡፡ መ.3 በተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃ ላይ ስለሚሰጠው የጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ መምህራን ምን ማድረግ አለባቸው? ተማሪዎችስ? ለሚለው መጠይቅ፡- መምህራን ለተማሪዎች በማይጎዳ መልኩ የትምህርቱ ሃሳብ እነዲገባቸው በማድረግ ቀለል ያሉ ጽሁፎችን በመስጠት መጀመሪያ ማለማመድ ከዛ ቀስ ቀስ እያሉ ደግሞ የተለያዩ ጽሁፎችን በመስጠትና ስህተታቸውን እንዲያውቁ ፣እንዲያርሙና እንዲያስተካክሉ በማድረግ የተቻላቸውን እገዛ ማድረግ የመምህሩ ተግባር ነው፡፡ ተማሪዎች ደግሞ ይህንን መሰረት አድረገው ከመምህሩ የሚሰጠውን ስህተት ትኩረት ሰጥተው ከስህተታቸው እንዲማሩ ወይም ከስህተታቸው እንዲመለሱና አስተካክለው እንዲጽፉ ማድርግ የተማሪዎችን መሻሻል ያሳድጋል የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግርዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በተማሪዎች የጽሁፍ

መልመጃ ላይ ስለሚሰጠው የጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ መምህራን ምን ማድረግ አለባቸው? ተማሪዎችስ? ለሚለው መጠይቅ መ4. እንዲህ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡- ……. በመጀመሪያ ተማሪዎች ማድረግ ያለባቸው ነገር ቢኖር ለጽሁፍ ትኩረት በመስጠት እንዲጽፉ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተማሪዎቹ ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ ደግሞ የተሻለ አንባቢ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የሚጽፉት ያነበቡትን ነገር ነው፡፡ ጽሁፋቸው የሚስተካከለው ብዙ ማንበብ ሲችሉ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ላይብረሪ በመግባት የተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ጽሁፎችን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለዚህ ያነበቡትን ለመጻፍ አይቸገሩም ማለት ነው፡፡ ተማሪዎች ብዙ ካነበቡ በኋላ ብዙ እንዲጽፉ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ያዩትን የአካባቢያቸውን ሁኔታ ያነበቡትን ነገርና ገጠመኞቻቸውን እንዲጽፉ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከመምህራን ምን ይጠበቃል ለሚለው መምህራን ተማሪዎቻቸው እንዲጽፉ በትኩረት መከታተልና ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የስነ-ጽሁፍ ውድድሮችን በተማሪዎች መካከል ቢያደርጉ መልካም ይሆናል፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በሚኒሚዲያ በስነ-ጽሁፍ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ በተለያዩ ክበቦች በተለይም ሁኔታ ቢያበረታቱአቸው መልካም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የትምህርት ቤቱ አቅም በፈቀደ መጠን ተማሪዎች የጻፉትን ጽሁፍ ራሳቸው እንዲያነቡ ወይም በጓደኞቻቸው እንዲነበቡ ወይም በመቅረጸ ድምጽ እና በመሳሰሉት ተቀርጾ እንዲሰሙት ማድረግ ጥሩ ነው በማለት ሀሳባቸውን ተናግረዋል፡፡

በአጠቃላይ ሁሉም መምህራን የሚሰጡት ግብረመልስ በጊዜው እንደሚሰጥ አብራርተዋል፡፡ ክፍለ ጊዜው አናሳ ቢሆንም ካሉት የተማሪዎች ብዛት ጋር እያጣጣሙ ግብረመልሱን እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡

## 4.3 ከመጠይቅ የተገኘ የተማሪዎች መልስ

### 4.3.1 የመምህራን የግብረመልስ አይነት አተገባበር በተመለከተ ከተማሪዎች የተሰጠ ምላሽ

ከታች ሰንጠረዥ ሰባት እንደሚያሳየው መምህራን በተማሪዎች ወረቀት ላይ ግብረመልስ ሲሰጡ የሚያዘወትሩት የግብረመልስ አይነት ምንነት ለማወቅና የግብረመልስ አሰጣጣቸውን ከተማሪዎች በኩል ያለውን ምላሽ ለመፈተሽ የተጠየቁ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ይኸውም አስተካካይ ግብረመልስን፣ ትእዛዛዊ ግብረመልስ ፣ገምጋሚ ግብረመልስ እና አመቻች ግብረመልስን በተመለከተ የተጠየቁ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ ሰባት፤-የመምህራን የግብረመልስ አይነት አተገባበር

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መምህራን በተማሪዎች ወረቀት ላይ ግብረመልስ ሲሰጡ የሚያዘወትሩት የግብረመልስ አይነት የትኛው ነው? | በጣም አልስማማም | | አልስማማም | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | እስማማለሁ | | በጣምእስማማለሁ | |
| | | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % |
| ሀ | አስተካካይ ግብረመልስ | 15 | 10 | 15 | 10 | - | - | 70 | 49 | 44 | 31 |
| ለ | ትእዛዛዊ ግብረመልስ | 20 | 14 | 25 | 17 | - | - | 63 | 44 | 36 | 25 |
| ሐ | ገምጋሚ ግብረመልስ | - | - | 9 | 6 | - | - | 85 | 59 | 50 | 35 |
| መ | አመቻች ግብረመልስ | 25 | 17 | 12 | 8 | - | - | 65 | 45 | 42 | 29 |

ከታች በሰንጠረዥ ሰባት ላይ ለተጠቀሰው ጥያቄ ከተሰጡት ነጥቦች ከአልስማማም እና በጣም አልስማማም የበለጠ ለእስማማለሁ እና በጣም እስማማለሁ ለሚሉት አማራጮች በሁሉም የግብረመልስ አይነቶች ላይ ከፍተኛ  ድርሻ ለናሙና በተመረጡ ተማሪዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይኸውም ለአስተካካይ ግብረመልስ የተሰጠው 49% እስማማለሁ 31 % በጣም እስማማለሁ በድምሩ 80% ያህል ምላሽ ሲገኝለት እዛዛዊ ግብረመልስ መጠይቅ ደግሞ የተሰጠው 44% እስማማለሁ  25% በጣም እስማማለሁ ሲሆን  በድምሩ 69% ያህል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ለአመቻች ግብረመልስ 45% ለእስማማለሁ፤ 29% በጣም እስማማለሁ ለሚሉት በጠቅላላ 74% ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ለአማራጭ ገምጋሚ ግብረመልስ ጥያቄ 59% እስማማለሁ፤ 35% በጣም እስማማለሁ በድምሩ 94% ያህል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ ከትንታኔው መረዳት እንደሚቻለው በአጠቃላይ ገምጋሚ ግብረመልስ 94%፣ ለአስተካካይ ግብረመልስ 80%፤ ለተዕዛዛዊ ግብረመልስ 69 % ያህል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ገምጋሚ ግብረመልስ 94% የሚሆነው ምላሽ ከፍተኛውን መጠን ስለያዘ መምህራን አዘውትረው የሚሰጡት ግብረመልስ መሆኑን ከጽሁፍ መጠይቁ ከተሰጠው ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከተሰጡት ምላሾች እንደምንመለከተው መምህራን የተማሪዎችን ጽሁፍ በሚያርሙበት ጊዜ ገምጋሚ ግብረመልስን በከፍተኛ መጠን፣ አስተካካይና አመቻች ግብረመልስ በመጠኑ እደሚተገብሩ የተማሪዎች መልስ በግልጽ ያሳያል፡

### 4.3.2 የመምህራንን የግብረመልስ አይነት አተገባበር በተመለከተ ተማሪዎች ለጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት መረጃ

ግብረመልስ አይነት አተገባበር በተመለከተ በተማሪዎች የጽሑፍ ስራ ላይ እንዴትና በማን እንደሚከናወን በክለሳ ድርሳን ክፍል እንደተብራራው መምህራን ተማሪው የጻፈውን የጽህፈት ስራ በማረም ምን አይነት ስህተት እንደፈጸመ መጠቆም አለባቸው፡፡ መምህራን የተለያዩ የእርማር ስልት ተጠቅመው የግብረመልስ ይሰጣሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ርዕስ ስር ግብረመልሱ በማንና እንዴት እንደሚሰጡ እንመለከታለን፡፡

**ሰንጠረዥ ስምንት፡የመምህራን የግብረመልስ አይነት አተገባበር በተመለከተ ተማሪዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት መረጃ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም አልስማማም | | አልስማማም | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | እስማማለሁ | | በጣምእስማማለሁ | |
| | | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % |
| 1. | በምጽፋቸው ጽሁፎች ውስጥ የፈጸምኳቸውን ስህተቶች መምህሬ አስተካክለው በመጻፍ ግብረመልስ ይሰጡኛል (ያርሙልኛል)፡፡መምህሬ የሚሰጡት ጽሁፎች ሁሉ ይታረማሉ፡፡ | 0 | 0 | 5 | 3.5 | 2 | 1.4 | 120 | 83.3 | 17 | 11.8 |
| 2. | በምጽፋቸው ጽሁፎች ላይ ስህተቴን ራሴ ፈልጌ እንዳስተካክል መምህሬ ትዕዛዝ በመስጠት ያግዙኛል፡፡ (መምህሬ ከጽሁፌ ውስጥ የተሳሳተውን አስተካክለው ያሳዩኛል)፡፡ | 0 | | 0 | 0 | 0 | | 95 | 66 | 49 | 34 |
| 3 | መምህሬ በእያንዳን ዱጽሁፌ ላይ ምንም አይነት አስተያየት ሳይሰጡኝ ውጤት ብቻ ያስቀምጡልኛል፡፡ | 24 | 17 | 75 | 52 | | | 30 | 21 | 15 | 10 |
| 4 | በጽሁፌ ላይ የፈጸምኳቸውን ስህቶች መምህሬ በጥያቄና በአስተያየት መልክ ይጠቁሙኛል፡፡ (የሚሰጠኝ የግብረመልስ አሰጣጥ አይነት የተለያየ ነው)፡፡ | 14 | 10 | 10 | 7 | | | 80 | 56 | 35 | 24 |

ከላይ ሰንጠረዥ ስምንት እንደሚያሳየው የመምህራን የግብረመልስ አይነት አተገባበር በተመለከተ ለተማሪዎች የግብረመልስ ሲሰጡ እንዴት እንደሆነ እና ምን አይነት ምላሽ ለማወቅና የግብረመልስ ትግበራ አሰጣጣቸውን ለመፈተሽ የተጠየቁ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ይኸውም ለተ.ቁ 1 የተሰጠው 83.3% “እስማማለሁ” 11.8 % “በጣም እስማማለሁ” በድምሩ 95.1% ያህል ምላሽ ሲገኝ ለመጠይቅ ተ.ቁ 2 ደግሞ የተሰጠው 66% “እስማማለሁ”፣ 34% “በጣም እስማማለሁ” በድምሩ 100% ያህል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም ለጥያቄ ቁጥር 317% በጣም አልስማማም፤ 52% በጣም አልስማማም ፤ በድምሩ 69% ያህል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ለተራ ቁጥር 4 56% “እስማማለሁ”፣ 24% በጣም እስማማለሁ ሲሆን በጠቅላላ 80% የሚሉ እንደተገኙ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ለጥያቄ ቁጥር 2 ማለትም መምህሬ በምጽፋቸው ጽሁፎች ላይ ስህተቴን ራሴ ፈልጌ እንዳስተካክል ትዕዛዝ በመስጠት ያግዙኛል (መምህሬ ከጽሁፌ ውስጥ የተሳሳተውን አስተካክለው ያሳዩኛል) የሚለው ከፍተኛውን የድርሻ መጠን ስለያዘ መምህራን አዘውትረው የሚሰጡት ግብረመልስ አተግባበር መሆኑን ከጽሁፍ መጠይቁ ከተሰጠው ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመቀጠል ከተሰጡት ምላሾች እንደምንመለከተው መምህራን የተማሪዎችን ጽሁፍ በሚያርሙበት ጊዜ ተማሪው በሚጽፋቸው ጽሁፎች ውስጥ የፈጸማቸውን ስህተቶች በመምህሩ እገዛ  አስተካክለው በመጻፍ ግብረመልስ ይሰጡኛል (ያርሙልኛል) እንዲሁም መምህራን  የሚሰጡት ጽሁፎች ሁሉ ይታረማሉ የሚለው በሁለተኛነት ደረጃ በመምህራን ይተገበራል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን ገምጋሚ ግብረመልስን በትግበራ ወቅትም እንደሚያዘወትሩ ከጽሀፍ መጠይቁ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ መረጃ ከሰነድ ፍተሻው ከተገኘው መረጃ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይኸውም የሰነድ ፍተሻው ተተንትኖ እንደታየው መምህራን ገምጋሚ ግብረመልስን በአብዛኛው እንደሚያዘወትሩ ለማረጋጋጥ ተችሏል፡፡

መምህራን በገምጋሚ ግብረመልስ አይነት ብቻ ትኩረት እንደማያደርጉ እና ሌሎችንም የግብረመልስ አይነቶች እንደሚጠቀሙ ከቃለ መጠይቁ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ ደጋፊ ሁኖ ከገባው ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ገምጋሚ ግብረመልስን እንደሚያዘወትሩ ሲያጠናክረው በአንጻሩ ግን ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ መምህራን በአንዱ የግብረመልስ አይነት ብቻ ትኩረት እንደማያደርጉ፤ ሁሉንም አይነቶች እንደ አስፈላጊነታቸው እንደሚጠቀሙ የሚል መልዕክት ስላለው ከሰነድ ፍተሻውና ከጽሁፍ መጠይቆች የተገኘው መረጃ ከቃለ መጠይቁ ከተገኘው መረጃ ጋር አይመሳሰልም፡፡ በአጠቃላይ ከጽሁፍ መጠይቅና ከሰነድ ፍተሻው በተገኘው መረጃ አማካኝነት መምህራን ገምጋሚ የግብረመልስ አይነትን በግንባር ቀደምትነት የሚተገብሩ ሲሆን ትዕዛዛዊን፣

አመቻችንና፣አስተካካይን ደግሞ በተከታታይነት የሚተገብሯቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ውጤትን ብቻ በዋነኝነት መስጠት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ በማሻሻል በኩል ያለውን አስተዋጽኦ አነስተኛ ስለሆነ መምህራን በአብዛኛው ገምጋሚ የግብረመልስ አይነት መተግበራቸው ተገቢ አለመሆኑን በተገኙት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.3.3 ከጽሁፋዊ ግብረመልስ ስልቶች አንጻር ከተማሪዎች መጠይቅ የተወሰደ ምላሽ

የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶችን በተመለከተ በጥናቱ ክለሳ ድርሳን ክፍል ስር እንደቀረበው ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት፣ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት እና ጠቋሚ የአስተራረም ስልት መሆናቸውን ተገልጿል፡፡ እያንዳንዱ መምህር በሶስት ተከታታይ የተማሪ ጽሁፎች ላይ በተናጠል የግብረመልስ ስልቶችን እንደተጠቀሙ ለመጠቆም እና እነዚህን የግብረመልስ ስልቶችን ደጋግመው መጠቀማቸውን ለማመልከት ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ለተማሪዎች በመጠይቅ ከቀረበ ምላሽ ጋር ለማገናዘብ ያክል በቁጥርና በመቶኛ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ተገልጿል፡፡ ዝርዝር ትንተናውም እንዳስፈላጊነቱ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡

**ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡-የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶችን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣምአልስማማም | | አልስማማም | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | እስማማለሁ | | በጣምእስማማለሁ | |
| | | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % |
| | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ ልረዳቸው የማልችለውን ምልክቶች በመጠቀም ግብረመልስ አዘውትረው ይሰጡኛል (ግብረመልስ በጊዜው ይደረጋል)፡፡ | 30 | 21 | 35 | 24 | 4 | 3 | 75 | 52 | - | - |
| 2 | መምህሬ በጽሁፌ ላይ የሚታዩብኝን ስህተቶች በሙሉ ያርሙልኛል (መምህሬ በጽሁፌ ላይ ያሉትን ስህተቶች | 12 | 8 | 25 | 17 | - | - | 57 | 40 | 50 | 35 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ይጠቁሙኛል)፡፡ | | | | | | | | | | |
| 3. | መምህሬ በጽሁፌ ላይ ከሚታዩትን ስህተቶች ውስጥ የተወሰኑትን መርጠው ያርሙልኛል (ከስህተቴ ውስጥ ጥቂቱን ብቻ ያሳዩኛል)፡፡ | 18 | 13 | 22 | 15 | - | - | 75 | 52 | 29 | 20 |

ከላይ ከሰንጠረዥ ዘጠኝ መመልከት እንደሚቻለው መምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ ግብረመልስ ለመስጠት የሚያግዛቸው የግብረመልስ ስልቶችን በተመለከተ የቀረቡ መጠይቆች ናቸው፡፡ ይኸውም ተራ ቁጥር 1 ጠቋሚ የአስተራረም ስልት (ምልክቶችን በመጠቀም በተማሪ ጽሁፎች ላይ ስህተትን መጠቆም)፣ ተራ ቁጥር 2 ሁሉን ምስህተቶች የማረም ስልት እና ተራ ቁጥር 3 ስህተቶችን መርጦ የማርም ስልትን ይወክላሉ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ጥያቄዎች መምህራን በግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶች አጠቃቀማቸው ምን እንደሚመስል ለማወቅ የተጠየቁ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ስለሆነም በተራ ቁጥር 1 የተገለጸው ሃሳብ መምህራን በተማሪዎች ጽሁፎች ላይ እርማት ሲያካሄዱ ተማሪዎች ሊረዱት የማይችሏቸውን ምልክቶች መጠቀማቸውን በተመለከተ ሲገልጹ 3% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 52% የሚሆኑት አስማማለሁ እና 21% የሚሆኑት በጣም አልስማማም፤ 24% አልስማማም የሚሉ ሲሆኑ፤ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው በ52% እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች በጽሁፋቸው ውስጥ ለፈጸሟቸው ስህተቶች መረዳት እንዲችሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች ሊረዷቸው የማይችሉትን ምልክቶች በመጠቀም ግብረመልስ አዘውትረው ይሰጣሉ (ግብረመልስ በጊዜው ይደረጋል)፡፡ መምህራን ምልክቶች እንደሚጠቀሙ በቁጥር ላቅ ወይንም በግማሽ በዛ ያሉ ተማሪዎች ገልጸዋል፡፡

በተራ ቁጥር 2 የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ መምህራን ስህተቶችን በሙሉ መርጠው ለማረማቸው 40% እስማማለሁ 35% በጣም እስማማለሁ በድምሩ 75% ሲሆን ፣ 17% አልስማማም 8% በጭራሽ አልስማማም ያሉት በድምሩ 25% ከመቶኛ መልሰዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብላጫውን ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ማለትም 75% ያህሉ መምህራን ስህተቶችን በሙሉ መርጠው ማረማቸውን ከተማሪዎች ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በጽሁፍ መጠይቅ በተራ ቁጥር 3 የተገለጸው ሀሳብ መምህሬ በጽሁፌ ላይ

የሚታየውን ስህተቶች በከፊል መርጠው ያርሙልኛል ብለው በጣም የተስማሙት 20%፣ እስማማለሁ ያሉት 52% በድምሩ 72% ሲሆን፤ 15%፣ አልስማማም፤ 13% በጣም አልስማማም ያሉት በድምሩ 28% ያህሉ ናቸው፡፡ አብላጫውን ምላሽ የሰጡት ማለትም 72% ያህል ተማሪዎች መምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ ከሚታዩ ስህተቶች ውስጥ የተወሰኑትን መርጠው ወይንም ከስህተቶቻቸው ውስጥ ጥቂቱን ብቻ እንደሚያርሙ ገልጸዋል፡፡

በድጋሜ ደጋፊ ሆኖ ከቀረበው ከመምህራን ቃለ መጠይቅ እና የሰነድ ፍተሻ የተገኘው ምላሽ ማለትም የጽሁፋዊ ግብረመልስ ስልቶችን በተመለከተ ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ ለምሳሌ በቁጥር 3 የተማሪዎችን የጽሁፍ ስራ በሚያርሙበት ጊዜ የሚጠቀሙት ስልት በመ.1፣ መ.3 እና መ.4 ሲጠቀስ በመጀመሪያ ምልክትን በመጠቀም ምላሽ እሰጣለሁ ሲሉ በተለይም መ.3 "የጎላ ስህተት ሲያጋጥመኝ ምልክት በመጠቀም እርማት እሰጣለሁ" በማለት ሁለቱን ስልቶች አጣምረው መጠቀማቸውን እግረ መንገዳቸውን ተናግረዋል፡፡ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ምልክቶች መጠቀማቸውን መግለጻቸውን እንጂ የትኛው ምልክት ለየትኛው ስህተት እንደተወከለ እንደማይገልጹ መረጃው ያስረዳል፡፡

በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ እንዳንዱን (ሁሉንም) ስህተት ተቆጣጥረው አዘውትረው አርመው እንደማያውቁ መምህራን አበክርው ሲጠቅሱ ለዚህም ያቀረቡት ምክንያት ህተቶችን ለቅሞና አውጥቶ ማረም ከተማሪው ቁጥር መብዛትና ከምንገባበት የሴክሽን ቁጥር መብዛት አዳጋች ስለሆነ ያን ያህል በዚህ ስልት ትኩረት አናደርግም የሚል ተቀራራቢ ምላሽ ከሁሉም መምህራን ተገኝቷል፡፡ በዚህ አጋጣሚ የተማሪው ቁጥር መብዛትና የሚገባበት የሴክሽን ቁጥር መብዛት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ሁልጊዜ እንዳይሰጥ ተጽዕኖ አድራሽ አካል መሆኑን እግረ መንገዱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የጽሁፋዊ ግብረመልስ ስልቶችን በተመለከተ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ መምህራን በአብዛኛው ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልትንና ጠቋሚ የአስተራረም ስልትን እንደሚያዘወትሩ፣ ጠቋሚ የአስተራረም ስልትን ቢጠቀሙም ምልክቶችን መጠቀማቸውን እንጂ ለተማሪዎች ይረዱታል አይረዱትም የሚለውን ከግምት ውስጥ እንደማያስገቡ እና ሁሉንም ስህተት የማረም ስልትን እንደማያዘትሩ ከትንተናው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻው፣ ከጽሁፍ መጠይቁ እና ከቃለ መጠይቁ ለመረዳት እንደተሞከረው መምህራን ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልትን አዘውትረው አንደሚጠቀሙ፣ ይህ ደግሞ መምህራን ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልትን አዘውትረው

መጠቀማቸው ለተማሪዎች የጽሁፍ ችሎታ መዳበር አስተዋጽኦ አለው፡፡ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት ተማሪዎች በጽሁፋቸው ላይ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የቋንቋውን መማር ማስተማር ሂደት የሚያደናቅፍ ስህተቶች ላይ ብቻ እንደሚሰጥና የመምህሩን የስራ ጫና ለመቀነስና በተማሪዎች ላይ የሚፈጥረውን የተስፋ መቁረጥ ስሜት እንዲቀርፍ ማስቻሉን ለመረዳት ይቻላል፡፡

### 4.3.4 የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ባህሪያት በተማሪዎች እይታ

የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ባህሪያትን በተመለከተ በክለሳ ድርሳን ክፍል ስር እንደተገለጸው ተማሪዎች ጥሩ ጽሑፍ ከጻፉ ጥሩ ምላሽ ሲሰጣቸው ነገር ግን የጽሑፍ ስራቸው ጥሩ ካልሆነ የሚሰጣቸው እርማት ጥሩ ምላሽ አይሆንም፡፡ እነዚህን የግብረመልስ አይነቶች አዎንታዊና አሉታዊ የግብረመልስ ባህሪያት ብለን በሁለት እንከፍላቸዋለን፡፡ በዚህ ርዕስ ስር ለተማሪዎች የጽሁፍ ስራ መዳበር ስህተታቸውን የሚጠቅም የግብረመልስ መሰጠቱን እንመለከታለን፡፡

**ሰንጠረዥ አስር ፦የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ባህሪያት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም አልስማማም | | አልስማማም | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | እስማማለሁ | | በጣምእስማማለሁ | |
| | | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % | በ.ቁ | % |
| 1. | መምህሬ በአብዛኛው በጽሁፌ ላይ ደካማ ጎኔን በተመለከተ ግብረመልስ ይሰጡኛል፡፡ መምህሬ በደካማ ጎኔ ብቻ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ይሰጡኛል፡፡ | 34 | 24 | - | - | 12 | 8 | 73 | 51 | 25 | 17 |
| 2. | የሚሰጠኝ ግብረመልስ በቀጣይ የተለያዩ ጽሑፎችን እንድጽፍ የሚያግዝ አዎንታዊ የሆነ ግብረመልስ የሚታይበት ነው፡፡ መምህሬ በተለየየ ዘዴ ግብረመልስ ይሰጡኛል፡፡ | 19 | 13 | 18 | 13 | 22 | 15 | 85 | 59 | - | - |
| 3 | መምህሬ የሚሰጡኝ ግብረመልስ አይገባኝም (ግልጽ አይደለም)፡፡ | 65 | 45 | 56 | 39 | 23 | 16 | - | - | - | - |

ከላይ ከሰንጠረዥ አስር መረዳት እንደሚቻለው ለናሙና ከተወሰዱ የተማሪ የመጠይቅ ምላሽ ውስጥ ጠቅላላ ከሰጡት አዎንታዊ ባህሪን ከያዘ ጥያቄ ቁ.1 ላይ መምህሬ በአብዛኛው በጽሁፌ ላይ ደካማ ጎኔን በተመለከተ ግብረመልስ ይሰጡኛል ለሚለው 51% እስማማለሁ፣ 17% መጣም እስማማለሁ፤ በድምሩ 68% ያህሉ ተማሪዎች ምላሽ ሰጥተዋል። እንዲሁም ጠቅላላ ከሰጡት ምላሽ 24% መጣም አልስማማም ሲሉ 8% ለመወሰን እቸገራለሁ የሚል ምላሽ መልሰዋል። በተመሳሳይ ለጥያቄ ቁጥር 2 ከመምህሬ የሚሰጠኝ ግብረመልስ በቀጣይ የተለያዩ ጽሁፎችን እንድጽፍ የሚያግዝ አዎንታዊ የሆነ ግብረመልስ የሚታይበት ነው ለሚለው ጥያቄ 59% እስማማለሁ፤ 13% በተመሳሳይ መልኩ በጣም አልስማማም እና አልስማማም በድምሩ 26% ያክል ሲመልሱ15% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል። በተጨማሪም በጥያቄ ቁጥር3 ላይ መምህሬ የሚሰጡኝ ግብረመልስ አይገባኝም (ግልጽአይደለም) ለሚለው መጠይቅ 45% ያህሉ በጣም አልስማማም፤ 39% አልስማማም በድምሩ 84% ያህሉ እንደማይስማሙ ገልጸዋል። በአጠቃላይ ሁለቱንም ጥያቄዎች ስናወዳድር መምህራን ለተማሪዎቻቸው በ68% በጽሁፎቻቸው ላይ ያለውን ደካማ ጎን በተመለከተ ግብረመልስ እንደሚሰጡ ያመላክታል። በተጨማሪም ይህ የሚያመለክተው መምህራን በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ሲሰጡ ከአሉታዊ ግብረመልስ ይልቅ አዎንታዊ ግብረመልስ እንደሚያዘወትሩ ከፍተሻ ሰነዱ ለማረጋገጥ ተችሏል።

የግብረመልስ መግለጫ ባህሪን በሚመለከት አብዛኛዎቹ መምህራን ለጥሩ ጽሁፍ አዎንታዊነት የተላበሰ ግብረመልስ እንደሚሰጡ፣ ጥሩ ለማይባል ጽሁፍ ደግሞ አሉታዊ ግብረመልስ እነደሚሰጡ እነዲሁም አሉታዊና አዎንታዊ ለማለት የተማሪው የጽሁፍ ችሎታ እንደሚወስናቸው ከቃለ መጠይቁ ለማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ መምህራን ሁለቱንም ባህሪያት እንደ አስፈላጊነታቸው ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ይጠቀማሉ ማለት ነው። በአጠቃላይ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ መምህራን አዎንታዊና አሉታዊ ግብረመልስ አመጣጥነው መጠቀማቸውን የሚገልጽ ቢሆንም ከሰነድ ፍተሻው እና ከጽሁፍ መጠይቁ የመረጃ ትንተና ለማረጋገጥ የተቻለው ግን መምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ ሲሰጡ አዎንታዊ ግብረመልስ እንደሚያዘወትሩ ነው።

### 4.3.5 ግብረመልስ ከጊዜ፣ ከመጠንና ከግልጽነት አንጻር

ግብረመልስ ሲሰጥ የትምህርቱን ዓላማና ግብ መሰረት አድርጎ፣ ተመጥኖና ግልጽ ሆኖ መስጠት እንዳለበት፣ ግብረመልስ የተሰጠበት ወረቀት (ደብተር) ከጊዜ አንጻር በቶሎ

መመለስ እንዳለበት በክለሳ ድርሳኑ ላይ መገለጹ ይወታሳል፡፡ ስለሆነም የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የመምህራን የግብረመልስ አሰጣጣቸው ከጊዜ፣ ከመጠንና ከግልጽነት አንጻር ምን እንደሚመስል በሚከተለው መረጃ ማየት ይቻላል፡፡

**ሰንጠረዥ አስራ አንድ፡- አጠቃላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጣቸውን የሚያሳይ**

<table>
<tr><th rowspan="3">ተ.ቁ</th><th rowspan="3">ጥያቄዎች</th><th colspan="10">አማራጮች</th></tr>
<tr><th colspan="2">በጣም አልስማማም</th><th colspan="2">አልስማማም</th><th colspan="2">ለመወሰን እቸገራለሁ</th><th colspan="2">እስማማለሁ</th><th colspan="2">በጣም እስማማለሁ</th></tr>
<tr><th>በ.ቁ</th><th>%</th><th>በ.ቁ</th><th>%</th><th>በ.ቁ</th><th>%</th><th>በ.ቁ</th><th>%</th><th>በ.ቁ</th><th>%</th></tr>
<tr><td>1</td><td>የምጽፋቸው ጽሁፎች በጊዜ ታርመው ተመልሰውልኝ አያውቁም (ምህሬ ጽሁፋ ዊግብረመልስ አይሰጡኝም ነጥብ ብቻ ወይም ማርክ ይጽፋሉ)፡፡</td><td>62</td><td>43</td><td>82</td><td>57</td><td>-</td><td>-</td><td>-</td><td>-</td><td>-</td><td>-</td></tr>
<tr><td>2</td><td>በጽሑፌ ላይ በመጠን ብዙ የሆነ ግብረመልስ ይሰጠኛል (መምህሬ ከጽሁፋዊ ግብረመልስ ፋንታ በቃል አስተያየት ይሰጡኛል)፡፡</td><td>45</td><td>31</td><td>35</td><td>24</td><td>-</td><td>-</td><td>64</td><td>44</td><td>-</td><td>-</td></tr>
<tr><td>3.</td><td>መምህሬ ግልጽ ያልሆነ ግብረመልስ አዘውትረው ይሰጡኛል (መምህሬ በጽሁፌ ውስጥ ስህተቴን እራሴ እንዳርም ያደርጉኛል)፡፡</td><td>43</td><td>30</td><td>89</td><td>62</td><td>12</td><td>8</td><td>-</td><td>-</td><td>-</td><td>-</td></tr>
<tr><td>4</td><td>መምህሬ ግብረመልስን እርስ በእርስ (ከተማሪዎች ጋር ) እንዳደርግ ያዙኛል፡፡</td><td>62</td><td>43</td><td>82</td><td>57</td><td>-</td><td>--</td><td>-</td><td>-</td><td>-</td><td>-</td></tr>
</table>

ከሰንጠረዥ አስራ አንድ እንደምንረዳው በተዘርዘሩት ወይንም የተገለጹት መጠይቆች ግብረመልስ ተሰጥቶ የሚመለስበት ጊዜ፣ የግብረመልሱ መጠንና የግብረመልሱ ግልጽነትን የሚያመላክቱ ሀሳቦች ናቸው፡፡ በተራቁ ጥር 1 የቀረበው የጻፍኩት ጽሁፍ በጊዜ ታርሞ

ተመልሶልኝ አያውቅም ለሚለው መጠየቅ 57% አልስማማም እና 43 % በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ይህም የሚያመለክተው መምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከሰጡ በኋላ በጊዜ እንደሚመለሱ ነው፡፡ በተራ ቁጥር 2 የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው በጽሁፌ ላይ በመጠን ብዙ የሆነ ግብረመልስ ይሰጡኛል ለሚለው 44% የሚሆኑት እንደሚስማሙ፤ 55% እንደማይስማሙ ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ መምህራን ከመጠን ያለፈ ጽሑፋዊ ግብረመልስ በተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላይ እንደማይሰጡ ከጽሁፍ መጠይቁ ብቻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተራ ቁጥር 3 የተገለጸው መጠይቅ ደግሞ መምህሬ ግልጽ ያልሆነ ግብረመልስ ይሰጡኛል የሚል ሲሆን የተማሪዎች የምላሽ መጠን እንደሚከተለው ነው፡፡ በድምሩ 92% ማለትም 30%ቱ በጭራሽ እንዳልተስማሙ እና 62%ቱ እንደማይስማሙ፣ 8%ቱ ለመወሰን እንደሚቸገሩ ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም ይህ መረጃ ተማሪዎች በመምህራን ግልጽ ያልሆነ ግብረመልስ ተሰጥቷቸው እንደማያውቅ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ መልኩ ይህ ማለት በተማሪዎች ጽሁፎች ላይ የሚሰጠው ግብረመልስ ተማሪዎች የጽሁፋቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን እንዲለዩ ግልጽና ሊታይ በሚችል መልኩ መገለጽ አለበት ተብሎ ከሚገለጹት ሃሳቦች ጋር የሚመሳሰል እንደሆነ ያመላክታል፡፡

ጥያቄ 4ን በተመለከተ መምህሬ ግብረመልስን እርስ በእርስ (ከተማሪዎች ጋር ) እንዳደርግ ያዙኛል፡፡ 43% በጣም አልስማማም፤ 57% አልስማማም በማለት መልስ ሲመልሱ፤ የተማሪዎች በክፍል ውስጥ በብዛት መመደብ እና የመማሪያ ክፍሎች ብዛት ይህንን እንዳይተገብሩ ያደርጋቸዋል ለማለት ያስችላል፡፡ በመጨረሻም ለተማሪዎች የቀረበው ክፍት ጥያቄ በአጠቃላይ ከመምህራቸው ስለሚሰጣቸው ጽሁፋዊ ግብረመልስ ያላቸውን አስተያየት እንዲገልጹ የሚያደርግ ነው፡፡ ለዚህም የሰጡት አስያየት ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የተወሰኑት ከታረመልኝ ሌላውን ነገር አያስተካክሉልኝም፤ በአንድ ላይ ርዕስ ከጻፍን በኋላ ያንን ሳንጨርስ ሌላ እንድንጽፍ እንታዘዛለን፡፡ ስለሆነም የመጀመሪያው ታርሞ ከዛ ሌላ የሚጻፍ ቢሰጠን መልካም ነው፤ መምህሬ በጽሁፌ ላይ የሚያርሙልኝ በጣም ጥሩ የሆነና ከዚያም በኋላ ለምን ጽፌው ጽሁፍ እውቀት እንዲኖረኝ የሚያደርግ ነው፤ መምህሬ ብዙ ጊዜ ጥሩ የሚባል ጽሁፍ ጽፌ ጭራሽ በዚህ መልክ መጻፍ የለበትም ብለው ልፋቴን ውድቅ ያደርጉታል፤ የአስተሳሰብ አድማሳችን እንዲሰፋ ያደርጋል፤ የቃላት ግድፈት እና የዓረፍተ ነገር አወቃቀር አመሰራረት ስለሚያሳዩን እውቀት እንዲኖረኝ አድርጎልኛል፤ ጥሩ የሚባል ጽሑፍ ብጽፍም ባልጽፍም ጥሩ የሚባል ውጤት አይሰጡኝም፤ እና በአብዛኛው እንድንጽፍ ቢደረግም የሚታረምልን

ግን አልፎ አልፎ ነው፡፡ ስለዚህ የምንጽፈው ጽሁፍ ሁሌ ቢታረምልን ጥሩ ነው፡፡ የማያርሙልን ከሆነ ለምን ያስጽፉናል? የሚሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች በመምህራን የሚሰጣቸው ጽሁፋዊ ግብረመልስ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳለ የገለጹ ቢኖሩም በአንጻሩ ደግሞ በጥሩ ሁኔታ ላይ እደሌለ የገለጹም አሉ፡፡ ይኸውም ለመምህራን በቀረበ ቃለ መጠይቅ አማካኝነት ሁሉም መምህራን አርመው ቶሎ እንደሚመልሱ ቃላዊ ምላሽ ሰጥተው ነበር፡፡ ነገር ግን ከተማሪዎች አስተያየት ለመመልከት እንደተሞከረው “በአንድ ጉዳይ ጽፈን ሳንጨርስ ሌላ እንድንጽፍ እንታዘዛለን፡፡” የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ መምህራን የመጀመሪያውን ጽሁፍ አርመው ሳይመልሱ ሌላ የጽሁፍ ስራ መስጠታቸው ከመጀመሪያው ስህተት ምንም ሳይማሩ በሁለተኛው የጽሁፍ ስራቸው ላይ ሌላ ስህተት እንዲሰሩ እድል ይከፍቱላቸዋል ማለት ነው፡፡ እንዲሁም መምህራን የተማሪዎችን የጽሁፍ ስህተት የተወሰነውን ካረሙ ሌሎችን ስህተቶች ትኩረት እንደማይሰጡ ከተማሪዎች አስተያት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጻፏቸው ጽሁፎች ላይ መምህራን የሰጧቸውን ግብረመልሶችን መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ግብረመልስ የተሰጠባቸው የተማሪ ጽሑፎች፣ ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅና ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሆነው አገልግለዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ ከላይ ጽሁፋቸው ለተሰበሰበው ተማሪዎች በመበተን መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በዚህ መሰረት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ተማሪዎች በሚጽፏቸው ጽሁፎች የሚታዩ ስህተቶች የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረመልስ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ የተሞከረ ሲሆን መምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ የሚታዩትን ስህተቶች በምን በምን እንደሚያተኩሩ፣ ምን አይነት የግብረመልስ ስልት እንደሚጠቀሙ፣ ምን አይነት የግብረመልስ አይነትን እንደሚተገብሩ እንዲሁም አጠቃላይ የመምህራን የጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ ትኩረት፣ ባህሪ እና አቀራረብ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል፡፡

በመሆኑም የመምህራን ግብረመልስ አሰጣጥ ስልትን፣ የሚጠቀሙባቸውን የግብረመልስ አይነቶችን፣ የግብረመልስ የትኩረት አቅጣጫ እና ባህሪ ለማወቅ ግብረመልስ ከተሰጠባቸው የተማሪዎች ጽሁፎች፣ በተማሪዎች ከተሞሉ የጽሁፍ መጠይቆች እና ከመምህራን ጋር ከተደረገው ቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ አመች ተብሎ በተመረጠ የምርምር ዘዴ በመጠቀም በጥናቱ ዓላማ መሰረት ተተንትነዋል፡ ፡ በአጠቃላይ ከትንተናው የተገኘው ውጤቱ እንደሚያመለክተው በተደርገው ጥናት መሰረት በይዘታቸው መልካምና ሊሻሻሉ የሚገባቸው የመማር ማስተማር ችግሮች አጥጋቢ በሆነ ትንታኔ ሊዳሰሱ ችለዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል ከመልካም ተግባራቶች እና ክንውኖች ብንነሳ፡-

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ አራቱን ክሂሎች ለተማሪዎቻቸው ለማስተማር ያሳዩት ትጋት እጅግ ሊበረታታ የሚገባውና ከሚመለከተው የመማር ማስተማር የስራ ሂደት ኃላፊዎች የማበረታቻ እና የማበልጸጊያ ተግባሮች በተከታታይ ሊሰጥ እንደሚገባ ከጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

2. መምህራን በተማሪዎቻቸው ላይ የሚተገብሩት የቁጥጥርና የክትትል ስልት፣ የጊዜ አጠቃቀም፣ መርዳት፣ የማደራጀት፣ የማለማመድ፣ የግብረ መልስ አሰጣጥ፣ የሰነድ ፍተሻ እርማት በጊዜ ላይ ያተኮረ ምላሽ ወይንም ማስተካከያ መስጠት፣ የተለያዩ ግብረመልስ ስልቶችን በተግባር ላይ ማዋል እና ለተማሪዎቻቸው የሚያሳዩት የስነ ምግባር ክንውኖች ሊበረታቱ እንደሚገባ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

3. ምንም እንኳን የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በሳምንት የተመደበው የትምህርት ክፍለ ጊዜ አናሳ ቢሆንም፤ መምህራን በእረፍት ቀናቸው የማካካሻ የመማር ማስተማር ክፍተትን ለመሸፈን የሚያደርጉት ጥረት የተማሪዎችን የመጻፍ እና የማንበብ ችሎታ ከማገዙም በተጨማሪም በዓመት የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ለማጠቃለል እንደሚጠቅማቸው ከመምህራንና ተማሪዎች ምላሽ የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡

በተጨማሪም ግብረመልስን በታቀደው መሰረት እንዳይከወን እንደ ችግር የተነሱ እና መሻሻል የሚገባቸው ነገሮች፡-

1. በሳምንት አናሳ የሆነ የክፍለ ጊዜ ምደባ፤
2. በአንድ ክፍል ውስጥ በቁጥር ከፍተኛ የሆነ የተማሪዎች ምደባ፤
3. አማርኛ ቋንቋ ለተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ መሆኑ እና ለመማር ፍላጎት ማነስ ባህሪ መታየት፤
4. መምህራን ሁሉንም የግብረመልስ ዘዴዎች ያለመጠቀም ችግር፤
5. ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚሰጣቸውን የቤት ስራ ተመላልሰው አለመመልከት፤ አራቱን ከሂሎች የማቀናጀት ችግር፤
6. ግብረመልሱ ውጤታማ እንዳይሆን  በጊዜው አለመስጠት፤

7.ተማሪዎች ማስተካከል ያለባቸውን ነገር ቢጠቆም ጥሩ ነው፡፡

እንደ ማጠቃለያ ይረዳ ዘንድ የሚከተሉት ዋና ዋና የጥናቱ ውጤቶች ቀርበዋል፡-

- ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት እንደተቻለው የግብረመልስ አይነቶችን አስመልክቶ ከሰነድ ፍተሻና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደ ሚያመለክተው መምህራን ከሌሎቹ የግብረመልስ አይነቶች ወይንም ዘዴዎች ገምጋሚ

ግብረመልስን እንደሚያዘወትሩ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን የዚህ ግብረመልስ አይነት ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር በመጨረሻ አማራጭነት የሚወሰድ መሆኑን ምሁራን አብራርተዋል፡፡ ስለዚህ የመምህራኑ የግብረመልስ አይነት አጠቃቀም ሁሉንም አይነት ያካተተ አለመሆኑን እና ወደ አንዱ አይነት ያደላ ስለሆነ ግብረመልሱ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ውጤታማ እንዲሆን የተጠበቀውን የመማር ማስተማር ሂደት ሙሉ አያደርገውም፡፡

- በተጨማሪም መምህራን የሚያዘወትሩትን የግብረመልስ ስልቶችን አስመልክቶ ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ የሚያሳየው አብዛኛውን ጊዜ የተማሪዎችን ስህተቶች የማረም ስልት እንደሆነ እንዲሁም መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልትን ይተግብሩ እንጂ ስህተቶችን መርጠው ሲያርሙ ጠቋሚ የአስተራረም ስልትን በማዛመድ እንደሚጠቀሙ የተሰበሰቡት መረጃዎች እና መምህራን በምክንያትነት ያቀረቡት የተማሪው ቁጥር መብዛት መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡
- የተሰበሰበው መረጃ ትንተና እንደሚያሳየው መምህራን በግንባር ቀደምትነት ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት አስከትሎም ጠቋሚ የአስተራረም ስልትን በመጨረሻም ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልትን እንደሚጠቀሙ ለመገንዘብ እና ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- በሌላ መልኩ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ጽሁፍ ለማረም እንዲረዳቸው የሚሰጧቸው ግብረመልሶች አዎንታዊነት እና አሉታዊነትን ባህሪ እንዳላቸው ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት የተቻለ ቢሆንም አሉታዊነት ባህሪ ያላቸውን ግብረመልሶች መገልገላቸውን በፍተሻው እና በጽሁፍ መጠይቁ በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ቢቻልም ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ያሳድገዋል ብሎ ሙሉ በሙሉ ለመደምደም አያስችልም፡፡
- የመምህራን የግብረመልስ የትኩረት አቅጣጫን በተመለከተ የትንተናው ውጤት እንደሚያመለክተው መምህራን በጽሁፍ ይዘት እና በቋንቋው ቅርጽ ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ መስጠታቸውን የሚያመለክት ከፍተኛ ውጤት ከሰነድ ፍተሻና ከጽሁፍ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ መምህራን ለዚህ ያቀረቡት ምክንያት ይዘትንም ቅርጽንም መሰረት ተደርጎ የሚሰጥ ግብረመልስ የተማሪዎች የጽሁፍ ክሂል እንዲዳብር እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲሻሻልላቸው የሚያደርግላቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡
- በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ የሚሰጠው ግብረመልስ ከትምህርቱ ዓላማ እና ግብ

አንጻር ስለሚከወን በመጠን ደረጃ መልካም የሚባል ግብረመልስ በመምህራን እንደሚሰጥ ከመረጃ ትንተናው የተገኘው ውጤት ያመላክታል፡፡

- ግብረመልስ ተማሪዎች ሊረዱት በሚችሉት እና ግልጽነት በተሞላበት መልኩ አስተያየት እንደሚሰጡ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

➢ ግብረመልስ የተሰጠበት የተማሪዎች የጽሁፍ ወረቀት ችግር ካልተፈጠረ በስተቀር በተወሰነ መልኩ ለተማሪዎች በጊዜ እንደሚመለስላቸው የተገኙት መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ማጠቃለያዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ጠቅለል ባለመልኩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአብዛኛው ገምጋሚ ግብረመልስን መጠቀማቸው፣ እንዲሁም የግብረመልስ ስልቶችን በመጠኑም ቢሆን እያሰባጠሩ መጠቀማቸው፣ ቅርጽ እና ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው ግብረመልስ መስጠታቸው፣ ግልጽ የሆነ ግብረመልስ መስጠታቸው፣ የትምህርቱን ይዘትና ዓላማ መሰረት አድርገው የተመጠነ አስተያየት መስጠታቸው እና ግብረመልስ የሰጡበትን ወረቀት በተወሰነ መልኩ በጊዜ መመለሳቸው የግብረመልስ አሰጣጣቸው መልካም መሆኑን የመረጃ ትንታኔ ውጤቱ ያመላክታል፡፡

## 5.2 አስተያየት

የተሰበሰበውን መረጃ እና የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግ የመምህራን ጽሑፋዊ ግብረመልስ ለተማሪዎች ምን አይነት መሆን እንዳለበት እና እንዴት ሊሰጥ እንደሚገባው በሚመለከት ከቀረቡት መነሻ ሃሳቦች ጋር በማጣጣም ቀጥሎ የቀረቡት አስተያየቶች በአጥኚዋ ተጠቁመዋል፡፡

- የቋንቋ መምህራን በመማር ማስተማር ወቅት የሚያዘወትሩት የግብረመልስ አይነት ገምጋሚ ግብረመልስ መሆኑ፡፡ ይህ ደግሞ የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ አነስተኛ በመሆኑ የግብረመልስ አይነቶችን ከጠቀሜታቸው ደረጃ አንጻር እያጣመሩ ግብረመልስ ቢሰጡ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ በበለጠ ሊሻሻል ይችላል፡፡ ስለሆነም ሁሉንም የግብረመልስ ስልቶችን እንደየአስፈላጊነታቸው እያጣመሩ ግብረመልስ ቢሰጡ፤
- መምህራን የሚያዘወትሩት የግብረመልስ ባህሪ አሉታዊነትን የተላበሰ መሆኑን ተገንዝበው እንደየአስፈላጊነቱ አዎንታዊውን እና አሉታዊውን እያጣመሩ ግብረመልስ ቢሰጡ፤
- በመቀጠል በእያንዳንዱ ስህተት ልክ ምልክትን መጠቀም አስቸጋሪ ቢሆንም መምህራን ጠቋሚ የአስተራረም ስልትን በሚጠቀሙበት ጊዜ ስለ ምልክቶች

አጠቃላይ ግንዛቤ ለተማሪዎች ቢሰጧቸው፤

- ጽሁፋዊ ግብረመልስ ውጤታማ እንዲሆን ስለ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ አላማና አተገባበር መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ቢደረግ፤
- በመጨረሻም መምህራን የሁሉንም ተማሪዎች ጽሁፍ ሳይሰለቹ ጽሑፋዊ ግብረመልስ እንዲሰጡ የሚያስተምሯቸው የተማሪዎች ቁጥርና የሚሰጧቸው የክፍለ ጊዜ ብዛት የተመጣጠነ እንዲሆን ቢደረግ፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች

ሂሩት ካሳው፡፡ (1997)፡፡በአዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳደር በሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሴትና የወንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት፡፡ ለኤም.ኤማሚያ የቀረበ ቴሲስ፡፡ አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፡፡ (ያልታተመ)

ባየ ይማም፡፡ (2009)፡፡ የአማርኛ ሰዋሰው፡፡ አዲስ አበባ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1986)፡፡ አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር፡፡ አዲስ አበባ ትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፡፡

ኢሳያስ ይልማ፡፡ (2002)፡፡ የጽሁፍ ክሂልን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የትምህርት አደረጃጀታቸው 10+2 የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ደብዳቤ ለመፃፍ ያላቸው ብቃት በጎባና ሮቤ መሰናዶ ትምህርት ቤት ናሙናነት፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂውማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት ጆርናሊዝም እና የኮምኒኬሽን ኮሌጅ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፡፡ (ያልታተመ)

እታለማሁ ታዬ:: (2006):: የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ፍተሻ በየካቲት 23 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት:: የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር በተግባራዊ ሥነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ:: (ያልታተመ)

እንዳለ ተስፋዬ፡፡ (1992)፡፡ በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ሚና፡፡ ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ መሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ዳዊት ፍሬህይወት፡፡ (2008):: የመምህር-ተማሪ ምክክር እና የመምህር የጽሑፍ ግብረመልስ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ያላቸው ተጽዕኖ፡፡ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በሆኑ የዶዶላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተሳታፊነት የተከናወነ ሙከራዊ ጥናት):: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: (ያልታተመ)

ጌታቸው ቸርነት። (2001)። በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ። የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር። አዲስ አበባ። (ያልታተመ)

ፋንታዬ በየነ። (1988)። የደብረብርሃን ሀይለማሪያም ማሞ መሰናዶ ትምህርት ቤት የአማርኛ መምህራን ቃላዊ ግብረመልስ ስልቶች ፍተሻ። ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)

Anglo, T.A. and Cross, P.k. (1993).*Classroom Assessement Technique: A Handbook for College Teachers*. Sanfrancisco: bass L.t.d.

Anker, W. (2000). “Error and corrective Feedback: update theory and Classroom practice.” Forum.38 (4), 21-24.

Asri, I. (1996). University EFL Teachers’ Written Feedback On Compositions and students’ Reactions, Ph.D Dissertation. University of Essex.(Unpebelished)

Atkins, J. et.al.(1996).*Skills Development Methodology II. Addis Ababa.* Addis Ababa University.

Brookhart, S.M. (2008). *How to Give Effective Feedback to Your Students*.U.S.A.ASCD Publication.

Byme, D. (1991). Teaching Writing Skills.London.Longman .Limited.

Byrne, D. (1988). *Teaching English Writing*. London: longman .Limited.

Cole, P.G and Lorna K.S.C. (1994).*Teaching Principles and Practice*.Sydney Printce Hall of Australia Private Ltd.

Daiker, D.J. (1989). *Writing and Response: Theory, Practice and Research*. NJ: Hampton.

Duker, H. (1983).*Writing through sequence: A process Approach*. Oxford: Oxford University Press.

Guest, G., Mack, N., Mac queen, M., Namely, E., and Woodsong, C. (2005). *Qualitative Research Methods: A data Collectors field guide*. USA: Family Health International. (P.25-52)

Hyland, K. (1990). “Providing Productive Feed back.”*ELT Jornal*.vol .44.No, 4 pp.279-285.

Jacobs, H. et. al. (1881).*Testing ESL Composition: A practical Approach*. Rowler: Massachusetts. New Buny House Publishers.

Kroll, B. (1990). (ed.) Second Language Writing : Research Insights for the classroom. Cambridge: Cambridge University press.

Kroll, B. (ED). (1994). *Second Language Writing* .Cambridge: Cambridge University Press.

Laland, J. (1982). Reducing Composition Errors: An Experiment."*Modern language jornal*, 66(2), 140-49.

Lee, E. (1997). "Evaluating Student Writing."*College Compostion and Communication*. 30:370-374.

Leki, I. (1990). "Coaching From The Margin: Issues in Written Response. In B. kroll (Ed) *Second language writing: Research In Sight for the Classroom*. Cambridge: Cambridge University Press.

Moxely, J. (1989). "Responding To Student Writing: Goals, Method and Alternatives."*Freshman English news*, 17(2), 3-11.

Pincas, A. (1992). *Teacher English writing*. London: Macmillan Publishers.

Raimes, A. (1983). *Techniques in Teaching Writing*. Oxford: University Press.

Richards, J. (1996) .Reflective Teaching in second language classrooms. Cambridge: Cambridge University Press.

Ur, P. (1996). *A Cource in Language Teaching: Practice and Theory*. Cambridge: Cambridge University Press.

Wajnery, B. (1942). *Class Room Observation Tasks*. Cambridge: Cambridge University Press.

Zamel, V. (1985)."Responding to Student Writer."*TESOL Quarterly*, 19(1), 697 – 715

Zamel, V. (1985)."Responding to Student Writing."*TESOL Quarterly*, 19 (1), 79-101.

# አባሪዎች
# አባሪ 1

## በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

### በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

### የድህረ-ምረቃ መርሀ-ግብር

በቅድሚያ ለዚህ የጽሁፍ መጠይቅ ፈቃደኛ በመሆንህ/ሽ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የዚህ የጽሁፍ መጠይቅ ዓላማ "የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

- ጥያቄው ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡
- መጠይቁን በግልህ/ሽ ብቻ ሙላ/ሙይ፡፡
- ፆታ ——————————
- ዕድሜ ——————————

**መመሪያ**፡-

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ የምትስማሙበትን "✓" ምልክት በማድረግ ሀሳብዎን ይግለጹ፡፡

**መልስ የሚሰጠው ፡-**

በጣም እስማማለሁ ፡- 5 ፣ እስማማለሁ ፡- 4 ፣ ለመወሰን እቸገራለሁ፡- 3 ፣ አልስማማም፡- 2 ፣ በጣም አልስማማም፡- 1

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1 | መምህሬ የሚሰጡት ጽሁፎች ሁሉ ይታረማሉ (ግብረመልስ ይሰጡኛል)፡፡ | | | | | |
| 2. | መምህሬ ከጽሁፌ ውስጥ የተሳሳተውን አስተካክለው ያሳዩኛል፡፡ | | | | | |
| 3 | የሚሰጠኝ የግብረመልስ አሰጣጥ አይነት የተለያየ ነው፡፡ | | | | | |
| 4 | መምህሬ በጽሁፌ ውስጥ ስህተቴን እራሴ እንዳርም ያደርጉኛል፡፡ | | | | | |
| 5 | መምህሬ ግብረመልስን እርስ በእርስ (ከተማሪዎች ጋር) እንዳደርግ ያዙኛል፡፡ | | | | | |
| 6 | መምህሬ በጽሁፌ ላይ ያሉትን ስህተቶች ይጠቁሙኛል፡፡ | | | | | |
| 7 | ግብረመልስ በጊዜው አይደረግም፡፡ | | | | | |
| 8 | ከስህተቴ ውስጥ ጥቂቱን ብቻ ያሳዩኛል፡፡ | | | | | |
| 9 | በጽሁፌ ውስጥ የአፃፃፍ ስህተቶችን፣ ሥርዓተ-ነጥቦችን እና ወዘተ. ለይተው ያርሙልኛል፡፡ | | | | | |
| 10 | መምህሬ የሚሰጡኝ ግብረመልስ አይገባኝም (ግልጽ አይደለም)፡፡ | | | | | |
| 11 | መምህሬ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ሳይሰጡኝ ነጥብ ብቻ (ማርክ) ይጽፋሉ፡፡ | | | | | |
| 12 | መምህሬ ከጽሁፋዊ ግብረመልስ ፋንታ በቃል አስተያየት ይሰጡኛል፡፡ | | | | | |
| 13 | መምህሬ በደካማ ጎኔ ብቻ ጽሁፋዊ ግብረመልስ ይሰጡኛል፡፡ | | | | | |
| 14 | መምህሬ በተለየየ ዘዴ ግብረመልስ ይሰጡኛል፡፡ | | | | | |
| 15 | መምህሬ ግብረመልስ የሚሰጡበት ትኩረት የተለያየ ነው፡፡ | | | | | |

**ነፃ አስተያየታችሁን ስጡ**

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በፃፋችሁት በማንኛውም የጽሁፍ አይነቶች ላይ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ግብረመልስ የሚያዘወትሩት በየትኛው የግብረመልስ አይነት ነው?-----------------------------------------------------------------------------

መጠይቁን በመሙላት ስለተባበራችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

# አባሪ 2

## ለመምህራን የሚቀርብ ቃለ-መጠየቅ

### በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

### የድህረ-ምረቃ መርሀ-ግብር

በቅድሚያ ለዚህ ቃለመጠይቅ ፈቃደኛ በመሆንዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የዚህ ቃለመጠይቅ ዓላማ "የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ለሚደረገው ጥናት መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡

**ጥያቄ**

1. በተማሪዎች ጽሁፋዊ መልመጃዎች ላይ ግብረመልስ ይሰጣሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን?
2. የተለያዩ የግብረመልስ አይነቶችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ፡- አመቻች ግብረመልስ ፣ ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ፣ አስተካካይ ግብረመልስና ገምጋሚ ግብረመልስ፡፡ አልጠቀምም ካሉ ለምን?
3. የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልሶች ምን ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው?
4. በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ ግብረመልሶችን በጊዜው ይሰጣሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን?
5. የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከመዋቅር አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ ፡- በሆሄያት ፣ በቃላት ፣ በዐረፍተ ነገሮች ፣ በሰዋሰዋዊ ስህተቶች ፣ በሥርዓተ ነጥብ ስህተቶችና ወዘተ. ናቸው፡፡
6. የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከይዘት አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ ፡- የመልዕክቱ ትክክለኛነት ላይ ሂሳዊ አስተያየት በመስጠት ፣ በመጠየቅና በማስተካከል ናቸው፡፡
7. ግብረመልሶቹ ምን ያህል ከክፍል ደረጃው ጋር የተገናዘቡ ናቸው?

8. የግብረመልስ አሰጣጥ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ፡- ቀጥተኛ እርማት ፣ ኢ-ቀጥተኛ እርማት ፣ አዎንታዊ እና አሉታዊ ግብረመልስ ፣ ጥያቄ እና አስተያየቶች፡፡ ካልተጠቀሙ ለምን?
9. የሚሰጡት ግብረመልሶች ከሳምንታዊ ክፍለ ጊዜው እና ከተማሪዎች ብዛት ጋር ምን ያህል እያጣጣሙ ይሰጣሉ?
10. በተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃ ላይ ስለሚሰጠው ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ መምህራን ምን ማድረግ አለባቸው?ተማሪዎችስ?

# አባሪ 3

## ከመቅረጸ-ድምጽ ወደ ጽሁፍ የተሸጋገረ የመምህራን ቃለ-መጠይቅ

ማስታወሻ፡- ከመምህራን ጋር የተደረገው ቃለ-መጠይቅ የመምህራንን ትክክለኛ መጠሪያ ስያሜ በመጠቀም ነው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ዘገባ ላይ ግን የምርምር ስነ-ምግባራዊ መርሆን ከመጠቀም አንጻር የመምህራንን በግል መጠሪያ ስያሜ ከመጠበቅ አንጻር የመምህራንን በግል መጠሪያ ስያሜ (የተጸውኦ ስም) በወል ስም (መምህር) ተቀይሮ መቅረቡን ልብ ይሏል፡፡

### መምህር አንድ

በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፍቃደኛ በመሆንህ/ሽ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዓላማ ‹‹የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡትን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት፡፡››በሚል ርዕስ ለሚደረገው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

**1ኛ. ጥያቄ፡- በተማሪዎች ጽሁፋዊ መልመጃዎች ላይ ግብረመልስ ይሰጣሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን?**

መልስ፡- እሰጣለሁ፡፡

**2ኛ. ጥያቄ፡-የተለያዩ የግብረመልስ አይነቶችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ ፡- አመቻች ግብረመልስ ፣ ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ፣ አስተካካይ ግብረመልስና ገምጋሚ ግብረመልስ፡፡ አልጠቀምም ካሉ ለምን?**

መልስ፡- ያው ሁሉንም እጠቀማለሁ፡፡ግን ሁሌም ባይሆን አልፎ አልፎ ሁሉንም ማወቅ ስላለባቸው ለመጠቀም እሞክራለሁ፡፡ ግን በእኔ ትኩረት የማደርገው በገምጋሚ ግብረመልስ ነው፡፡

**3ኛ. ጥያቄ፡-የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልሶች ምን ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው?**

መልስ፡- በግምጋሚ ግብረመልስ በመስጠት ነው፡፡

**4ኛ. ጥያቄ፡-በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ ግብረመልሶችን በጊዜው ይሰጣሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን?**

መልስ፡- ያው እስኬጁልም ስላለ ከጊዜው ጋር ለማጣጣም በማሳጠር እሞክራለሁ፡፡

**5ኛ. ጥያቄ፡-የሚሰጡትጽሁፋዊ ግብረመልስ ከመዋቅር አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ ፡- በሆሄያት ፣ በቃላት ፣ በአርፍተ ነገሮች ፣ በሰዋሰዋዊ ስህተቶች ፣ በሥርዓተ ነጥብ ስህተቶችና ወዘተ. ናቸው፡፡**

መልስ፡- ያው ሁሉንም ያካትታል ግን ቢሆንም በአርፍተ ነገር ላይ አተኩራለሁ፡፡አርፍተነገር በሚሰሩበት ጊዜ ሁሉንም ቃላትና የሥርዓተ- ነጥብ አጠቃቀምንና ሌሎችንም አካቶ በውስጡ ስለሚይዝ ነው ፡፡ ያው ሁለንም መነካካቴ አይቀርም፡፡

**6ኛ. ጥያቄ፡-የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከይዘት አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ፡- የመልዕክቱ ትክክለኛነት ላይ ሂሳዊ አስተያየት በመስጠት ፣ በመጠየቅና በማስተካከል ናቸው፡፡**

መልስ፡-ያው ይዘቱ አንዱ የትምህርቱ ፓርት ነው ፤ ይዘት ግድ ነው፡፡ እንደማጠሩና መርዘሙ እንደ ርዕሱ እሰጣለሁ ማለት ነው፡፡

**7ኛ. ጥያቄ፡-ግብረመልሶቹ ምን ያህል ከክፍል ደረጃው ጋር የተገናዘቡ ናቸው?**

መልስ፡-ያው መጽሐፉን በምናይበት ጊዜ የተለያዩ ችግሮች አይጠፉም፡፡ግን እኛ የተለያዩ ሪፈረንሶችን በመጠቀም በማሳጠርና በማስተካከል እሰጣለሁ፡፡ መጽሐፉ የራሱ የኦርደር ችግር አለበት፡፡ መምህር እንደ መሆኔ መጠን በራሴ ስልት እሰጣለሁ፡፡

**8ኛ. ጥያቄ፡-የግብረመልስ አሰጣጥ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ ፡- ቀጥተኛ እርማት ፣ ኢቀጥተኛ እርማት ፣ አዎንታዊ እና አሉታዊ ግብረመልስ ፣ ጥያቄ እና አስተያየቶች፡ ፡ ካልተጠቀሙ ለምን?**

መልስ፡- በብዛት እኔ የምጠቀመው ቀጥተኛ እርማት ነው፡፡ ያው ከተማሪዎች አቅም አንጻር ነው፡፡ ያው በቀጥታ እራሴ ልጽፍላቸው እችላለሁ፡፡ቋንቋውን በማስፋት ደረጃ እንዲታይልኝ ማለት ነው፡፡ ለተማሪው በተለያ ቃላት ሊገባው ስለ ሚችል በብዛት እኔ የምጠቀመው ግን ቀጥተኛ እርማት ነው፡፡አልፎ አልፎ ኢ-ቀጥተኛም እርማት ሊኖር ይችላል ተማሪው በተለያየ መንገድ እንዲገባው ማለት ነው፡፡

**9ኛ. ጥያቄ፡-የሚሰጡት ግብረመልሶች ከሳምንታዊ ክፍለ ጊዜው እና ከተማሪዎች ብዛት ጋር ምን ያህል እያጣጣሙ ይሰጣሉ?**

መልስ፡-ያው እስኬጁልምስላለ ማጣጣም ግድ ነው፡፡ርዕሱም እንዲገፋልኝ መጽሀፉም ብዙ ስለሆነ በማሳጠርም በተለያየ ሲስተም በመጠቀም በማጣጣም በሚለው ብዙ ጊዜ እጠቀማለሁ፡፡ሜንፖይንቱን በመስጠት ማለት ነው፡፡ምክንያቱም የዛሬን ሣምንት ትምህርት ለሚቀጥለው ማገኘት የለባቸውም ፤ ሌላ አዲስ ነው ማወቅ የሚጠቅባቸው፡፡

**10ኛ. ጥያቄ፡-በተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃ ላይ ስለሚሰጠው ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ መምህራን ምን ማድረግ አለባቸው? ተማሪዎችስ?**

መልስ፡-ያው መጀመሪያ መምህሩ የተማዎቹን አቅም ማወቅ አለበት፡፡ ምን ያህል ይችላሉ ምን ያህል አይችሉም በማለት ማለትም ባዘዛቸው ጽፌው ይመጣሉ ፤ ወይስ ጽፌው ሲመጡ ምን ያህል ይለማመዳሉ ፣ ያውቃሉ ብሎ ማገናዘብ አለበት፡፡ምክንያቱም ጽፌው ሲመጡ ሲያዛቸው ይጽፋሉ ፤ ሲያዛቸው ይጠይቃሉ፡፡ ስለዚህ የጽፈት አድማሳቸውን ለማስፋፋት  መምህሩ ማዘዝ አለበት፡፡ ከርዕሱ ጋርም ይሁን ከመጽሀፉ ውጭ አቅማቸውን በሚመጥን መርጦ የጽህፈት አድማሳቸውን ለማስፋት ይረዳቸዋል፡፡

## መምህር ሁለት

በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፍቃደኛ በመሆንህ/ሽ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዓላማ ‹‹የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡትን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት፡፡›› በሚል ርዕስ ለሚደረገው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

**1ኛ. ጥያቄ፡-በተማሪዎች ጽሁፋዊ መልመጃዎች ላይ ግብረመልስ ይሰጣሉ?አልሰጥም ካሉ ለምን?**

መልስ፡- እሰጣለሁ፡፡

**2ኛ. ጥያቄ፡-የተለያዩ የግብረመልስ አይነቶችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ ፡- አመቻች ግብረመልስ ፣ ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ፣ አስተካካይ ግብረመልስና ገምጋሚ ግብረመልስ፡፡ አልጠቀምም ካሉ ለምን?**

መልስ፡- ከነዚህ ከተዘረዘሩት ውስጥ የምጠቀመው አስተካካይ ወይም ስህተትን መጠቀምና ገምጋሚ ግብረመልስ ናቸው፡፡ ትዕዛዛዊ ግብረመልስ አልጠቀምም ምክንያቱም ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን ከ5ኛ ክፍል ስለሚጀምሩ እራሳቸው ሊያርሙ ስለማይችሉ ነው፡፡

**3ኛ. ጥያቄ፡-የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልሶች ምን ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው?**

*መልስ፡- ስህተትን በመጠቆም ተማሪዎች የሚሰጡትን ስህተት እጠቁማቸዋለሁ፡፡*

**4ኛ. ጥያቄ፡- በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ ግብረመልሶችን በጊዜው ይሰጣሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን?**

*መልስ፡-አዎ እሰጣለሁ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ ወዲያው ካልተጠቆሙ ስህተት ውስጥ ስለሚገቡ ይህን በግልጽ አደርገዋለሁ፤ እሰጣለሁ፡፡*

**5ኛ. ጥያቄ፡-የሚሰጡትጽሁፋዊ ግብረመልስ ከመዋቅር አንጻር ምን ይመስላል?ለምሳሌ ፡- በሆሄያት ፣ በቃላት ፣ በዐረፍተ ነገሮች ፣ በሰዋሰዋዊ ስህተቶች ፣ በሥርዓተ ነጥብ ስህተቶችና ወዘተ. ናቸው፡፡**

*መልስ፡-እሰጣለሁ፡፡ እንግዲህ እነኚህ ተማሪዎች ይህንን ስህተቶች ካልተማሩ ያው ምንም ትምህርት ተማሩ ስለማይባል በቃላት ፣ በስርዓተ-ነጥብና በሰዋሰው እንዲሁም ሌሎችን ስህተቶችን የግድ ነው መስጠት አለብኝ ተማሪው እንዲያውቅ ማለት ነው፡፡*

**6ኛ. ጥያቄ፡- የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከይዘት አንጻር ምን ይመስላል?ለምሳሌ ፡- የመልዕክቱ ትክክለኛነት ላይ ሂሳዊ አስተያየት በመስጠት ፣ በመጠየቅና በማስተካከል ናቸው፡፡**

*መልስ፡-በጥያቄናመልስ መንገድ ገለጻ አደርጋለሁ፡፡የመልክቱም ትክክለኛነት እከታተላለሁ፡፡*

**7ኛ. ጥያቄ፡- ግብረመልሶቹ ምን ያህል ከክፍል ደረጃው ጋር የተገናዘቡ ናቸው?**

*መልስ፡- እንግዲህ በክፍል ደረጃቸው መሰረት እሰጣቸዋለሁ፡፡ነገር ግን የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ስላለሆነ ያስቸግረናል፡፡ ቢሆንም ያንን አጣጥሜ ለመስራት እሞክራለሁ፡፡ እንደዛ እያደረኩ ነው የምሠራው፡፡*

**8ኛ. ጥያቄ፡-የግብረመልስ አሰጣጥ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ ፡- ቀጥተኛ እርማት ፣ ኢቀጥተኛ እርማት ፣ አዎንታዊ እና አሉታዊ ግብረመልስ ፣ ጥያቄ እና አስተያየቶች፡፡ ካልተጠቀሙ ለምን?**

*መልስ፡- እጠቀማለሁ፡፡ እንግዲህ እኔ በቀጥተኛ እርማት ድክመታቸውን መጠቆም ስለሆነ ግድ ነው፡፡ በቀጥተኛ እርማት ምልክቶችን በመጠቀም እጠቁማቸዋለሁ፡፡ አዎንታዊ ግብረመልስ በቀጥታ ሚያገልግል ስለሆነ ይህንን ከተማሪዎቹ የቋንቋ ችግር አንጻር ይህንን*

አልጠቀመውም፡፡ሌላው አሉታዊ ግብረመልስ ተባለውን የተማሪውን ሞራል ስለሚነካ ይህንን መጠቀም ሌሎችም መምህራኖች ይህንን ባይጠቀሙ እሞክራለሁ፡፡

**9ኛ. ጥያቄ፡- የሚሰጡት ግብረመልሶች ከሳምንታዊ ክፍለ ጊዜው እና ከተማሪዎች ብዛት ጋር ምን ያህል እያጣጣሙ ይሰጣሉ?**

መልስ፡- እንግዲህ በእኛ ትምህርት ቤት ያው የተማሪው ቁጥር በአንድ ክፍል እጅግ በርካታ ነው፡፡ክፍለ ገዜውም በሣምንት አናሳ ነች፡፡ ሁለት ክፍለ ጊዜ ነች ያለችን፡፡ቢሆንም ይሄ ችግር ቢኖርም ባለችን ክፍለ ጊዜ አናሣ ብትሆንም ይህንን እያጣጣምኩ እሰጣለሁ፡፡

**10ኛ. ጥያቄ፡-በተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃ ላይ ስለሚሰጠው ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ መምህራን ምን ማድረግ አለባቸው? ተማሪዎችስ?**

መልስ፡-በየጊዜው የተማሪዎችን የእጅ ጽሑፍ መከታተል መምህራኖች አለባቸው እንዲሁም ተማሪዎች በርትተው ሰርተው ማሣየት አለባቸው እላለሁ፡፡

**መምህር ሶስት**

በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፍቃደኛ በመሆንህ/ሽ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዓላማ ‹‹የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡትን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት፡፡›› በሚል ርዕስ ለሚደረገው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

**1ኛ. ጥያቄ፡-በተማሪዎች ጽሁፋዊ መልመጃዎች ላይ ግብረመልስ ይሰጣሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን?**

መልስ፡- አዎ እሰጣለሁ፡፡

**2ኛ. ጥያቄ፡-የተለያዩ የግብረመልስ አይነቶችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ ፡- አመቻች ግብረመልስ ፣ ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ፣ አስተካካይ ግብረመልስና ገምጋሚ ግብረመልስ፡፡ አልጠቀምም ካሉ ለምን?**

መልስ፡- እሺ… ከእነዚህ ውሰጥ አመቻች ግብረመልስ እጠቀማለሁ፡፡ አስተካካይ ግብረመልስና ገምጋሚ ግብረመልስ እጠቀማለሁ ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ግን አልሰጥም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የእራሳቸውን ሰህተት እንዲያስተካክሉ የሚል ስለሆነ ተማሪዎቹ ራሳቸው ማስተካከል ከበድ ስለሚላቸው እሱን አልጠቀመም፡፡

**3ኛ. ጥያቄ፡-የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልሶች ምን ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው?**

*መልስ፡- ገምጋሚ ግብረመልስ ላይ፡፡*

**4ኛ. ጥያቄ፡- በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ ግብረመልሶችን በጊዜው ይሰጣሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን?**

*መልስ፡- አይ እሰጣለሁ፡፡ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ መልሱን በጽሁፋቸው ላይ ትኩረት አድርጌ እሰጣለሁ፡፡*

**5ኛ. ጥያቄ፡- የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከመዋቅር አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ ፡- በሆሄያት ፣ በቃላት ፣ በዐረፍተ ነገሮች ፣ በሰዋሰዋዊ ስህተቶች ፣ በሥርዓተ ነጥብ ስህተቶችና ወዘተ. ናቸው፡፡**

*መልስ፡-እሰጣለሁ ሁሉንም፡፡ ምክንያቱም ትምህርቱ ጽሁፍ ላይ ያለው ስርዓተ-ነጥብንም ፣ የሆሄያትን ግድፈትንም ፣ የቃላት ግድፈትንምና የሰዋሰው ሁሉንም የሚመለከት ስለሆነ ሁሉንም በተቻለ መጠን ለማስያዝ ለማስጨበጥ ወይም ስህተታቸውን እንዲያርሙ ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡*

**6ኛ. ጥያቄ፡-የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከይዘት አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ ፡- የመልዕክቱ ትክክለኛነት ላይ ሂሳዊ አስተያየት በመስጠት ፣ በመጠየቅና በማስተካከል ናቸው፡፡**

*መልስ፡-ሁሉንም እጠቀማለሁ፡፡ያው ጽሁፉ የሚያተኩረው ስህተቶችን ለማረም ስለሆነ እዚያ ላይ ትኩረት ሰጥቼ እከታተላለሁ ፤ እንዲያስተካክሉ አደርጋለሁ፡፡*

**7ኛ. ጥያቄ፡- ግብረመልሶቹ ምን ያህል ከክፍል ደረጃው ጋር የተገናዘቡ ናቸው?**

*መልስ፡-እንዳይከብድም ፤ እንዳይቀልም ፤ መካከልኛ አድርጌ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እሰጣቸዋለሁ፡፡*

**8ኛ. ጥያቄ፡-የግብረመልስ አሰጣጥ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ ፡- ቀጥተኛ እርማት ፣ ኢቀጥተኛ እርማት ፣ አዎንታዊ እና አሉታዊ ግብረመልስ ፣ ጥያቄ እና አስተያየቶች፡፡ ካልተጠቀሙ ለምን?**

*መልስ፡-ከእነዚህ ውስጥ አራቱን እጠቀማለሁ፡፡አሉታዊ ግብረመልስን ግን አልጠቀመም፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎችን የጽሁፍ ተነሳሽነትና ሞራላቸውን ስለሚነካ ነው፡፡*

**9ኛ. ጥያቄ፡-የሚሰጡት ግብረመልሶች ከሳምንታዊ ክፍለ ጊዜው እና ከተማሪዎች ብዛት ጋር ምን ያህል እያጣጣሙ ይሰጣሉ?**

መልስ፡- የክፍለ ጊዜው ብዛት አነስተኛ ቢሆንም ያው ሁለት ስለሆኑ በዛን ሰዓት የተማሪው ብዛትም ትንሽ በዛ ያለ ስለሆነ በተቻለ መጠን እነሱን አጣጥሜ የተማሪውን ጽሁፍ ለማሻሻል ጥረት አደርጋለሁ፡፡

**10ኛ. ጥያቄ፡- በተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃ ላይ ስለሚሰጠው ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ መምህራን ምን ማድረግ አለባቸው? ተማሪዎችስ?**

መልስ፡-መምህራን ተማሪዎችን በማይጎዳ መልኩ እነዲገባቸው በማድረግ ቀለል ያሉ ጽሁፎችን በመስጠት መጀመሪያ ማለማመድ፡፡ ካዛ ቀስ ቀስ እያሉ ደግሞ ያው የተለያዩ ጽሁፎችን በመስጠትና ስህተታቸውን እንዲያውቁ ፣እንዲያርሙና እንዲያስተካክሉ በማድረግ የተቻለውን እገዛ በመምህሩ ማድረግ ነው፡፡ ተማሪዎች ደግሞ ያንን መሰረት አድረገው ከመምህሩ የሚሰጠውን ስህተት ትኩረት ሰጥተው ከስህተታቸው እንዲማሩወይም ከስህተታቸው እንዲመለሱና አስተካክለው እንዲጽፉ ያደርጋሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡

**መምህር አራት**

በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፍቃደኛ በመሆንህ/ሽ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዓላማ ‹‹የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መልመጃ ላይ የሚሰጡትን ጽሁፋዊ ግብረመልስ አተገባበር ፍተሻ በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ በሹርሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት፡፡›› በሚል ርዕስ ለሚደረገው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

**1ኛ. ጥያቄ፡- በተማሪዎች ጽሁፋዊ መልመጃዎች ላይ ግብረመልስ ይሰጣሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን?**

መልስ፡-አዎ እሰጣለሁ፡፡

**2ኛ. ጥያቄ፡- የተለያዩ የግብረመልስ አይነቶችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ ፡- አመቻች ግብረመልስ ፣ ትዕዛዛዊ ግብረመልስ ፣ አስተካካይ ግብረመልስና ገምጋሚ ግብረመልስ፡፡ አልጠቀምም ካሉ ለምን?**

መልስ፡- አዎ… የተለያዩ የግብረመልስ አይነቶችን በተለይም ከተራ ቁጥር1-3 ያሉትን እጠቀማለሁ፡፡ አመቻችን በአብዛኛው የማዘውትረው ይሆናል፡፡

**3ኛ. ጥያቄ፡- የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልሶች ምን ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው?**

*መልስ፡-አዎ …ከላይ እንደተጠቀስኩት የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልሶች በአመቻች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡*

**4ኛ. ጥያቄ፡- በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ላይ ግብረመልሶችን በጊዜው ይሰጣሉ? አልሰጥም ካሉ ለምን?**

*መልስ፡-አዎ… ለተማሪዎች በጽሁፍ ሥራ ላይ የምሰጠው ግብረመልስ በጊዜው ነው የምሰጠው፡፡*

**5ኛ. ጥያቄ፡- የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከመዋቅር አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ ፡- በሆሄያት ፣ በቃላት ፣ በዐረፍተ ነገሮች ፣ በሰዋሰዋዊ ስህተቶች ፣ በሥርዓተ ነጥብ ስህተቶችና ወዘተ. ናቸው፡፡**

*መልስ፡-አዎ… የጽሁፍ ስራ ላይ የምሰጠው የግብረመልስ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነው፡ ፡ በአብዛኛው እና የሚጽፉት በአማርኛ ስለሆነ የ1ኛ ቋንቋ በ2ኛ ቋንቋ ንግግራቸውና ጽሁፋቸው ላይ ተጽዕኖ እንዳያመጣ በማሰብ በፊደል ላይ ትኩረት አላደርግም፡፡ ነግር ግን ሥርዓተ-ነጥቦችንና ሰዋሰዎችን በልዩ ትኩረት እርማት እሰጣለሁ፡፡*

**6ኛ. ጥያቄ፡- የሚሰጡት ጽሁፋዊ ግብረመልስ ከይዘት አንጻር ምን ይመስላል? ለምሳሌ ፡- የመልዕክቱ ትክክለኛነት ላይ ሂሳዊ አስተያየት በመስጠት ፣ በመጠየቅና በማስተካከል ናቸው፡፡**

*መልስ፡-አዎ… ለተማሪዎች የምሰጠው ግብረመልስ በተለይ በይዘቱ ትክክለኛነት ላይ ግብረመልስ በትኩረት እሰጣለሁ፡፡*

**7ኛ. ጥያቄ፡- ግብረመልሶቹ ምን ያህል ከክፍል ደረጃው ጋር የተገናዘቡ ናቸው?**

*መልስ፡- ግብረመልሶቹ ተማሪዎች ካሉት የክፍል ደረጃው ያነሰና በታች እንዳይሆን ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ተማሪዎቹ ባላቸው የትምህርት ደረጃ ልክ እንዲጽፉ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡ ከተቻለ ግን ከዛ በላይ እንጂ በታች እንዳይሆን ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ፡፡*

**8ኛ. ጥያቄ:- የግብረመልስ አሰጣጥ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ? ለምሳሌ :- ቀጥተኛ እርማት ፣ ኢቀጥተኛ እርማት ፣ አዎንታዊ እና አሉታዊ ግብረመልስ ፣ ጥያቄ እና አስተያየቶች: : ካልተጠቀሙ ለምን?**

*መልስ:-አዎ... ለተማሪዎች ግብረመልስ ሁሉንም ዘዴዎች ሳይሆን አሉታዊውን አልጠቀምም ግን ሌሎችን የግብረመልስ ዓይነቶችን እሰጣለሁ። ከአሉታዊ በስተቀር ማለት ነው።*

**9ኛ. ጥያቄ:- የሚሰጡት ግብረመልሶች ከሳምንታዊ ክፍለ ጊዜው እና ከተማሪዎች ብዛት ጋር ምን ያህል እያጣጣሙ ይሰጣሉ?**

*መልስ:-አዎ ግብረመልሱን ከተማሪዎች ቁጥርና ካለው ክፍለ ጊዜ ጥበት አንጻር አስቸጋሪ ቢሆንም ተማሪዎች የሚጽፉትን ጽሁፎች ሰብስቦ ወደ ቤት እና ወደ እስታፍ በመውሰድ ለተማሪዎች ግብረመልስ ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ።*

**10ኛ. ጥያቄ:- በተማሪዎች የጽሁፍ መልመጃ ላይ ስለሚሰጠው ጽሁፋዊ ግብረመልስ አሰጣጥ መምህራን ምን ማድረግ አለባቸው?ተማሪዎችስ?**

*መልስ:-አዎ... በመጀመሪያ ተማዎች ማድረግ ያለባቸው ነገር ቢኖር ለጽሁፍ ትኩረት በመስጠት እንዲጽፉ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎቹ ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ ደግሞ የተሻለ አንባቢ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል። ምክንያቱም ተማሪዎች የሚጽፉት ያነበቡትን ነገር ነው። ጽሁፋቸው የሚስተካከለው ብዙ ማንበብ ሲችሉ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች ላይብረሪ መግባት የተለያየ ቦታ የሚገኙ ጽሁፎችን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል። ያንን የነበቡትን ስለሚጻፍ ማለት ነው። ተማሪዎች ብዙ ካነበቡ በኂላ ብዙ እንዲጽፉ ይጠበቅባቸዋል። ያዩትን የአካባቢያቸውን ሁኔታ ያነበቡትን ነገርና ገጠመኞቻቸውን እንዲጽፉ ተማሪዎች ይጠበቅባቸዋል።*

*ከመምህራን ምን ይጠበቃል ለሚለው መምህራን ተማሪዎቻቸው እንዲጽፉ በትኩረት መከታተልና ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል። የሥነ-ጽሁፍ ውድድሮችን በተማሪዎች መካከል ቢያደርጉ መልካም ይሆናል። መምህራን ተማሪዎቻቸውን በሚኒሚዲያ በስነ-ጽሁፍ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ በተለያዩ ክበቦች በተለይም ቢያበረታቱአቸው መልካም ነው። ከዚህ በተጨማሪ የትምህርት ቤቱ አቅም በፈቀደ መጠን ተማሪዎች የጻፉትን ጽሁፍ ራሳቸው እንዲያነቡ ወይም በጓደኞቻቸው እንዲነበቡ ወይም በመቅረጸ ድምጽ እና በመሳሰሉት ተቀርጾ እንዲሰሙት ማድረግ ጥሩ ነው በማለት ሀሳብ ይኖረኛል።*

# አባሪ 4

## የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች መረጃ መመዝገቢያ ፎርም

**የትምህርት ቤቱ ስም**____________________

**የክፍል ደረጃ**_____________

**የመማሪያ ክፍል**_________

**ቀን**____________________

| ተ.ቁ | የተማሪው ስም | ጾታ | አድራሻ | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |
| 6 | | | | |
| 7 | | | | |
| 8 | | | | |
| 9 | | | | |
| 10 | | | | |
| 11 | | | | |
| 12 | | | | |
| 13 | | | | |
| 14 | | | | |
| 15 | | | | |
| 16 | | | | |
| 17 | | | | |
| 18 | | | | |

**ወንድ-------------**

**ሴት ------------**

**ድምር-----------**